# ‹‹ከማያምኑ ጋር››

## ጋብቻና ማኅበራዊ ሕይወት

አድራሽ፡- ዲያቆን ኀብረት የሺጥላ

ስልክ 251 011 2 132854
251 091 1 617077
የመ.ሣ. ቁ 59012
E-mail Hibretyes@yahoo.com

www.ethiopianorthodox.org

‹‹ከማያምኑ ጋር››
ጋብቻና ማኅበራዊ ሕይወት
ወርኅ ሚያዝያ ፳፻፩
የመጀመሪያ ኅትም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው!
© ALL RIGHTS RESERVED.

## መታሰቢያነቷ

በብዙ ተጋድሎ ኖረው በሰማንያ አምስት ዓመታቸው ታኅሣስ ፳ ፳፻፩ ዓ.ም ላረፉት ታላቁ አባት አባ ይትባረክ ወልደ ሥላሴ ትሁንልኝ!

## ምስጋና

የሽፋን ስዕሉን ዲዛይን ለሠራልኝ
ለአቶ አብርሃም ታምሩ

# ማውጫ

ምዕራፍ አንድ ..... 7
- ‹‹አንዲት ሃይማኖት›› ..... 7-11
- የሃይማኖት ልዩነት ..... 11-18
- ሃይማኖትን ደብቆ መቅረብ ..... 18-20
- ‹‹ከማያምኑ ጋር›› ..... 20-22
- ‹‹የማይመች አካሄድ›› ..... 22-23

ምዕራፍ ሁለት ..... 24
- ለጋብቻ ሃይማኖት መስፈርት ይሆናል? ..... 24-35
- ‹‹ከማያምኑ ጋር›› መጋባት ያለው መዘዝ ..... 35-40
- ‹‹ከማያምኑ ጋር›› ላለመጋባት የሚከፈል መሥዋዕትነት ..... 40-44

ምዕራፍ ሦስት ..... 45
- ‹‹ከማያምኑ ጋር›› ጋብቻ በዘመነ ሕገ ልቡና ..... 45-49

ምዕራፍ አራት ..... 50
- ‹‹ከማያምኑ ጋር›› ጋብቻ በዘመነ ኦሪት ..... 50-52

ምዕራፍ አምስት ..... 53
- ‹‹ከማያምኑ ጋር›› ጋብቻ በዘመነ ወንጌል ..... 53-57

ምዕራፍ ስድስት ..... 58
- ‹‹ከማያምኑ ጋር›› ስለመጋባት በቀኖና ቤተ ክርስቲያን የተጻፈ ..... 58-61

ምዕራፍ ሰባት ..... 62
- ‹‹ከማያምኑ ጋር›› ጋብቻን በተመለከተ ልዩ ልዩ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው ..... 62-90

ምዕራፍ ስምንት ..... 91
- ‹‹ከማያምኑ ጋር›› ማኅበራዊ ኑሮ ..... 91-94
- ‹‹ከሰው ሁሉ›› ጋር በሰላም መኖር ..... 94-95
- የማያምኑትን አለመምሰል ..... 95-97
- የማያምኑትን እንዴት እንያቸው? ..... 97-98
- ለመልካም ሥራቸው ዋጋ መስጠት ..... 98-100
- ወደመናፍቃን አዳራሽ፣ ወደ መስጊድ እና ጠንቋይ ቤት ስለመሄድ ..... 101-103
- ‹‹መብል አትብሉ›› ..... 103-104
- ‹‹ሰላም ተባባሉ›› ..... 104-105
- ዋቤ መጻሕፍት ..... 106
- ዜና መጻሕፍት ..... 107-108

# መቅድም

ብዙዎች ‹‹ከማያምኑ ጋር›› በጋብቻ አንድ ከሆኑና ልጆች ከወለዱ በኋላ ሕይወታቸው ሲፈተሽ ሁሉም ለማለት በሚያስደፍር መልኩ ትዳራቸውን ሲያማርሩ ይገኛሉ፡፡ ፈተናውን መሸከም አቅቷቸው እስከ መፋታት የሚደርሱት ባልና ሚስት ቁጥርም ጥቂት የሚባል አይደለም፡፡ በእውነቱ ይህ ክሥተት ሁሉንም ሰው የሚያሳዝን ነው፡፡ በተለይ ከዚህ ዓይነት ትዳር የተወለዱት ጨቅላ ሕፃናት የወደፊት ዕጣ ፈንታ ሲያስብ ልቡ የማይደማ የሰው ዘር ይኖራል ብዬ አላስብም፡፡

ይህን መሰል ክፉ አጋጣሚ በመቀነሥ ወገናዊ ኃላፊነቴን ለመወጣት ይህችን መጽሐፍ ጽፌአለሁ፡፡ ‹‹ከማያምኑ ጋር›› ተጫጭተው ለጋብቻ የሚዘጋጁ ሰዎች ወደፊት በነፍስም ሆነ በሥጋ የሚጠብቃቸውን ተጠያቂነት፣ አለመግባባትና የመፋታት አደጋ ከወዲሁ ተገንዝበው መፍትሔ እንዲያፈላልጉ ጠቃሚ ምክር በመለገስ ይህች መጽሐፍ የበኩሏን አስተዋጽኦ ታደርጋለች ብዬ አምናለሁ፡፡

በእርግጥ መጽሐፏ በዋናነት የምትመለከተው ወደ ጋብቻ የሚሄዱ ሰዎችን ነው፡፡ ይሁን እንጂ በሃይማኖት ተለያይተው ሳለ ቀደም ሲል የተጋቡትን ሰዎች የሚረዳ ብዙ ቁም ነገር ይዛለች፡፡ ከተጋቡ በኋላ አንዱ ወገን ለብቻው ወደ ክህደት የመሄድ አጋጣሚ ለተፈጠረበት ትዳርም የመፍትሔ ሐሳብ አላት፡፡ በሚገባ ያንብቧትና ለሚመለከታቸው ሰዎች ያበርክቱላቸው፡፡ እንዲያነቧትም ያበረታቷቸው!

ከዚህ በፊት በልዑል እግዚአብሔር አጋዥነት ‹‹ትዳርና ተላጽቆ››፣ ‹‹ሕይወተ ወራዙት - የወጣቶች ሕይወት›› አንደኛና ሁለተኛ መጽሐፍ እንደዚሁም ‹‹ትምህርተ ውግዘት›› የሚሉ አራት መጻሕፍትን ለንባብ አብቅቻለሁ፡፡ ይህን መጽሐፍ የምታነቡ አብዛኞቻችሁ ‹‹ትዳርና ተላጽቆ›› እና ‹‹ሕይወተ ወራዙት›› የሚሉትን እንደምታውቋቸው እገምታለሁ፡፡

‹‹ትምህርተ ውግዘት›› የተሰኘችው የመጨረሻዋ መጽሐፍ ብዙ ቁም ነገር ያላት፣ በአጭር ጊዜ የምትነበብና ኪስ የማትጎዳ አነስተኛ ይዘት ያላት ሆና ሳለ እንደሚገባት ያህል አልተነበበችም፡፡ ይህም በርእሷ ብቻ ስለተመዘነች እንደሆነ ገብቶኛል፡፡

አንድ ስጋት አለኝ! እንዲህ ዓይነቱ የተሳሳተ የመጻሕፍት አመራረጥ ጸሐፊዎች የአንባቢያቸውን ፍላጎት ለማሟላትና ሸጦ ለመጠቀም ሲሉ በተወሰኑ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ብቻ ትኩረት ሰጥተው እንዲጽፉ ያደርጋቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ ምን ጉዳት እንዳለው ከእናንተ የተሰወረ አይደለም፡፡ በዚህ መንገድ በጣም ጠቃሚ መጽሐፍ ጽፈው በርእሱ ብቻ ያልተነበበላቸውና ሌላ የመጻፍ ፍላጎታቸውን ያጡ በአንጻሩ ደግሞ ወሬ እንጂ ምንም ፍሬ የሌለው መጻሕፍቶቻቸውን በብዙ ቅጂ የሸጡ ሰዎችን እናውቃለን፡፡

መጻሕፍትን አዘጋጅቶ ማቅረብ የመንፈሳዊ አገልጋዮች ግዴታ ሲሆን ገዝቶ ማንበብ ደግሞ የምእመናን ኃላፊነት ነው፡፡ ስለዚህ ድርሻችሁን ለመወጣት ትጉ፡፡ ‹‹ጌታ ቢፈቅድ ብንኖርም›› በቅርብ ጊዜ በ‹‹ሕይወተ ወራዙት›› ክፍል ሦስት መጽሐፍ ዳግመኛ እንደምንገናኝ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ጸሎታችሁ አይለየኝ!

ጸሐፊው

www.ethiopianorthodox.org

## መግቢያ

ይህች አነሥተኛ መጽሐፍ ስምንት ምዕራፎች አሏት። የመጀመሪያው ምዕራፍ እውነተኛ ሃይማኖት አንዲት ብቻ መሆኗን በማስረገጥ ይናገራል። አያይዞም «የማያምኑ» የሚባሉት እነማን እንደሆኑና ከእነርሱ ጋር ምእመናን ሊኖራቸው ስለሚገባ ተገቢ ቅርርብ ያስረዳል። ተገቢ ያልሆነ ቅርርብ የሚባሉት እንዴት ያሉት እንደሆኑም ይዘረዝራል። የሃይማኖት ልዩነት እንዴት ሊታይና ሊመዘን እንደሚገባውና፣ ሃይማኖታቸውን ሰውረው ከሚቀርቡን አታላይ ሰዎች መጠንቀቅ እንደሚያስፈልግ ይጠቁማል።

ሁለተኛው ምዕራፍ ደግሞ የጋብቻ ነገር ሲነሣ ሃይማኖት ለምን መስፈርት እንደሚሆን፣ የሃይማኖትን ሥርዓት አፍርሶ ከማያምኑ ጋር መጋባት ሊያስከትል የሚችለውን መዘዝና ጉዳት ያብራራል። አክሎም ከማያምኑ ጋር ላለመጋባት መሥዋዕትነትን የሚጠይቅ ቢሆን እንኳን የተጠየቀውን መሥዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ እንድንሆን ያስጠነቅቃል።

ምዕራፍ ሦስት፣ አራት፣ አምስትና ስድስት እነዚህ ተከታታይ ምዕራፎች በዘመነ ሕገ ልቡና፣ በሕገ ኦሪት፣ በሕገ ወንጌልና በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ከማያምኑ ጋር መጋባት እንዴት እንደሚታይ ታሪኮችንና በየዘመኑ የተሠሩትን ሕግጋት በመጥቀስ ያስረዳሉ።

ከማያምኑ ጋር ስለመተጫጨትና ስለመጋባት ከምእመናንም ሆነ ከማያምኑ ወገኖች በኩል ልዩ ልዩ ጥያቄዎች መኖራቸው ይታመናል። ምዕራፍ ሰባት በተቻለ መጠን ሊነሡ የሚችሉ እነዚያን ጥያቄዎችን ነቅሶ በማንሣት ሃይማኖታዊ መልሳቸውን ያስቀምጣል።

ምዕራፍ ስምንት የመጽሐፉ የመጨረሻው ምዕራፍ እንደመሆኑ መጠን ደግሞ «ከማያምኑ ጋር» ስለሚኖረን ማኅበራዊ ኑሮ፣ ስለ ሰላምታ፣ አብሮ ስለመመገብና፣ ስለመሳሳሉት ሁሉ ግንዛቤ በማስጨበጥ ይደመድማል።

መልካም ንባብ!
አዘጋጁ



በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

## ምዕራፍ አንድ

### «አንዲት ሃይማኖት»

እውነተኛዪቱ ሃይማኖት አንዲት ናት። ነገር ግን ብዙ ሰዎች እውነተኛ ሃይማኖት አንዲት ብቻ መሆኗን ሲጠራጠሩ ይታያሉ። አንተስ? እውነተኛዪቱ ሃይማኖት አንዲት ናት ብሎ ማመን አርቆ አለመመልከት፣ ጠባብነት ወይም አላዋቂነት አይደለም።

አንዳንድ ሰዎች ሁሉም ሃይማኖት በየራሳቸው መንገድ መመዘን ስላለባቸው ሁሉም በየራሳቸው ዓይን ልክ ናቸው ይላሉ። ስለዚህ እውነተኛዋ ሃይማኖት አንዲት ብቻ ልትሆን አትችልም ከሚል ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል። ሌሎች ደግሞ እውነተኛ ሃይማኖት የምትባል የለችም። ሁሉም ሃይማኖቶች የየራሳቸው ችግርና ጉድለት አለባቸውና ሙሉ በሙሉ ትክክል የሆነና ያልታዛባ ሃይማኖት አይገኝም የሚሉም ቁጥራቸው ቀላል የሚባል አይደለም።

ይሁን እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል የሚያምንና የሚመራ ክርስቲያን የቅዱስ ጳውሎስን ትምህርት ይከተላል። ቅዱስ ጳውሎስ እውነተኛ ሃይማኖት አንዲት ብቻ መሆኗን አስረድቷል። እርሱ በማያሻማ መንገድ «አንዲት ሃይማኖት» ብሎ ሰብኳልና። (ኤፌ፬÷፬) እርሷም መንትያ፣ ቅጥያ፣ አምሳያም የሌላት ፍጽምት ናት። ሁሉም ሰው የራሱ የሆነ እምነት፣ አቋምና አመለካከት ሊኖረው ይችል ይሆናል። በፈጣሪ ዘንድ ተቀባይነት ያላት ሃይማኖት ግን አንዲት ናት። ብዙ መገለጫዎች ቢኖሩአትም ዋና መታወቂያዋ ፍቅር ነው።

የያዕቆብ ወንድም ሐዋርያው ይሁዳም እውነተኛ ሃይማኖት አንዲት ብቻ መሆኗንና እርሷም ለቅዱሳን ከእግዚአብሔር የተሰጠች እንጂ በምርምርና በሰው ጥበብ የተገኘች አለመሆኗን «ለቅዱሳን <u>አንድ ጊዜ</u> ፈጽሞ ስለተሰጠ ሃይማኖት» በማለት



www.ethiopianorthodox.org

አስረድቷል። (ይሁዳ ቁ፫) ከፈጣሪ የተሰጠች እንደመሆኗ መጠን ምንም ጉድለት የለባትም።

ሃይማኖት አንዲት መሆኗን መጽሐፍ ቅዱስ ነግሮናል። ይህን በማመን ሲጓዙ በሰዎች ሕሊና የሚፈጠሩ በርካታ ጥያቄዎች አሉ። ለምሳሌ፡- ሃይማኖት አንዲት ብቻ ከሆነች ሁሉም ሰው የየራሱን ‹‹እውነተኛዋ ሃይማኖት የኔ ናት!›› ማለቱ አልቀረም። ታዲያ እውነተኛዪቱ ሃይማኖት የቷ ናት? ከእርሷ ውጭ የሚኖሩ ሰዎች በሙሉ የወደፊት ዕጣ ፋንታ ምንድር ነው? እነዚያ ሁሉ ይጠየቃሉን? የሚኮነኑ ከሆኑ እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ ቸር ነው፤ እውነተኛ ፈራጅ ነው ለማለት አያስቸግርም ወይ? ስለ እውነተኛዪቱ ሃይማኖት ለማወቅና ለማመን ቀርቶ ለመስማት እንኳን ምንም ዕድል የሌላቸው ሰዎች በዓለም ሞልተው እንዳሉ እየታወቀ በአንዲት ሃይማኖት ስላልኖሩ ‹‹ይፈረድባቸዋል›› ማለት የማይመስል አይሆንም ወይ? ወዘተ ... (ዮሐ፫፥፲፰) የሚሉ እርስ በእርሳቸው የተቀጣጠሉ ጥያቄዎች እንደ ምንጭ ውኃ ከአእምሮ መፍለቅ ይጀምራሉ።

ይሁን እንጂ ይህ ሁሉ የጥያቄ ጋጋታ እውነተኛይቱ ሃይማኖት አንዲት መሆኗን አያስቀርም። ይህን ለመሰሉ ለሁሉም ጥያቄዎች በቂ ማብራሪያና መንፈሳዊ ምክንያቶች አሏቸው። ምክንያቶቹን እዚሁ ለማቅረብ የሐሳቡ መስፋት ብቻ ሳይሆን ርእሳችንም ይገድበናል። እግዚአብሔር ቢፈቅድ የእነዚህን ጥያቄዎች መልስ በሌላ መጽሐፍ እንመለስበት ይሆናል።

መልሳቸውን እስክናገኝም ቢሆን ጥያቄዎቹ ሃይማኖት አንዲት መሆኗን እንዳናምን የሚያደርጉን መሆን የለባቸውም። እውነተኛ ክርስቲያን ለጠየቀው ጥያቄ በወቅቱ መልስ ያላገኘ ሲመስለው እምነቱን የሚተው፣ አቋሙን የሚለዋውጥና ሁሉን ትቶ በራሱ አመለካከት የሚመራ ሳይሆን ይህን ለመሰለ የሕሊና ፈተና ሳይበገርና ከተጻፈው ሳያልፍ አምኖ የሚገኝ ነው። የተጻፈው ደግሞ ‹‹አንዲት ሃይማኖት›› የሚል ነው። (ኤፌ፬፥፬)





በቅዱስ መጽሐፍ የተገለጠችው ‹‹አንዲት ሃይማኖት›› ኦርቶዶክሳዊት የተዋሕዶ የክርስትና ሃይማኖት ናት። ይህን ለማረጋገጥ ከፈልግህ አንድ ብቸኛ መንገድ አለህ። እርሱም የመጨረሻ ምቹና ቀላሉ መንገድ ሲሆን እውነተኛዪቱ መንገድ አንዲት ብቻ መሆኗን አምኖ መቀበል ነው። ሃይማኖት ስጦታ ናት እንጂ በሰው ምርምር የሚደረስባት አይደለችምና። (ይሁዳ ቁ፫)

ኀሠሣን፣ ምርመርንና ፍለጋን አናወግዝም። ነገር ግን እውነተኛዋ ሃይማኖት በሰው ችሎታና ምርምር ሊደረስባት እንደማይችል እንናገራለን። የሰው ምርምር ቅንና በፈጣሪ ዘንድ ብቁ ሆኖ ከተገኘ ፈጣሪ የዚያን ሰው የልብ መሻት ምክንያት አድርጎ ራሱን ይገልጣል። ይህም የመፈለግና የምርምር በጎ ጎን ተደርጎ ይጠቀሳል።

አብርሃም አባታችን እውነተኛውን መንገድ ያገኘ ዘንድ ፈለገ። ምርምሩንም ቀጠለ። ይሁን እንጂ ከምርምሩ የደረሰበት እውነት ቢኖር ፈጣሪ እርሱ በሚፈልግበት መንገድ ወይም በምርምሩ ሊገኝ አለመቻሉን መረዳት ነበር። ስለዚህ በመጨረሻ ‹‹የፀሐይ አምላክ ተገልጠህ አነጋግረኝ!›› እያለ በትጋት በመጸለዩ ፈጣሪውን ለማነጋገር በቃ። ሃይማኖት ወደ ፈጣሪ የምታደርስ መንገድ ስትሆን እርሷም በአምላክ ፈቃድ የምትሰጥ እንጂ በመራቀቅና በምርምር የምትገኝ አለመሆኗን የአባታችን የአብርሃም ገድል ያስረዳናል።

ሰው ፈጣሪውን ለማግኘት መመራመሩ መፈለጉን ብቻ እንጂ ማመኑን ላያሳይ ይችላል። ምርምር ያለ እምነት ከመፈለግ ብቻ ሊመነጭ ይችላል። እንዲያውም በምርምር ፈጣሪን ለማግኘት ማሰብ በተመራማሪው ዘንድ ብዙ ጉድለቶች መኖራቸውን ይጠቁማል። አንደኛ የእምነት ጉድለትን፣ ሁለተኛ ግብዝነትንና በራስ ችሎታ መመካትን፣ የፈጣሪን ከሕሊና በላይ መሆኑን ያለመረዳት ችግርን፣ ሰይጣን ሃይማኖት እንዳትገኝ የሚያደርገውን ርብርብ ያለመመልከትን ወዘተ ችግሮች ሊያሳይ ይችላል።

በተለይ በዚህ ዘመን እውነተኛዋ ሃይማኖት በምርምር የምትገኝ ብትሆን እንኳን ከመገኘቷ ያለ መገኘት ዕድሏ በጣም የሰፋ ነው፡፡ የሰው ዕድሜ፣ ዕውቀትና አጠቃላይ ችሎታም ሃይማኖትን መርምሮ ወደ እውነተኛው መንገድ ለመድረስ በቂ አይደለም፡፡ ሃይማኖት እንደ ቁስ የሚታሠሥ ቢሆን ሰው ሃይማኖትን በማፈላለግ ዘመኑን ይፈጅ ነበር፡፡ ይህ ሲሆን ደግሞ ለፈጣሪው ምንም ዓይነት ምስጋናና ሥርዓተ አምልኮ ሳይፈጽም በሞት ይጠራ ነበር ማለት ነው፡፡

እውነተኛ ሃይማኖትን ለማግኘት በጥቂቱ እነዚህን መመዘኛዎች ተከትሎ ሰፊ ምርምር ማድረግን ይጠይቃል፡፡ ይኸውም ከልብ ንጽሕናና ቅንነት ጋር መሆን አለበት፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹ልበ ንጹሐን ብፁዓን ናቸው፡፡ እግዚአብሔርን ያዩታልና›› ስለሚል (ማቴ፭፥፰)

፩ኛ. የሃይማኖትንና አጠቃላይ ታሪኮችን በጠራ መንገድ

፪ኛ. መጽሐፍ ቅዱስን ከምሥጢሩ ጋር፣ የሌሎችንም ሃይማኖቶች መጻሕፍት

፫ኛ. ሃይማኖትን በተመለከተ ጥናታዊ ግኝቶችን፣

፬ኛ. በዘመናችን ሲፈጸሙ የሚታዩትን ከሰይጣን ማታለል የጸዱትን አምላካዊ ሥራዎችን፣ አምላካዊ ምስክሮችንና የመሳሰሉትን

ታዲያ ከተጠቀሱት ሰፋፊ አጀንዳዎች አንጻር በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የሃይማኖት ተቋማትን አንድ በአንድ የሰው ልጅ በግሉ አጥንቶ ወደ እውነቱ የመድረስ ዕድሉ ስንት ስንተኛ ነው? በቂና ያልተዛባ መረጃ የማግኘቱስ ዕድል?፣ የግለሰቡ የራሱ ነገሮችን የመመርመር ችሎታና ብቃትስ? የሚሉት ጥያቄዎች ሊመለሱ የማይችሉ ናቸው፡፡ እውነተኛዋ ሃይማኖት አንዲት ብቻ እና የአምላክ ስጦታ መሆኗን አምኖ መቀበል የበለጠ የተሻለ መንገድ የሆነው በእነዚህ ምክንያቶች ነው፡፡

በመጨረሻ ሰው በፈጣሪ ዘንድ የሚጸድቀው በሃይማኖቱ እንጂ በእውቀቱ አይደለም፡፡ መመርመር ዕውቀትን እንጂ





ሃይማኖትን አይገልጽም፡፡ ሃይማኖት ግን ዕውቀትን ያካትታል፡፡ የታወቀውን ትረዳዋለህ ያልታወቀውን በእምነት ታስተውለዋለህ፣ በእምነት ትጨብጠዋለህ፡፡ (ዕብ፲፩፥፩) ስትመራመር ብትሞት አላመንክም ልትባል ትችላለህ፡፡ ካመንክ በኋላ ግን ስትመራመር መኖር ትችላለህ፡፡ ‹‹በእምነት እንጂ በማየት አትመላለስ፡፡›› (፪ቆሮ፭፥፯-፯) ማለትም ዕድሜህን በመመራመር ብቻ አትፍጀው፡፡ አእምሮህንም ሰላምና እረፍት አትንፈገው፡፡

## የሃይማኖት ልዩነት

እንደየሁኔታው ልዩ ልዩ ሃይማኖቶችን ያለመጠን ከራስ ሃይማኖት አርቆና አቅርቦ ማየት በብዙ ሰዎች ዘንድ ያለ አመለካከት ነው፡፡ አንዳንድ ኦርቶዶክሳውያን ‹‹ከጥንትም ያሉ ሁለት ሃይማኖቶች ክርስትናና እስልምና ናቸው፡፡ መጤ ሃይማኖት አናውቅም፡፡›› በማለት ‹‹ከጴንጤ›› ይልቅ እስልምናን ቀረብ አድርገው ሲናገሩ ይሰማል፡፡ እንዲያውም ‹‹ከእስላም ጋር እየተጋባን ኖረናል›› አሁን ልዩነቱን ምን አመጣው? እስከ ማለት የሚደርሱም አሉ፡፡ ‹‹ቅዳሴና አዛኑን አጥር ቢለያቸው ፈጣሪ ከሰማይ አንድነት ሰማቸው›› እያሉ መዝፈን የተወለደውም ከዚህ ዓይነት የተሳሳተ አመለካከት ነው፡፡

ሌሎች ደግሞ ‹‹ከእስላምስ ጴንጤዎች ይሻሉናል ምንም ቢሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ያምናሉ›› እያሉ መናፍቃኑን በማቅረብ ሌሎቹን ያርቃሉ፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ለይቶ ማየት የሚያዳግታቸው በርካታ ሰዎች አሉ፡፡ ከሁለቱ የተመቻቸው ዘንድ ሄደው ያስቀድሳሉ፡፡ ሲጠየቁም ‹‹አንድ ናቸው ምን ችግር አለው?›› ይላሉ፡፡ እንደዚህ እንዲያስቡና ይህን አመለካከት አምነው እንዲቀበሉ ሆን ተብሎ የተቀመረ ነገር መኖሩን ለመጠርጠር ጊዜ የላቸውም፡፡ ‹‹እነርሱም እኛ እንደምናምነው በድንግል ማርያም ያምናሉ፣ ቅዳሴ አላቸው፣ ታቦት አላቸው፣ ወዘተ…›› ይላሉ፡፡ ብዙ ሰዎች መንፈሳዊ ዕውቀት እጅግ ስለሚጎድላቸው የሚያነጻጽሩትና የሚናገሩት በእነርሱ እውቀት ደረጃ ያለውን ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ እንዲህ ባሉ



www.ethiopianorthodox.org

ሰዎች ዘንድ ኦርቶዶክሳዊነትና ካቶሊካዊነት ልዩነት የላቸውም። እውነቱ ግን ከዚህ በጣም የተለየ ነው።

የተለያዩ የእምነት ተቋማትን የሚያመሳስላቸው መጠነኛ የሆነ የዶግማ፣ የቀኖናና የትውፊት ክፍል ይኖራል። ከዚህ ሁሉ ግን የሚሰፋው ልዩነታቸው ነው። የተለያዩ ባይሆኑ ኖሮ ጥንቱንም እንደ ሁለት የሃይማኖት ተቋም ባልታዩ ነበር።

የሁለት የእምነት ተቋሚት የልዩነታቸው መጠን የሚለካው በተለያዩበት ሐሳብ ጭብጥ እንጂ በሚለያዩበት ጽንሰ ሐሳብ ብዛት (ቁጥር) አይደለም። የእምነት ተቋሚት በአንድ ዶግማዊ ይዘት ባለው ሃይማኖታዊ ፅንሰ ሐሳብ ብቻ እንኳን ቢለያዩ ልዩነቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊና ሃይማኖታዊ እስከሆነ ድረስ የጎላ ነው።

ሁለት የሃይማኖት ተቋማት ብዙ መመሳሰል ስላላቸውም አንድ ናቸው ሊባል አይቻልም። እውተኛዋ ሃይማኖት ከሌሎች ሃይማኖቶች ያላት ልዩነት እውነት ከሐሰት እንዳላት ዓይነት ልዩነት ነው።

በሃይማኖቶች መካከል ስላለው ልዩነት ስንናገር እንደምናይበት አቅጣጫ አቋማችን ሊለያይ ይችላል። የተለያዩ ቢመስሉም አንድ የሆኑ አንድ ሲመስሉ ደግሞ እጅግ የተለያዩ የሃይማኖት ተቋማት አሉ። ክርስቲያን ሆነህ እንደ ቅዱስ ጳውሎስ በ‹‹አንዲት›› ሃይማኖት የምታምን ከሆነ ከእርሷ ውጭ ያሉ በሙሉ በስሕተት ጎዳናቸው አንድ ሆነው ይታዩሃል፤ ምንም የተለያዩና እጅግ የተራራቁ ቢመስሉም በሐሰትነት አንድ መሆናቸውን ትረዳለህና። የመጻሕፍቶቻቸውና የዶግማዎቻቸው መለያየት እንደልዩነት አትቆጥረውም። ክርስቲያን እስከሆንክ ድረስ አንተ እንደ ‹‹ፍጥረታዊ›› (ሥጋዊ) ሰው ሳይሆን እንደ መንፈሳዊ ሰው መመልከት ጀምረሃልና። (፩ቆሮ፪፥፲፬)

ከአንዲቷ ሃይማኖት ውጭ ያሉ ሁሉ ምንም የተለያዩ ቢመስሉም አንድ ናቸው እንዳልን ሁሉ በእውነተኛዋና በአንዲቷ ሃይማኖት ጥላ ውስጥ ያሉ እኅት አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ ምንም የየራሳቸው ሀገራዊ፣ ባህላዊ ትውፊትና ቀኖና





ቢያለያያቸውም በመሠረተ ሃይማኖት አንድ እስከሆኑ ድረስ አንድነታቸው የጸና ነው።

አንዳንድ ሰዎች የሃይማኖትን መለያየት ከመግባባትና በሰላም ከመኖር አንጻር ብቻ ስለሚመለከቱት በየሃይማኖቱ ያለው የዶግማ ልዩነት አይታያቸውም። ሁሉን እረስታችሁ ከማንም ጋር ቢሆን ለምን የራሳችሁን አቋም ሳትይዙ ተስማምታችሁ አትኖሩም ይላሉ። ይህን ሲሉ እምነትና የየራስ አቋም ከሌለ ማንነት ሊኖር እንደማይችል እንኳን አይገነዘቡም። ሰው ያለ ሃይማኖትና ያለ አቋም እንዴት ይኖራል? አቋም ካለ ደግሞ ልዩነት መኖሩ ግድ ነው።

እንደዚሁም በተለያየ ሃይማኖት እየኖሩ የተፋቀሩ ወንድና ሴት ፍቅራቸው ብቻ እንጂ እውነት የትም ትኑር የት ጉዳያቸው አይደለም። ምናልባትም ሃይማኖት የሚባል ነገር ባይኖር ደስ ሳይላቸው አይቀርም። የሚያዩት ከግል ስሜታቸው አንጻር ብቻ ነውና። ሃይማኖት የሚያበረክተው ሀገራዊ፣ ሥነ ምግባራዊ፣ አካላዊ፣ ሕሊናዊ፣ ዘላለማዊ፣ በአጠቃላይ ቁሳዊና መንፈሳዊ ፋይዳ ከቶ አይታያቸውም።

በተመሳሳይ መንገድ በየዘመኑ የተነሡና የሚነሡ የሀገር መሪዎችም ስለ እውነተኛ ሃይማኖት ግድ አይኖራቸውም። እነርሱን ሌት ተቀን የሚስጨንቃቸው ‹‹እንዴት አድርጌ ለብዙ ዘመን በሥልጣን ላይ መቆየት እችላለሁ›› የሚለው የገገርዎች ሐሳብ ብቻ ነው። ስለዚህ እውነትም ሆነ ሐሰት ይህን ለማድረግ የሚያስችላቸውን መንገድ እያበረታቱ ኖረዋል፤ ይኖራሉም።

በመሆኑም ስለእውነተኛ መንገድ ተጨንቃና ተጠባ ማስተማር ያለባት እውነተኛዪቱ ቤተ ክርስቲያን ናት። ሃይማኖትን በተመለከተ በእውነተኛ መንገድ ላይ ቆሞ ለመገኘት ሌላው ኃላፊነት የሚወድቀው በእያንዳንዱ ግለሰብእ ላይ ነው። ስለአንተ በእውነት መንገድ መሰማራት ሌላው ሰው እንዲጨነቅልህ መናፈቅ ሞኝነት ነው።

በየሃይማኖቱ ያለውን የጽንሰ ሐሳብ ልዩነት በጥልቀት ማየት ያልቻሉ አንዳንድ የዋህ ምእመናን በግላቸው አመለካከት እየተጓዙ እነርሱ ከሚከተሉት ሃይማኖት ጋር ተቀራራቢ የአምልኮ ሥርዓት የሚያካሂደውን የሌላ እምነት ተቋም አባል ማግባት የራሳቸውን ሃይማኖት ተከታይ እንደማግባት ያህል ይቆጥሩታል። ይህ አመለካከት በመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት ሲመዘን ፍጹም ስሕተት ነው።

ለምሳሌ፡- አንዲት ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን ሴት ሙስሊም ወንድ ማግባቷ እና ተመሳሳይ ሴት የካቶሊክ ሃይማኖት ተከታይ ወንድ ማግባቷ በብዙዎች ዘንድ በእኩል ዓይን አይታይም። ካቶሊኩን ያገባችዋ ሴት ሙስሊም ካገባችዋ የተሻለ ነገር እንዳደረገች እንጂ ስሕተት እንደሠራች የማይቆጥሩ ሰዎች አሉ። ይህም ቀደም ሲል እንደተገለጠው የካቶሊክ ሃይማኖት ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ብዙ ልዩነት የላትም ከሚል የተሳሳተ ግንዛቤ የመነጨ ነው።

እንደ ክርስትና እምነት የአንድ ሃይማኖት እውነተኛነት የሚወሰነው በመጽሐፍ ቅዱስ የዶግማ አስተምህሮ መሠረት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የእውነተኛዪቱ ሃይማኖት ገጽታዋ ወይም ሙሉ መልኳ ይታያል። ሌሎች ግን በቅዱስ መጽሐፍ ሲመዘኑ ብዙ ነገር አጉድለው ወይም የሌለ ነገር ጨምረው ይገኛሉ። ክርስቲያኖች እንደመሆናችን መጠንና መጽሐፍ ቅዱስን መመዘኛ አድርገን እስከተነሣን ድረስ አንድ ሃይማኖት በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተዛባ ትምህርት ላይ የተመሠረተ ዶግማ ከሌለው እውነተኛ ሃይማኖት ሊሆን አይችልም። መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር የተገኘ የአምላክ ቃል ነውና። የክርስትና ሃይማኖት መሠረቱ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

አንድ ሃይማኖት ባልተዛባ መንገድ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተና እንከን የማይወጣለት ሃይማኖታዊ ትምህርቶችን ይዞ ከተገኘ አስተዳደራዊ ችግሮች ቢኖሩበት፣ ዘመናዊና የሠለጠነ አሠራርን ባይከተል ወይም በአባላቶቹ ዘንድ የስነ ምግባር ችግር





ጎልቶ ቢታይም ሃይማኖቱ ልክ አይደለም የሚል ድምዳሜ ላይ መድረስ አይቻልም። የሃይማኖቱ መሠረታዊ መመሪያ ከግለሰቦች የስነ ምግባር ጉድለት ጋር ሊያያዝ አይችልምና።

በግለሰቦች የስነ ምግባር ጉድለት የተነሣ የሚፈጠር እንቅፋትና የሚያስነቅፍ ነገር በእውነተኛዋ ሃይማኖት ዘንድ ባይኖር ማንም የሚመኘው ነገር ነው። ይሁን እንጂ ይህ ዓይነቱ መሰናክል ግለሰባዊ ስለሆነ የሃይማኖቱ ደረጃ ሊመዘንበት አይችልም። ከዚህም በተጨማሪ እንዲህ ዓይነቱ ሥነ ምግባራዊ ችግር በየሃይማኖት ተቋማቱ ሁሉ የሚታይ ችግር ነው እንጂ የእውነተኛዪቱ ቤተ ክርስቲያን ችግር ብቻ አይደለም።

ማንኛውም ሃይማኖት በርካታ ዓይነት ሰዎችን የሚያቅፍ ተቋም እንደመሆኑ መጠን እንዲህ ዓይነት ምግባር የጎደላቸው ሰዎች በየሃይማኖቱ ውስጥ መገኘታቸው አያስደንቅም። አላዋቂ ሰው የየሃይማኖቱን ዶግማዊ ይዘትና መሠረታዊ መመሪያዎችን ሳይረዳና ሳይመዝን ሃይማኖቶችን በተከታዮቻቸው ብዛት፣ በሥነ ምግባራቸው ደረጃና በአስተዳደር ብቃታቸው ወዘተ ብቻ ልክ ናቸው አይደሉም ወደሚል መደምደሚያ ላይ ይደርሳል። አስተዋይ ሰው ግን ይህ ሃይማኖት እውነተኛ ነው ወይስ አይደለም ከማለቱ በፊት የሃይማኖቱን መሠረታዊ ጭብጥ ተጨባጭ ማስረጃዎችን በመያዝ በተገቢው መንገድ ይመረምራል። በዚህ መንገድ ለሚመለከት ሰው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደጻፈልን እውነተኛ ሃይማኖት ‹‹አንዲት›› ብቻ ናት። (ኤፌ፬፥፬)

ሃይማኖት አንዲት መሆኗን ያመነ ሰው ከእርሷ ውጭ ያሉ ሁሉ የተሳሳቱ ናቸው ለማለት አያቅማማም። እውነት ናት ብለህ ለተቀበልካት ሃይማኖት በሰው ሰውኛ እይታ ቅርብ መስሎ የታየህን ሁሉ ‹‹አንድ ናቸው›› የምትል ከሆነ በእውነተኛዪቱ ሃይማኖት አንዲትነት ማመንህ ያጠራጥራል። ሃይማኖት አንዲት እስከሆነች ድረስ ሁሉም ሃይማኖቶች እውነተኞች ሊሆኑ አይችሉም። በእርግጠኝነት ‹‹አንዲት›› እውነተኛ ሃይማኖት

እስካለች ድረስ ጨፍልቆ ሁሉም ሃይማኖቶች ስሕተት ናቸው ለማለት አይቻልም። ቢያንስ አንድ እርሷን ለይቶ መናገር ይገባልና።

በየሃይማኖቱ ያለውን ልዩነት ሰዎች የፈጠሩትና ልዩነት የማይባል መስሎ ሊታይህ ይችላል። ዋናው በየሃይማኖቱ ልዩነት መኖሩን ማመንህ ነው። ግለሰቦች ለገዛ ጥቅማቸው ሲሉ ልዩነቱን ፈጠሩት ብሎ ማሰብህ ሰዎች ከዚህም የበለጠ ሊያደርጉ ይችላሉና ሐሳብህ መጠነኛ እውነትነት ይኖረዋል። ልዩነቱን ሰዎችም ፈጠሩት ወይም ሰይጣን ከእውነተኛዋ ‹‹ሃይማኖት ተሳስተህ›› ብትገኝ ጥፋተኛ ነህ። (፩ጢሞ፮፥፲) አንተ ‹‹በሃይማኖትህ ጤናማ›› መሆን ይጠበቅብሃልና። (ቲቶ፩፥፲፫-፲፬)

ጋብቻን በተመለከተ ልዩ ልዩ ሃይማኖቶች የተለያየ አቋም አላቸው። ይህንን አጠቃላይ ሁኔታ ማወቅ ለምእመናን ይረዳቸዋል። በሃይማኖት ከማይመስሏቸው ጋር መጋባትን የሚፈቅዱ ወይም የሚደግፉና የማይደግፉ የሃይማኖት ተቋማት በዘመናዊው ዓለም በሦስት ወገን ይታያሉ።

አንደኛው ወገን ሃይማኖትን እየመረጡ አባላቶቻችን ከዚህ እና ከዚህ ሃይማኖት ጋር መጋባት ይችላሉ የሚሉ ናቸው። እነዚህ በእንግሊዝኛው ‹‹Inclusive Faith Group - ኢንክሉሲቭ ፌይዝ ግሩፕ›› ይባላሉ።

ሌሎቹ ደግሞ ምንም ሳይመርጡ የሁሉንም እምነት ዜጋ ተቀብለው ጋብቻ የሚፈጽሙ ሲሆኑ ‹‹Pluralistic Faith Group - ፕሉራሊስቲክ ፌይዝ ግሩፕ›› ይባላሉ።

ሦስተኛ ወገኖች ደግሞ ከራሳቸው ሃይማኖት ተከታይ ውጭ መጋባትን የማይደግፉ ናቸው። እነዚህም በእንግሊዛኛው ‹‹Exclusive Faith Group - ኤክስክሉሲቭ ፌይዝ ግሩፕ›› የሚባሉት ናቸው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት በዚህ ውስጥ ልትጠቀስ ትችላለች።

የሒንዱ ሃይማኖት አባላቶቹ በሃይማኖት ከማይመስላቸው ጋር ቢጋቡ አይቃወምም። የእስልምና ሃይማኖት አባላቶቹ





ከክርስቲያን ጋር መጋባታቸውን ይፈቅዳል። ይህ መብት የተሰጠው ለወንዶች ብቻ ነው። እንዲያውም ወንዶች ሙስሊሞች ክርስቲያን ሴትን እንዲያገቡ ይበረታታሉ። ስለዚህ የአንዳንድ ሃይማኖት ተከታዮች የማይመስሏቸውን ላለማግባት ሊጠነቀቁ ይቅርና ሆን ብለው ክርስቲያኖችን ለማግባት የሚጣደፉበት ሁኔታ መኖሩን ማስተዋል ያስፈልጋል። በቅዱስ መጽሐፍ እንደተጻፈው አህዛባዊው ሴኬም እስራኤላዊቷን ዲናን ለጋብቻ መጠየቁ ምን ያስደንቃል? (ዘፍ፴፬፥፩-፴፩)

ይገርማችኋል! ሃይማኖትን ሰብኮና አስረድቶ ያላመነውን በማሳመን ፋንታ ሌላውን በጥቅም በመደለል፣ በኃይል በማስገደድ፣ ወይም ቀጥተኛና ግልጽ ያልሆነ ልዩ ልዩ ተፅዕኖ በማሳደር እያሳመኑ የአባላቶቻቸውን ቁጥር ለማብዛት አጀንዳ ቀርጸው የሚያራምዱ የእምነት ተቋማትም አሉ።

ለምሳሌ፡- በኅዳር ወር በናይጀሪያ ከተማ ‹‹የአፍሪካ ሙስሊሞች ጉባኤ›› በሚል ርእስ በተደረገው የእስላም ምሁራን ስብሰባ አፍሪካን ሙሉ በሙሉ በማስለም ላይ ያተኮረ ነበር። ለዚህም እንዲረዳ ከተቀረጹት አምስት ማስፈጸሚያ ዘዴዎች ‹‹ስትራቴጂስ›› መካከል ሙስሊም ወንዶች ክርስቲያን ሴቶችን በጋብቻ ገመድ ካሰሩ በኋላ ሃይማኖታቸውን እንዲቀበሉ ማድረግንም ይጨምራል።

ይህን ሐሳብ ሔኖክ ጸጋዬ የተባሉ ግለሰብእ በጥናት ጽሑፋቸው ጠቅሰዉታል። ሙሉ ሐሳቡን በቀጣዩ አንቀጽ እንዲህ ተመዝግቧል።

> "The fourth groups are the ordinary people in Islam. **People in this group are encouraged to marry Christian women as much as possible.** This by itself is Islamize Christians. Ethiopian Orthodox Christians are under focus in this effort as Orthodox women who are weak in their faith are bribed to change their faith for the sake of marriage. This strategy is purposely carried out, as there are many unmarried women both

in the Orthodox and Evangelical Christian circles in Ethiopia due to the Biblical teaching on marriage. Such kind of approach serves to increase the Muslim population both now and in the future." **(The Growth and Influence of Islam In Ethiopia from 1989 to 2000 Date: May 27, 2002)**

‹‹አራተኛው ምድቦች ተራዎቹ ሙስሊሞች (በአማኝነት ደረጃ ብቻ ያሉ ሙስሊም ኅብረተሰብእ) ናቸው። በዚህ ምድብ ውስጥ የሚገኙ ሙስሊሞች በተቻለ መጠን ክርስቲያን ሴቶችን እንዲያገቡ ይበረታታሉ። ይህ በራሱ ክርስቲያኖችን ማስለሚያ መንገድ ነው። ደካሞች ሴቶች በጋብቻ ምክንያት ሃይማኖታቸውን ለመቀየር በቀላሉ የሚታለሉ እንደመሆናቸው መጠን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስቲያን ሴቶች ለዚህ ዋና ዒላማ ናቸው። ይህ ሆን ተብሎ የሚከናወን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጋብቻ ከሚያስተምረው ትምህርት የተነሣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስና በወንጌላውያን ክርስቲያኖች ዘንድ በርካታ ያላገቡ ሴቶች እንደ መኖራቸው መጠን እንዲህ ያለው አካሄድ አሁንም ሆነ ወደፊት እስላሞች ቁጥራቸው እንዲጨምር ይረዳቸዋል።›› **(The Growth and Influence of Islam In Ethiopia from 1989 to 2000 Date: May 27, 2002)**

## ሃይማኖትን ደብቆ መቅረብ

የክርስትና ሃይማኖት ከማያምኑ ጋር ስለሚፈጸም የጋብቻ ትሥሥርን አስመልክቶ ያላት አቋም ግልጽ ነው። ከላይ እንደተገለጠው ሃይማኖታቸውን በጋብቻ ማስፋፋት የሚመኙ አካላት ልዩ ልዩ ዘዴ ሊጠቀሙ ይችላሉ።

፩ኛ. ያመኑ መስሎ መቅረብ፣





፪ኛ. እንጋባ እንጂ ወደፊት አምናለሁ እያሉ ተስፋ እየሰጡ መቅረብ ወይም

፫ኛ. ማንነትን በመሰወር መቅረብ የተለመዱ ናቸው።

ይህም የተኩላና የክፉ አዳኝ ጠባይ ስለሆነ ሃይማኖታቸው በማጭበርበር እንጂ በእውነት ላይ አለመመሥረቱን ለማስረዳት እንደ አንድ ምስክር ሊጠቀስ ይችላል።

ሙሐመዳውያን፣ መናፍቃን፣ ከሀዲያንና የማያምኑ ሰዎች ሁሉ ከምእመናን ወገን ለጋብቻ የሚፈልጉት ሰው ሲኖር በሃይማኖታቸው ምክንያት ብቻ ተቀባይነት እንደሚያጡ ስለሚያውቁ ማንነታቸውን ደብቀው የሚጠጉበት አጋጣሚ ብዙ መሆኑን ክርስቲያኖች ማወቅ አለባቸው። በዚህ ዓይነት የሸፍጥ አካሄድ ብዙ ምእመናን ለግራ መጋባትና ለችግር ተጋልጠዋል።

ለበርካታ ዓመታት ተፋቅረው የኖሩ ጥንዶች በስተመጨረሻ አንዳቸው ሌላኛውን ‹‹ሳንቀራረብ ከወዲሁ እንዳትሸሺኝ (እንዳትሸሸኝ) ብዬ ነው እንጂ እኔኮ እስላም ነኝ›› ከፊሎች ደግሞ ‹‹ፕሮቴስታንት ነኝ›› ሌሎች ‹‹እኔኮ የይሖዋ ምስክር ነኝ›› ሲሉ ተገኝተዋል። ይህን በተመለከተ የግለሰብእ ሕይወት ብዙ ውስብስባ ተዛማጅ ችግሮች ያሉበት ሆኖ ነው እንጂ ታሪካቸውን ያጫወቱንን የብዙዎችን ታሪክ ልናወሳላችሁ እንችል ነበር።

የክርስቲያኖች በሃይማኖታቸው ልዝብ ሆኖ መኖር የዚህ ዓይነት ድብቅ ጉዞ ለሚጓዙ ኢአማንያን ምቹ ሁኔታ ይፈጥርላቸዋል። ክርስቲያኖቹ ጠንካራ አቋም ሲኖራቸው ግን የኢአማንያኑ ሥውር አካሄድ አንድ ቦታ ሳይገለጥ አይቀርም። በቀላል ምሳሌ ለማስረዳት ራሱ ክር የማያስር ሰው ሌላውን ‹‹ለምን ክር አታስርም? ክርስቲያን አይደለህም እንዴ?›› ለማለት እንዴት ይችላል?

በተጨማሪም ራሱ ቤተ ክርስቲያን የማይሄድና ሲያጋጥመው እንኳን ጣቶቹን አመሳቅሎ ለመሳለም እጁን የማያንቀሳቅስ፣ ራሱንም ዝቅ የማያደርግ ሰው ሌላውን ሰው ‹‹ቤተ ክርስቲያን እንሂድ፤ እንሳለም፤ እንጸልይ።›› ለማለት እንዴት ይችላል? ወይም



www.ethiopianorthodox.org

ለምን አልተሳለምክም ክርስቲያን አይደለህም እንዴ ለማለት እንደሚያዳግተው ግልጽ ነው። ራሱ የማይጾም ሰው አብሮት ያለውን ሰው አትጾምም እንዴ? ይለው ዘንድ እንዴት ይችላል?

አንድ ሰው ቢያንስ ይህን ካላደረገና እንደአስፈላጊነቱ ካልጠየቀ ደግሞ አጠገቡ ያለውን ሰው የሃይማኖት አቋም ለመገምገም አይችልም። ስለዚህ የጋብቻ አጋራችንንም ሆነ ሌላ ማንኛውም በዙሪያችን ያለውን ሰው ሃይማኖታዊ አቋም ለመረዳት የምንችለው ራሳችን በሃይማኖታችን የተስተካከለ አቋም ይዘን ስንገኝ ብቻ ነው። እኛ ጥብቅ አቋምና ጥሩ ክትትል ካለን ስለ ሃይማኖቱ ሊደብቀን ያሰበ ወዳጅ ቢኖረን እንኳ ምቹ ሁኔታ እናሳጣዋለን። በዚህ ጊዜ እምነቱን መደበቅ ስለማይችል በጊዜ መውሰድ ያለብንን እርምጃ አውቀን አቀራረባችንን መልክ ማስያዝ እንችላለን። አንዳንድ ጊዜ እንዲህ ጠንካራ አቋም ይዘንም የሌላውን ሰው ይዘት ለመረዳት የማንችልበት ጊዜ መኖሩንም አንዘንጋ።

ክርስቲያኖች እንኳን ጉልህ የሃይማኖት ልዩነትን እየተመለከቱ ይቅርና በሃይማኖት አንድ ከሚሆኑት ሰው ጋር እንኳን ሃይማኖታቸውን በተመለከተ ያላቸው አቋም (ዝንባሌ፣ ፍላጎት፣ ትኩረት፣ ፍቅር፣ ክትትልና ጥንካሬ) ከፍተኛ ልዩነት ካለው ምንም የአቋም ማስተካከያ ሳያደርጉ ባሉበት ሁኔታ ጋብቻን ማሰባቸው ለቀጣይ ኑሯቸው በጣም አደገኛ ነው።

በአንድ ሃይማኖት ውስጥ የሚኖሩ ጥንዶች ከጋብቻቸው በፊት አስቀድመው በመካከላቸው ያለውን የመንፈሳዊነት ዝንባሌ ልዩነት ማጥበብ ይኖርባቸዋል። ሃይማኖታቸው አንድ ቢሆንም በመንፈሳዊ ጥንካሬ ከፍተኛ ልዩነት ሲኖር የሚከሠት ችግር በተለያየ ሃይማኖት እየኖሩ በተጋቡ ሰዎች መኻል ከሚፈጠር ችግር ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው። (ትዳርና ተላጽቆ ምዕ፭)

## ‹‹ከማያምኑ ጋር››

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ከማያምኑ ጋር በማያመች አካሄድ አትጠመዱ›› በተጨማሪም ‹‹የሚያምን ከማያምን ጋር





ምን ክፍል አለው?›› በማለት ደጋግሞ ‹‹የማያምኑ›› ሲል የጠቀሳቸው አካላት አሉ። ሌሎች ነጥቦች ከማየት የሚቀድመው እነዚህ ‹‹የማያምኑ›› የሚባሉት እነማን ናቸው የሚለውን ጥያቄ መመለስ ነው። (፪ቆሮ፮÷፲፬ (፲፭))

በመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ መሠረት ‹‹የሚያምኑ›› (ክርስቲያኖች) የሚባሉት መጽሐፍ ቅዱስን ከነምሥጢሩ ተቀብለው በኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት አምነው በ‹‹አንዲት›› በቀናች ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖት ጥላ ሥር የሚኖሩ ሁሉ ናቸው። ለምሳሌ፡- በዓለም ላይ የሚገኙት አምስቱ እኅት አብያተ ክርስቲያናት ምንም እንኳን የታሪክ፣ የባህል፣ የቀኖና ልዩነት ቢታይባቸውም ዶግማዊ በሆነ ትምህርተ ሃይማኖት አንድ በመሆናቸው። በአንዲት እውነተኛ ሃይማኖት ጥላ ውስጥ ናቸው። ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹የሚያምኑ›› በማለት የሚገልጻቸው እነዚህን ሁሉ ነው። ተከታዮቿ በቁጥር ጥቂት ቢመስሉም እውነተኛዋ ‹‹አንዲት ሃይማኖት›› ዓለም አቀፋዊት ናት።

ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ከማያምኑ ጋር››፤ ባለ ጊዜ ‹‹የማያምኑ›› በማለት የጠራቸው ከ‹‹አንዲት›› ሃይማኖት ውጭ የሚኖሩትን ሁሉ ነው። መናፍቃን ምንም እንኳን ራሳቸውን በክርስቲያን ስም ቢጠሩም በመጽሐፍ ቅዱስ ሲመዘኑ ሙሉ ሆነው ስለማይገኙ ሁሉም የሚመደቡት ከኢአማንያን ጎራ ነው። በሐዋርያት ዘመንና ከዚያም አስቀድሞ በዘመነ ክርስቶስ በክርስትና ስም የሚነግዱና የእግዚአብሔርን ቃል ‹‹የሚሸቃቅጡ›› ነበሩ። (፪ቆሮ፪÷፲፯) እነርሱም በጌታችንና በሐዋርያት ዘንድ ልዩ ልዩ መጠሪያ ነበራቸው። ‹‹ከእግዚአብሔር ያልሆኑ›› አጽራረ ቤተ ክርስቲያን ‹‹ጸራዊያን›› ወይም ‹‹ጠላት፣ ጠላቶች››፣ ‹‹ቢፅ ሐሳዊያን›› ወይም ‹‹ሐሰተኛ ወንድሞች›› እየተባሉ ይጠሩ ነበር። (ማቴ፲፫÷፳፰፤ ፪ጴጥ፪÷፩-፪) እነዚህ ሁሉ በቅዱስ መጽሐፍ አስተምህሮ መሠረት ‹‹የማያምኑ›› ናቸው። እውነተኛዪቱ ሃይማኖት አንዲት መሆኗ ይታወቃልና።

በዘመናችን የመናፍቃንን ዓይነትና የአምልኮ ባዕድ ብዛት ለመቁጠር የሚያታክት ስለሆነ በጅምላ አህዛብ፣ አረማውያን፣ መናፍቃን፣ ከሃድያን፣ መምለክያነ ጣዖታት (ጣዖታትን የሚያመልኩ)፣ በጠንቋይ፣ በጥንቆላና በልዩ ልዩ ዛር፣ ድግምትና ሟርት የሚያምኑ እያሉ ካልሆነ በቀር እያንዳንዱን ክፍልፋይ በስም መዘርዘር ያዳግታል። ስለዚህ ‹‹የማያምኑ›› የሚባሉት ሃይማኖቷን፣ ሕጎንና ሥርዓቷን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ከመሠረተች ከ‹‹አንዲት›› የቀናች ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖት ውጭ የሚኖሩና በዚህ አንቀጽ ሥር የተዘረዘሩ የተዛቡ የአምልኮ መንገዶችን የሚከተሉ ሁሉ ናቸው።

## ‹‹የማይመች አካሄድ››

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ›› በማለት ከማያምኑ ጋር አብሮ መኖርን በተመለከተ ለክርስቲያኖች ሁሉ መመሪያ የሚሆን መልእክት ጽፎ አኑሯል። በተለይ ‹‹በማይመች›› የሚለው ቃል ክርስቲያኖች ከማያምኑ ጋር ሊሄዱበት የማይገባ ዘርፍ መኖሩን ይጠቁማል። (፪ቆሮ፮፥፲፬)

‹‹አካሄድ›› በመጽሐፍ ቅዱስ ጠቅላላ የሰው ልጆችን ኑሮ የሚያመለክት ቃል ነው። ሄኖክ ‹‹አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ።›› ሲል ኑሮውን ማለት እንደሆነ ይታወቃልና። (ዘፍ፭፥፳፬) ‹‹በማያመች አካሄድ›› ማለት ደግሞ በማያመች አኗኗር ማለት ነው።

ክርስቲያኖች ከማያምኑ ጋር የሚመቻቸውና የማይመቻቸው አካሄድ አለ። የማይመቻቸው የማያምኑ ሰዎች ሥርዓተ አምልኮ፣ ከማያምኑ ጋር ጸሎት፣ መዝሙር፣ ስብከት፣ አብሮ መብላትና መጠጣት፣ ጋብቻ ወዘተ ሲሆኑ የሚመቻቸው ደግሞ በአጠቃላይ በኀዘንና በደስታ ያለው መረዳዳትና ማኅበራዊ ኑሮ ሁሉ ነው።

ከማያምኑ ጋር በገበያ፣ በትምህርትና በሥራ፣ በደስታና በኀዘን ተባብሮ መኖር መንፈሳዊነትን ያጎለብታል እንጂ አይጎዳም። የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ትምህርትም ከዚህ ውጭ





አይደለም። ከኢአማንያን ጋር ማኅበራዊ ኑሮ እንዳለ ሆኖ ጋብቻ ክልክል የሆነበት ምክንያት የጋብቻ ምሥጢርና አንድነት ከሌሎች ማኅበራዊ ግኙነቶች ሁሉ በላይ ጥልቅና ውሳጣዊ ስለሆነ ነው።

# ምዕራፍ ሁለት

## ለጋብቻ ሃይማኖት መሰፈርት ይሆናል?

ማንኛውም ሰው ለማግባት ሲፈልግ ከኑሮ አቻው የሚፈልገው ነገር ይኖራል። ይህንንም የሚሻውን ነገር በእርሱ ዘንድ እንዳለው ትልቅነትና ትንሽነት ወይም እርሱ ለዚያ ነገር በሚሰጠው ግምት መጠን እንደ መስፈር አድርጎ በቅደም ተከተል ያስቀምጠዋል። ሃይማኖትን እንደ ቀዳሚ መስፈርት የሚያስቀምጡ በርካቶች ናቸው።

ጥቂቶች ግን ለሃይማኖት ከሚሰጡት ዝቅተኛ ግምት የተነሣ ሲያገቡ ሲያስቡ ስለሃይማኖት አያስቡም። እንኳን እነርሱ ሊያስቡት ሌሎች ሰዎች ሃይማኖትን ለጋብቻ ቅድመ ሁኔታ አድርገው ሲሰብኩ አይዋጥላቸውም። ይሁን እንጂ የሃይማኖት አንድነት በተጋቢዎች መኻል እንደ መስፈርትና ቅድመ ሁኔታ መቀመጥ ይኖርበታል።

በአፍላ ፍቅር ላይ ያሉ ጥንዶች ይህ ዓይነቱ ሐሳብ የፍቅራቸው ቀበኛ መስሎ ላይዋጥላቸው ይችላል። ጥንዶቹ ውሎ አድሮ ሊደበዝዝ የሚችለው አፍላ ፍቅራቸው እንጂ በሃይማኖት አንድ የመሆናቸው ምሥጢርና የሚያስገኝላቸው ጥቅም ቶሎ ግልጽ አይሆንላቸውም። እያደር ግን በችግሩ ወላፈን ሲገረፉ በቀደመ አቋማቸው መጸጸታቸውና በጋብቻ መኻል ሃይማኖትን መስፈርት አድርጎ የማስቀመጥን ጠቀሜታ መረዳታቸው አይቀርም።

ለጋብቻ የሚፈላለጉ ወንድና ሴት ሁለቱም የአንድ ሃይማኖት ተከታይ መሆን ይኖርባቸዋል። ሐዋርያው ‹‹ተፈጥሮ እንኳን አያስተምራችሁምን?›› እንዳለ ተፈጥሮ ብዙ ነገር ሊያስተምረን ይችላል። ሰዎች ብዙ ሕዋሳት ቢኖራቸውም ራሳቸው ግን አንድ ነው። ይህም ማለት የሚያዛቸው፣ የሚቆጣጠራቸውና የሚገዛቸው አካል አንድ ነው።





ሕዋሳት በአንድ ራስ መተዳደራቸው መልካም ነገር ነው። ምክንያቱም ለእያንዳንዱ ሕዋሳት የየራሳቸው ራስ ወይም አእምሮ ቢኖራቸው ትልቅ ችግር ሊፈጠር ይችል ነበር። ለሁለት የአንድ ሰው እግሮች ሁለት የየራሳቸው ራስ ቢኖራቸው ምን ይከሠት ነበር? አንዱ ራስ አንዱን እግር ወደ ፊት እንዲሄድ ቢያዘው ሌላኛው ራስ ደግሞ አንዱን እግር ወደ ኋላ እንዲሄድ ቢያዘው መሄድ አይታወቅም ነበር። ቅዱስ ወንጌል ‹‹ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም›› ያለው ይህን ለመሰለ ሁሉ ይሠራል። (ማቴ፮÷፳፬)

እንደዚሁም ባልና ሚስትም ‹‹አንድ ሥጋ›› ናቸውና እንደ ሁለት የሰውነት ክፍል ሊቆጠሩ ይችላሉ። የሰውነት ክፍሎች ሁሉ በአንድ ራስ እንደሚመሩ ባልና ሚስትም የሚመሩበት ሕግ አንድ መሆን አለበት። ማለትም የሚገዙበት ሃይማኖት አንድ መሆን አለበት። የተለያየ ሃይማኖት ይዞ መጋባት ለሁለት ጌቶች እንደ መገዛት ነው።

በተለያየ ሃይማኖት የሚመሩ ባልና ሚስት አንድ አካል አንድ ሥጋ፣ አንድ መንፈስ ናቸው ለማለትም በጭራሽ አይቻልም። ጥልቁ የአንድነት ምሥጢር ይቅር ቢባልና እንደ ሁለት እግር ብንቆጥራቸው እንኳን ሊስማሙና ወደ ፊት ለመራመድ አይችሉም።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ‹‹እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን›› የሚል አስደናቂ ቃል አለ። (ኢያ፳፬÷፲፭) የባልና ሚስቱ ሃይማኖት በተለያየበት ሁኔታ ይህን ቃል እንደ ቅዱሱ መጽሐፍ ደግሞ ማለት ይቻላልን? ያንተ ሃይማኖት ሌላ የሚስትህ ሃይማኖት ሌላ ሆኖ ሳለ እኩል ‹‹ክርስቲያኖች ነን፣ እግዚአብሔርን እናመልካለን›› ለማለት እንዴት ይቻልሃል? ‹‹እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን›› ለማለት የቤተሰብኽ ሃይማኖትና ያንተ ሃይማኖት አንድ መሆን አለበት። ሚስት ቤተሰብህ አይደለችምን? ባልሽ ቤተሰብሽ አይደለምን?

www.ethiopianorthodox.org

ሃይማኖት ለባልና ለሚስት የጋራ ጉዳይ መሆን አለበት፡፡ እንደመልካቸው ለየራሳቸው የሆነ ሃይማኖት ሊኖራቸው አይገባም፡፡ ባልና ሚስት በተናጠል የሚኖራቸው ነገር አለ፡፡ ከውጫዊ ነገር እንደ ልብሳቸው ያለውን ከባሕርያቸው ደግሞ እንደ አካላቸውና መልካቸው ያለውን መጥቀስ ይቻላል፡፡ እንደዚህ ያሉት ለየግል የሚኖራቸው ነገር ነው፡፡

ነገር ግን ፈጽሞ ሊለያዩት የማይገባ ለባልና ለሚስት የጋራ ብቻ መሆን ያለበት ነገር ደግሞ አለ፡፡ ለምሳሌ ልጆች ለባልና ለሚስት የጋራ እንጂ የተናጠል ንብረቶች አይደሉም፡፡ እንደዚሁም ሃይማኖት ለባልና ለሚስት የጋራቸው ነው፡፡ መንፈሳዊነት ለባልና ለሚስት የጋራ መሆን እንዳለበት የሕይወት ውኃን ሊሰጣት ፈልጎ ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሳምራዊቷን ሴት ‹‹ባልሽን ጠርተሽ ወደዚህ ነዪ›› በማለቱ ይታወቃል፡፡ (ዮሐ፬÷፲፮) ባለትዳር ከሆንን ለየብቻችን ብንማርና ብንሠራም መንፈሳዊ ሕይወታችንን ለየብቻ ለመምራት ባንሞክር መልካም ነው፡፡

ጋብቻህን በእውነተኛ የእግዚአብሔር መንገድ ማከናወን ይኖርብሃል፡፡ ጋብቻን እግዚአብሔር እንደመሠረተው ታምናለህን? ይህን ካመንክ ጋብቻ በእግዚአብሔር ፈቃድ፣ በመንፈሳዊ መንገድ፣ በእርሱ ሕግና ሥርዓት መሠረት መፈጸም እንዳለበት ለማመን አይቸግርህም፡፡ ከዚህ በኋላ ‹‹ታዲያ የእርሱ መንገድ የትኛው ነው?›› ወደ ማለት ትመጣለህ፡፡ ወደ እርሱ የምታደርሰዋ መንገድ ሃይማኖት ናት፡፡ እርሷም ‹‹አንዲት›› ናት፡፡ በእርሷም የሚፈጸም ጋብቻ በፈጣሪ ዘንድ እውቅና ያገኛል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው›› ይላል፡፡ (ማቴ፲፱÷፮) ይህ ቃል የተነገረው ስለ ጋብቻ ነው፡፡ አንድ የሚያደርግ ወይም የሚያጣምር ፈጣሪ መሆኑን ያስረዳል፡፡ ሰው በራሱ ፈቃድ ሊጣመር የማይችል ከሆነ ጋብቻ እግዚአብሔር በሚወደው መንገድ መከናወን ይኖርበታል ማለት ነው፡፡ እርሱ በመካከል የሚገኘውና ባልና ሚስቱን አንድ





የሚደርጋቸው ደግሞ ፈቃዱ ሲፈጸምና ሁለቱም በአንድ ሐሳብ፣ በአንድ ሃይማኖት ሆነው ሲለምኑት ነው፡፡

የጋብቻ መሥራች፣ ባለቤትና ተጠሪ ፈጣሪ እስከሆነ ድረስ ያለ ሃይማኖታዊ ሥርዓት ከእርሱ ፈቃድ ውጭ የሚፈጸም ጋብቻ መሠረት የሌለው ቤት ነው፡፡ ወይም በከንቱ መሠረት ላይ የተሠራ ቤት ይሆናል፡፡ መሠረቱ ‹‹ዓለት›› ማለትም በእግዚአብሔር ቃል መሠረት የተዘጋጀ ሃይማኖትና ምግባር ባለመሆኑ ደግሞ በቀላሉ ይፈርሳል፡፡ (ማቴ፯÷፳፬-፳፯) በሃይማኖት መንገድ ከተፈጸመ ጋብቻ ይልቅ በማኅበራዊ ተቋማት በተፈጸሙ ጋብቻዎች ላይ የፍቺ አኀዝ በልጦ መታየቱን ጥናቶች ማሳየታቸው ይህን ያስረዳል፡፡ ይህንንም ከመረጃ መረብ ድኅረ ገጾች ብታስስ ለቁጥር የሚያታክት ምስክር ታገኛለህ፡፡

ምን ጊዜም ቢሆን ጋብቻን በሃይማኖታዊ መንገድ ማከናወን ፈጣሪ የአምላክነት ድርሻውን እንዲወጣ ዕድል መስጠት ነው፡፡ በቃና ዘገሊላ በተደረገው ሠርግ ፈጣሪ ስለተጋበዘ ደጋሾቹ አምላካዊ ድጋፍ አግኝተዋል፡፡ የወይን ጠጅ ባለቀባቸው ጊዜ ውኃውን ወደ ወይን ለውጦላቸዋልና፡፡ ይህም ፈጣሪ በጋብቻቸው ለሚጠሩትና ለሚፈልጉት ሁሉ አምላካዊ ድጋፉን እንደሚቸራቸው ያሳያል፡፡ (ዮሐ፪÷፩-፲፩)

ባልና ሚስት በሃይማኖት ሲለያዩ ልጆችም እንደዚያው ሊለያዩ ይችላሉ፡፡ ይህም ውጤቱ አስከፊ ሊሆን ይችላል፡፡ ከባልና ሚስት አንሥቶ በርካታ የቤተሰብ አባላት በመሠረተ እምነት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የተለያየ አመለካከት የያዙበት ሁኔታ አለ፡፡ ክብር ይግባውና ኢየሱስ ክርስቶስን ያለ አግባብ ‹‹ፍጡር ነው፣ አማላጅ ነው፣ ወዘተ…›› እያሉ መለያየታቸው ለዚህ ምስክር ነው፡፡ ስለዚህ ከተጋቡ በኋላ እንዲህ ያለ መለያየት እንዳይፈጠር ቤትን በትምህርተ ሃይማኖትና በጸሎት ማጠር ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ የሚቀድመው ደግሞ ከማያምኑ ጋር በጋብቻ ላለመተሳሰር መጠንቀቅ ነው፡፡

ሃይማኖት የግል ቢሆንም ፍጻሜውና ጠቀሜታው ማኅበራዊ ሆኖ ይገኛል። ስለዚህ የሃይማኖትን ነገር ሁል ጊዜ እንደ ግላዊ ጉዳይ ብቻ መመልከት ጉዳቱ ያመዝናል። ይህ አመለካከት የበለጠ ጎጂ ሆኖ የሚገኘው በባልና በሚስት መካከል ሲሆን ነው። ለምሳሌ ሃይማኖት የግል ነው ብለህ ሚስትህ የሌላ ሃይማኖት ተከታይ ሆና ሳለ አገባሃት እንበል። አንተ በጾም ወራት መኝታ ለይተህ ወይም ከግንኙነት ርቀህ ታሳልፋለህ ሃይማኖትህም ይህን እንድታደርግ ያዝሃል። እርሷ ግን በሃይማኖቷ ውስጥ ያንተን የሚመስል ሕግ እስከሌላት ድረስ ሩካቤ ማድረግ ትፈልጋለች። ሃይማኖት የግል ነው ካላችሁ ይህን ልዩነት በምን ማስታረቅ ትችላላችሁ? የባልና የሚስት ሩካቤ የግል ነውን? ምናልባት እንዲያውም በሷ ሃይማኖት ጾምም ሆነ በጾም ወራት ከሩካቤ መከልከል ከንቱ ነገሮች ሆነው ሊሰበኩ ይችላሉ። ይህ በወንዱ በኩል ሆነን ስናየው ነው። በሴቲቱም በኩል ብንመለከተው ሐሳቡ አይለወጥም።

ጉዳዩን ብታሰፋው ደግሞ በተለይ ባልና ሚስትን ብቻ የሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የየሃይማኖቱ ቀኖና እጅግ በጣም ሰፊ ልዩነት እንዳለው ልትገነዘብ ትችላለህ። ወሊድን፣ የወሊድና የአባለዘር በሽታዎችን ስለመከላከያ መንገዶች፣ ፅንስ ስለማቋረጥ፣ ብዙ ስለማግባት፣ ስለ ፍቺ፣ በፍቺ ጊዜ ባልና ሚስት ስለሚኖራቸው ድርሻና መብት በየሃይማኖቱ ያለው ቀኖና ይለያያል። ክርስቲያን ሆነሽ እስላም ባል ብታገቢ ባልሽን ‹‹በእኔ ላይ ሌላ ሴት ለምን ታገባለህ?›› ልትዪው አትችዪም። ምክንያቱም ሃይማኖቱ እስከ አራት ሚስቶች እንዲያገባ ይፈቅድለታልና። ሌላው ቀርቶ ባልሽ እንደ ሕፃን ልጅ ሊገርፍሽና ሊቀጣሽ በቁርአን ሥልጣን ተሰጥቶታል። (አል-ኒሳእ ፬ አያት፫ እና ፴፬) በሃይማኖት አንድ መሆን እነዚህን የልዩነት አደጋዎች ሁሉ የሚያስወግድ ነው።

በምንም መንገድ አንድ መሆንና መስማማት ቢቻልም በሃይማኖት ብቻ እንኳን መለያየት በሁሉም ነገር የመለያየት





ያህል ነው። ምክንያቱም ከማንኛውም ትልቅ ቁሳዊና ውጫዊ ነገር ይልቅ ነገረ ሃይማኖት ከሥጋ፣ ከነፍስ፣ ከመንፈስና ከአእምሮ ጋር ጥልቅ ትሥሥር ያለው ነገር በመሆኑ ነው። በተጨማሪም ከማናቸውም ነገሮች በላይ ነገረ ሃይማኖት እኛነታችንን የመወሰንና የመቅረጽ ኃይል አለው።

የሃይማኖትን አንድነት ቢቀርም እንደማይጎዳ እንደ አንድ መልካም ነገር ብቻ፣ እንደ ባህል፣ ወይም እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ወይም ሙያ ብቻ የሚቆጥሩት ሰዎች አሉ። ይህም ከባድ የአመለካከት መዛባትን ይፈጥራል። በአንድ የትምህርት ዘርፍ ወይም የሥራ ዓይነት ባይሳካልህ የሕይወትህ መብራት ጠፋችብህ ማለት አይደለም። በሌላ አቅጣጫ ተሳክቶልህ በደስታ ለመኖር ትችላለህና። በሃይማኖትህ ግን ያልቀናውን ጎዳና ብትከተል መላ ሕይወትህን ታበላሸዋለህ። ስለዚህ ሃይማኖት እንደ አንድ ንዑስ የሕይወት ዘርፍ ብቻ የሚታይ ሳይሆን መላ የአንተነትህን ደረጃ እንደሚወስን መረዳት አለብህ። በትዳርህ ውስጥ ተስፋ የምታደርጋቸው ፍቅር፣ ሰላምና ደስታ በምትከተለው ሃይማኖት ላይ የተመሠረቱ ነው። ይህ የበለጠ የሚገባህ በራስህ ሲደርስ ወይም ሌሎች በሃይማኖታቸው መለያየት ምክንያት ፍቅር ያለቸው ቢመስሉ እንኳን ውሳጣዊ ሰላም አጥተው ወይም ትዳራቸው ተበጥብጦ ስታይና ስትሰማ ነው።

ነገረ ሃይማኖት ውስብስብ፣ ረቂቅና ሁለገብ ነው። ሚሏትም የልብህን እምነት አስተሳሰብህን፣ ምግባርህን፣ ጠባይህን፣ ስሜትህን በአጠቃላይ መላ አንተነትህን ይቀርጻል፤ ይወስናልም። ሃይማኖትህ የቀናች ከሆነች ሁለመናህ ቀና ይሆናል። ሃይማኖትህ ጨለማ ከሆነች ሁሉም ነገር ይጨልምብሃል። ሃይማኖት የሰውነት መብራት ናትና።

ሃይማኖትህ በሁለንተናህ ላይ እንድትሠለጥን ካልፈቀድክላት አንተ ሃይማኖት አለኝ ማለት አይገባህም። ሰው በሁሉም ረገድ ለሃይማኖቱ ይታዘዛል እንጂ በራሱ ፈቃድ የተመቸውን እየመረጠ ብቻ የሚጓዝ ከሆነ ሃይማኖቱን የፍጡር ውጤት ያደርጋታል።

የወደድከውን መርጠህ በመውሰድ ያልወደድከውን የምትተወው ከፍጡር የሚገኝ ነገር ሲሆን ነው፡፡ ከፈጣሪ ያገኘሽውን ሃይማኖት ግን ሙሉ ለሙሉ መቀበልና መፈጸም ይኖርብሃል፡፡ ሃይማኖተኛ ሰው በነገር ሁሉ ለሃይማኖቱ ቅድሚያ የሚሰጥ እንጂ የራሱን ፈቃድ የሚያስቀድም አይደለም፡፡ በሁለንተናህ ላይ ሥልጣን የሌለው ሃይማኖት ሃይማኖት አይባልም፡፡ ሃይማኖት በሰው ሕይወት ይህን ያህል ስልጣን ካለው ደግሞ እርሱን ችላ ብሎ ጋብቻን ማሰብ የማይሆን ነገር ነው፡፡

ዓይንህ እንግዲህ ጤናማ ብትሆን፥ ሰውነትህ ሁሉ ብሩህ ይሆናል፤ ዓይንህ ግን ታማሚ ብትሆን፥ ሰውነትህ ሁሉ የጨለመ ይሆናል፡፡ እንግዲህ በአንተ ዘንድ ያለው ብርሃን (ማለትም ዓይንህ፣ ሃይማኖትህ) ጨለማ ከሆነ፥ ጨለማው እንዴት ይበረታ? የሚለው የወንጌል ቃል ምንኛ ድንቅ ነው? ይህ ማለት ሃይማኖተኛ መሆንህ ብቻ ትልቅ ነገር አይምሰልህ፡፡ የምትከተለው ሃይማኖት ጤናማ መሆን አለበት፡፡ በተሳሳተ የሃይማኖት አቅታጫ ብትጓዝ ካለማመን ቢከፋ እንጂ የተሻለ ነገር የለውም፡፡

በርእዮተ ዓለም፣ በፖለቲካ አመለካከት፤ በገንዘብ ዐቅም፣ በትምህርት ደረጃ መራራቅ፣ በእድሜ፣ በዓላማና በፍላጎት አለመመሳሰል ለተጋቢዎች እንደ ትልቅ ልዩነት የሚታይ ከሆነ የሃይማኖት ልዩነታቸው እንደ ኢምንት የሚቆጠረው ለምንድን ነው? እንዲያውም የግል ዓላማ፣ ፍላጎትና አስተሳሰብ ከጊዜ ጋር ሊለዋወጡ የሚችሉ ነገሮች በመሆናቸው በእነዚህ ነገሮች ምክንያት በባልና በሚስት መካከል የተፈጠረ ልዩነት በራሱ ጊዜ የበለጠ ሊሰፋ፣ ሊጠብ ወይም ፈጽሞ ሊወገድ ይችላል፡፡ የሃይማኖት ልዩነት ግን ረቂቅና ጥልቅ በአንጻሩም ዘለቄታዊና ጽኑ ወይም በቀላሉ የማይለወጥ በመሆኑ እንዲህ በቀላሉ ሊጠብ ወይም ሊወገድ የሚችል ነገር አይደለም፡፡

ነገረ ሃይማኖት በሕይወትህ ውስጥ የሚጫወተው ሚና ካንተ ዓላማ፣ ዕቅድ፣ ፍላጎትና አስተሳሰብ የሚያንስ





ይመስልሃልን? ዓላማዬን፣ የወደፊት ዕቅዴን፣ ፍላጎቴንና ምኞቴን ያጨናግፍብኛል ብለህ ለምትጠረጥረው ዓይነት ትዳር እጅህን እንደማትሰጥ የታወቀ ነው፡፡ ይህም እንዳይከሠትብህ በብርቱ ትጠነቀቃለህ፡፡ ከማታምንና ለሃይማኖቷ ግድ ከሌላት ሴት ጋር በመጋባት ከሃይማኖትህ ጉዞ የሚያሰነካክልህን ተግባር ስትፈጽም ምንም ስጋት ስጋት አይልህምን?

ለብዙዎች ይህ ዘመን በመቻቻል የመኖር ባህል የዳበረበት የሠለጠነ ዘመን ብቻ ይመስላቸዋል፡፡ ስለሆነም ከቀድሞ ዘመን ይልቅ በዚህ ዘመን በሃይማኖት የተለያዩ ወንድና ሴት ጋብቻ ቢፈጽሙ ችግር እንደሌለው የሚያስቡ አሉ፡፡ ነገር ግን ይህ ጉዳይ መታየት ያለበት ከዚህ በተቃራኒ አቅጣጫ ነው፡፡

ይህ ዘመን ከቀድሞ ይልቅ ‹‹የሃይማኖት አክራሪነትና አሸባሪነት›› የበዛበት፣ ክህደት የጸናበት፣ በቅጽበት መላ አቋምንና ማንነትን መለዋወጥ እንደዘመናዊነት የሚቆጠርበት፣ ፍቅር የቀዘቀዘበት፣ ጭካኔ የነገሠበት፣ ብዙዎች ለፖለቲካና ለልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅም ማስከበሪያ ሃይማኖትን እንደ መሣሪያ ያዋሉበት ዘመን ነው፡፡ በመሆኑም ተጋቢዎቹ በሃይማኖት ተለያይተው ሳለ በመቻቻል መኖር የሚቻላቸው መስሎ ቢታያቸውም እንኳን ይህ ሐሳባቸው የጠዋት ጤዛ ነው፡፡

አንዲት ሴት ምታገባው ባል እርሷ እንደምታውቀው ዓይነት ሙስሊም ብቻ ሳይሆን አክራሪ ወይም አሸባሪ ሆኖ የመገኘት ዕድሉ በጣም ሰፊ የሆነበት ዘመን ላይ ደርሰናል፡፡ ባልሽ ወይም ትዳርሽ የዚህ ዓይነት አደጋ የተጋረጠበት እንዲሆን ትፈልጊያለሽ? ከዚህ ሁሉ ቀናው መንገድ ከማያምኑ ጋር በማያመች አካሄድ ከወዲሁ አለመጠመድ ነው፡፡

ምናልባት ባልና ሚስት በሃይማኖት የማይመስላቸውን ሰው አግብተው በመኖራቸው የሚፈጠርባቸውን ልዩነት ችለዉት ለመኖር ይወስኑ ይሆናል፡፡ እነርሱ ቢቻቻሉም እንኳን ከየአቅጣጫው የሚሰነዘርባቸው ተቃውሞና ትችት ከዓቅማቸው በላይ ሊሆን ይችላል፡፡ ወዳጅ ዘመድ፣ ባልንጀሮች ቤተሰብእና

ወላጆች ሁሉ የእኔ የሚሉአቸውን ሰዎች በሃይማኖት ከማይመስላት ወይም ከማትመስለው ሰው ጋር ሲጋቡ አይተው ዝም ማለት አይሆንላቸውም፡፡ በተቋም ደረጃ ሃይማኖቶቹ ራሳቸው አባላቸውን ላለማጣት የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ሊኖር ይችላል፡፡ ሌሎች አካላትም ተመሳሳይ ጫና የሚያሳድሩበት ጊዜና ሁኔታ ይኖራል፡፡ ይህን መሰሉ ውጫዊና ውሳጣዊ ጫናዎች ደግሞ ጥንዶቹን ባሰቡትና በሚመኙት መንገድ እንዳይኖሩ ሊያደርጋቸው የሚችልበት ዕድል የሰፋ ነው፡፡ በመጨረሻም እስከመለያየትና እስከመፋታት ሊደርሱ ይችላሉ፡፡

ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን በሃይማኖት የተለያዩ ወንድና ሴት ልዩነታቸውን ሳያስወግዱ ጋብቻ እንዳይፈጸሙ የምታስተምረው የልጆችን አስተዳደግ፣ ዘመናችንንና የዓለምን ክፉ አካሄድ፣ ወደፊት ሊያጋጥም የሚችልን ማንኛውንም የኑሮ እንቅፋት ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ ይህ ደግሞ መንፈሳዊነትና አርቆ ተመልካችነት ነው እንጂ ጭፍንነት፣ አለመሠልጠንና ወግ አጥባቂነት ወይም የ‹‹ፍቅር ባላንጣነት›› አይደለም፡፡

እውነት ለመናገር አንድ ሰው ‹‹የማገባት ሴት ይህ ይህ ነገር ሊኖራት ይገባል›› ብሎ ከሚፈልግባት ከማንኛውም ነገር ይልቅ ሚስቱ በሃይማኖት እርሱን የምትመስለው ብትሆንለት የበለጠ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡ ለሴቲቱም ቢሆን የምታገባው ሰው እንዲኖረው ከምትፈልገው ማንኛውም ቁሳዊ ነገሮች ይልቅ ባሏ በሃይማኖት እርሷን የሚመስል ቢሆን የበለጠ ተጠቃሚ ናት፡፡ በተጋቢዎች መኻል ከማንኛውም መስፈርት ይልቅ የሃይማኖት አንድነት ቀዳሚውን ስፍራ መያዝ የሚኖርበት ስለዚህ ነው፡፡

በዓለማችን ላይ ልዩ ልዩ የአምልኮ ሥርዓት ያላቸው በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የእምነት ድርጅቶች አሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ሁሉም ለማለት በሚያስደፍር ቁጥር (ከጥቂቶች በቀር) አብዛኞቹ የጋብቻን መልካምነት ተቀብለው ሥርዓታቸው በሚያዛቸው መንገድ ጋብቻን ይፈጽማሉ፡፡ እምነታቸው እውነትም ሆነ ሐሰት





በምድር ላይ የሠመረ ትዳር ለመምራት የአንድ እምነት ተቋም ተከታዮች ሆነው ጋብቻ መፈጸማቸው የሚመከር ነው፡፡

ከላይ የተጠቀሰው ምክር አዘል ቃል የሚያስገነዝበን አንድ ጭብጥ አለ፡፡ ይኸውም እንኳን ርትዕት በሆነች በክርስትና ሃይማኖት ለሚኖር ሰው ቀርቶ በክህደትና በመናፍቅነት ለሚኖሩ ለሌሎች ሰዎችም ቢሆን በተለያየ የእምነት አቋም ላይ ሳሉ መጋባት ምን ያህል ለሰላማዊ ኑሮ ከባድ እንቅፋት ሊሆን እንደሚችል ነው፡፡

ለጋብቻ ምንም ዓይነት መስፈርት ቢኖርሽ አንቺ የምትፈልጊው ዓይነት ወንድ በራስሽ ሃይማኖት ውስጥም አይጠፋም፡፡ ታዲያ ወደ ሌላ የእምነት ተቋማት አባላት መማተር ለምን አስፈለገሽ? ምንም ሳታጪ ወደ ሌላ ማየትሽስ ተወቃሽነትሽን የበለጠ እንደሚያሳድገው አታውቂምን? ደግሞስ የምትሺው እርሱን ነው? ወይስ ሃይማኖቱን? እርሱን ብቻ የምትሺ ከሆነ ለምን አትታገሺም? መሰሉን በራስሽ ሃይማኖት ታገኚ የለምን? ማንኛውንም መልካም ነገር ለማግኘት ትዕግሥት ማድረግንና ጊዜ መስጠትን ይጠይቃል፡፡ እውነተኛ ባልን ለማግኘትማ እንዴታ! ስለዚህ መልካም ትዳር ለማግኘት የሚጠበቅብሽ በሃይማኖታዊ ሥርዓት ጸንተሽ ፈጣሪሽን በትዕግሥት መጠባበቅ ነው፡፡ ለወንዱም ቢሆን እንዲሁ ነው፡፡

እንኳን ለጋብቻ ለባልንጀርነትም ሃይማኖት መመዘኛ መስፈርት መሆን ይገባዋል፡፡ ቅዱስ ዳዊት እግዚአብሔርን ለሚፈሩ ምእመናን የሰጠው ሰፊ ልብ ምን ይመስል እንደነበር ቀጣዩ ጥቅስ ያስረዳሃል፡፡ ንጉሥ ዳዊት ‹‹ከእኔ ጋር ይኖሩ ዘንድ ዓይኖቼ በምድር ላይ በሚኖሩ <u>ምእመናን</u> ላይ ናቸው፡፡›› ብሏል፡፡ (መዝ፻÷፮-፯) በዘመኑ የንጉሥ ዳዊት ዓይኖች በ‹‹ምእመናን›› ላይ ነበሩ፡፡ ከእርሱ ጋር አብረውት ይሆኑ ዘንድ ዕድል የሰጠውም ለምእመናን ነበር፡፡ ‹‹ምእመን›› የሚባለው ደግሞ ቀና ሃይማኖት ያለውና ‹‹ታማኝ›› ሰው ሁሉ ነው፡፡

ያንተ ዓይኖች በማን ላይ ናቸው? አብረህስ የምትኖረው ከእነማን ጋር ነው? ባልንጀሮችህ ምእመናን ናቸውን? የባልንጀርነቱን ነገር ተወውና ባለትዳር ከሆንክ ከሚስትህ ጋር በሃይማኖት ትተባበራላችሁ ወይስ ለየቅል ትጓዛላችሁ? ያጨኸ ከሆንክ ደግሞ እርሷ አንተን በሃይማኖት ትመስልሃለች? ወደፊት የምታጭ ወጣት ከሆንክ ደግሞ ሃይማኖትን በተመለከተ ያለህ አቋም ምን ይመስላል? ለጋብቻ የመረጥካት ሴት የትኛውንም ሃይማኖት ብትከተል አንተ ከወደድካት ግድ የለህምን? ፍቅር ትክክለኛ ትርጉም የሚያገኘው በሃይማኖት መሆኑን ታውቃለህ? ታዲያ እውነተኛ ሃይማኖት ሳይኖር ፍቅር ሊኖር እንዴት ይችላል?

በተጨማሪም እግዚአብሔርን የሚፈሩና ትእዛዙን የሚጠብቁ ሁሉ ለዳዊት ባልንጀሮቹ እንደሆኑ ራሱ ቅዱስ ዳዊት ሲናገር «እኔ ለሚፈሩህ ሁሉ ትእዛዝህንም ለሚጠብቁ ባልንጀራ ነኝ» ብሏል፡፡ (መዝ፻፲፰÷፷፫) በዚህ ቃል መሠረት ቅዱስ ዳዊት ራሱን ባልንጀራ ያደረገው እግዚአብሔርን ከሚፈሩ ከምእመናን ጋር ነው፡፡ የባልንጀርነት ፍቅር ወደ ትዳር ማምራት አለማምራቱን ማን ያውቃል? ባልንጀሮችህ ምእመናን ከሆኑ የትዳር አጋርህ ከምእመናን ወገን የመሆን ዕድሏ ያንኑ ያህል ይሰፋል፡፡

ይህ የንጉሥ ዳዊት ንግግር ጓደኛ ለማድረግ የአንድን ሰው ውጫዊ አቋምና የምግባር ቀናነት ከመመልከት አስቀድሞ በእግዚአብሔር ላይ ያለው እምነት ምን ይመስላል? ፈጣሪውን ይፈራል? ወይስ አይፈራም? በማለት ማመዛዘን እንደሚገባ ይጠቁማል፡፡ ይህ ባልንጀራ ለማድረግ ነው፡፡ ለትዳር ሲያጩስ ከዚህ በላይ የሃይማኖትን ነገር ቅድሚያ ሰጥቶ መመርመር አይገባምን?

ከሚስትህ ጋር በሁሉም መንገድ አንድ መሆን አትፈልግም? ታዲያ አንድ የሚያደርጋችሁ ማን ነው? እግዚአብሔር አይደለምን? በመጀመሪያ አዳምና ሔዋንን አንድ ያደረጋቸው ፈጣሪ ነው፡፡ ቀጥሎም ‹‹እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው›› ተብሏል፡፡ (ማቴ፲፱÷፮) ብር፣ ወርቅ





የትምህርት ደረጃ፣ ሥልጣንና ጥቅም ወንድና ሴትን ለዘለቄታው አንድ ሊያደርጉ ይችላሉ?

የእግዚአብሔር መንፈስ ግን እንኳን ሁለቱን ማለትም ባልና ሚስትን ብዙ ሕዝብን አንድ ያደርጋል፡፡ ሐዋርያትንና ሌሎች ደቀ መዛሙርትን አንድ ልብና አንድ ቃል እንዲኖራቸው ያደረገው መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ካህኑ ዘካርያስንና ሚስቱ ኤልሣቤጥን ሳይወያዩ አንድ ቃል እንዲናገሩ፤ በተናጠል ተጠይቀው ለልጃው አንድ ስም እንዲያወጡ ያደረጋቸው የእግዚአብሔር መንፈስ ነው፡፡

ኤልሣቤጥ ለልጇ ስም ስታወጣ ከባሏ ጋር ሳትነጋገር መንፈስ ቅዱስ አድሮባታልና ‹‹ዮሐንስ›› አለችው፡፡ ባሏ ዲዳ ሆኖ ነበርና አስቀድሞ ምንም ሊላት አልቻለም፡፡ እርሱ ስለ ልጁ ስም በተጠየቀ ጊዜ የሚስቱን አስተያየት ሳይሰማ መልአኩ ባበሠረው መሠረት ‹‹ዮሐንስ›› ይባል ብሎ ጻፈ፡፡ (ሉቃ፩÷፲፫፤ ፩÷፷፤ ፩÷፷፫) ባልና ሚስት አንድ መንፈስ ሲኖራቸው እንደ ካህኑ ዘካርያስና ኤልሣቤጥ በነገር ሁሉ የተስማማ አቋምና ዓላማ ይኖራቸዋል፡፡ እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ይሆናሉ፡፡ ከመነጋገር፣ ከመወያየትና ከመመካከር በላይ የእግዚአብሔር መንፈስ አንድ ያደርጋልና፡፡ አንድ መንፈስ በመካከል እንዲኖር ደግሞ አንድ ሃይማኖት ሊኖር ግድ ነው፡፡ ስለዚህ የባልና የሚስት ሃይማኖት አንድ መሆን ይኖርበታል፡፡

## ‹‹ከማያምኑ ጋር›› መጋባት ያለው መዘዝ

የተጠቀሱትን የሃይማኖት ቀኖናዎች፣ ትምህርቶችና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያዎችን ወደ ጎን በማድረግ ከማያምኑ ጋር መጋባት ብዙ መዘዝ አለው፡፡ ሊያደርስ የሚችለውን ችግር ዘርዝሮ መፈጸም አይቻልም፡፡ በአንደኛ ደረጃ ከፈጣሪ ጋር ያጣላል፡፡ ቀጥሎም ከቤተሰብእ፣ ከዘመድና ከወዳጅ ሁሉ ጋር ሊያራርቅና ሊያቀያይም ይችላል፡፡ አፍላ የፍቅር ስሜት

ሲሚጠጥና ውጫዊው ጫና ሲበረታ ጭቅጭቅ ያስከትላል። ዝብርቅርቅ ቤተሰብእ ይፈጥራል።

"ለውጥ የተፈጥሮ ሕግ ነው" ይባላል። ሰው ደግሞ የተፈጥሮ አንድ ቅንጣት ስለሆነ ለተፈጥሮ ሕግ ይገዛል። ስለዚህ መሻሻልና መለወጥ በሰው ውስጥ ይኖራሉ። በእርግጥ ለውጥ ለመጥፎና ለመልካም ሊሆን ይችላል። የሰው ልጅ የሚለወጠውና የሚሻሻለውም በብዙ አቅጣጫ ነው።

ለውጥ ያለ ነውና ሃይማኖትን በተመለከተ ዛሬ ልዝብ አቋም ያለው አንድ ሰው ነገ በዚህ ሁኔታ ላይቀጥል ይችላል። የላላ አቋም በነበረው ጊዜ ለሃይማኖቱ ግድ ሳይኖረው በሃይማኖት ከማትመስለው አንዲት ሴት ጋር ጋብቻውን የፈጸመ አንድ ሰው ለሃይማኖቱ ትኩረት መስጠት እንዳለበት የሚያሳምነው ሁኔታ በሕይወቱ ሲፈጠር ወይም በራሱ ይህን ማድረግ አለብኝ ብሎ በሚወስንበት ጊዜ ትዳሩ ችግር ላይ መውደቅ ይጀምራል። ስለዚህ በዚህ መልኩ የወደፊት ዕጣውን በማስተዋል የሚመለከት ሰው በጊዜያዊ ስሜት ተማርኮና በቁሳዊ ነገር ተገዝቶ በሃይማኖት ከማይመስለው ሰው ጋር ጋብቻ አይፈጽምም።

በሃይማኖት የተለያዩ ወንድና ሴት ባሉበት ሁኔታ እንጋባ ብለው ሲወስኑ የመቻቻል ክሂሎት አላቸው አያሰኝም። መቻቻል ይህን በመሰለ ሥጋዊነት ሳይሆን በሌላ በመልካም መንገድ መገለጥ አለበት። ይልቅ የሚያመለክተው ጥንዶቹ ለየሃይማኖታቸው የሰጡትን ዝቅተኛ ቦታ ነው። በተጨማሪም ስለወደፊት ሕይወታቸውና ስለልጆቻቸው ዕጣ ፋንታ አርቀው አለመመልከታቸውን ያሳያል። ምክንያቱም የሚወልዷቸው ልጆች በአስተሳሰብ፣ በዝንባሌና በስሜት ከእነርሱ በጣም የተለየ የራሳቸው ማንነት ያላቸው መሆናቸውን እንኳን አልተረዱምና። ሰው ከሃይማኖቱ ይልቅ የግሉን ፈቃድ ከተከተለ ምን ያህል ለሥጋው እየተገዛ መሆኑን ይጠቁማል። ባልና ሚስቶች ከሃይማኖታቸው ሕግጋትና ሥርዓት በራቁ ቁጥር ከሃይማኖታቸው ውጭ እየሆኑ ይመጣሉ።





ወላጆች በተለያየ ሃይማኖት የሚኖሩ ከሆነ እንኳን ወልዶ ማሳደግ ይቅርና ለልጆች ስም ማውጣት እንኳን ቀላል ነገር አይሆንም። በየሃይማኖቱ የየሰው አሰያየም የተለያየ ትርጉም ያስከትላልና። ታዲያ በሃይማኖት የተለያዩ ወንድና ሴት የሚጋቡት ልጆች ወልደው በየትኛው ሃይማኖታዊ ኅብረተሰብ ውስጥ ሊያሳድጓቸውና ሊመሩአቸው ነው? በአባታቸው ወይስ በእናታቸው ሃይማኖት?

ልጆች ከውጭ የሚሰነዘርባቸውን ዘለፋና ተፅዕኖ እንዴት ሊቋቋሙ ይችላሉ? ሃይማኖታዊ ሥርዓታቸውንስ እንዴት ይፈጽማሉ? የማናቸውንስ ሃይማኖታዊ በዓል ያከብራሉ? የአባታቸውን? የእናታቸውን ወይስ የሁለቱንም? ለምሳሌ፡- ልደተ ክርስቶስን ወይስ ‹‹መውሊድን››? ጥምቀትን ወይስ ‹‹አረፋን››? ልጆችን ጫወታና በዓል ማክበር ያስደስታቸዋልና። የት ሄደው ትምህርተ ሃይማኖት ይከታተላሉ? ቤተ ክርስቲያን ወይስ ‹‹መስኪድ?›› ወይስ ወደ ሌላ የእምነት ተቋም አዳራሽ?

እንደሚታወቀው በየሃይማኖቱ የቀብር ስፍራና ሥነ ሥርዓት አለ። ታዲያ ከዚህ ዓይነት ጋብቻ የተገኙ ልጆችና ወላጆቻቸው ሲሞቱ የሚቀበሩት እንዴትና የት ነው? ልጆች በእናትና በአባታቸው የሃይማኖት ልዩነት የተነሣ ምንም ዓይነት ሃይማኖታዊ ሥርዓት ሳይፈጽሙ ቢቀሩ በምን መንገድ ሕይወታቸውን የተሟላና ደስተኛ ሊያደርጉት ይችላሉ? ማኅበራዊነት ለሰው እንደ መሠረታዊ ፍላጎት ነውና።

ልጆችን «ወንዱን ላንተ ሴቷን ለእኔ» እያሉ በተለያየ መንገድ ማለትም በጾታ፣ በዕድሜ፣ በዝንባሌና በጠባይ፣ እየከፋፈሉ ወላጆቻቸው ወደየራሳቸው የእምነት አቅጣጫ ለመውሰድ መሞከራቸው በልጆቻቸው መካከል ምን ሊፈጥር እንደሚችል ወላጆች አያውቁምን? ወይስ አንድን ልጅ ወደ ሁለቱም ወላጆቹ የሃይማኖት ሥርዓት መፈጸሚያ ስፍራ በየተራ መውሰድ፣ ወይም ወደ ማናቸውም ሃይማኖት እንዳይሔድ ማገድ

ያንን ሕጻን ማምታታትና ግራ ማጋባት እንደሆነ ለወላጆቹ ማን በነገራቸው?

ስለዚህ ወላጆች በተለያየ ሃይማኖት ሆነው ሲጋቡ የወደፊቱን እንጂ አሁን ያሉበትን ሁኔታ ብቻ መመልከታቸው በወደፊት ሕይወታቸው ላይ ትልቅ አደጋ አለው፡፡ ሐዋርያው "አለዚያ ልጆቻችሁ ርኩሳን ናቸው" በማለት የተናገረው ቃል በሃይማኖት የተለያዩ ሰዎች በሚጋቡበት ጊዜ የልጆች ነገር ከግምት ውስጥ መግባት እንዳለበት ያመለክታል፡፡ (፩ቆሮ፯÷፲፬)

በሃይማኖት የተለያዩ ወንድና ሴት ልዩነታቸውን ሳይቀርፉ ተጋብተው ለመኖር በሚሞክሩበት ጊዜ ከፍተኛ ችግር እንደሚያጋጥማቸው ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ ለዚህ ጉዳይ ትኩረት ሰጥተው አንዳቸው አንዳቸውን አሳምነው በአንድ ሃይማኖት ለመኖር ከወሰኑ በኋላም ቢሆን ወደፊት ከሌላ ዓይነት ፈተና ጋር መጋፈጣቸው አይቀርም፡፡

እንደሚታወቀው ሁሉ ይህ ዘመን ከፍቅር ይልቅ የመብትና የጾታ እኩልነት ጥያቄ ጎልቶ የሚወደስበት ዘመን ነው፡፡ የሃይማኖት ልዩነታቸውን ካስወገዱ በኋላ የዚህ እርሾ ውጤት የሆነ ሌላ ዓቢይ ችግር ደግሞ ከፊታቸው ድንቅ ይላል፡፡ ይኸውም የመብትና የእኩልነት ጥያቄ ነው፡፡

የሃይማኖት ሉዓላዊነት ቸል ቢባልና አንዱ በአንዱ ሃይማኖት ለመኖር ወስኖ አንድነት ቢመሠርቱ እንኳን ያሳመነው ወገን ሁል ጊዜ እኔ ብቻ ልደመጥ የሚል እብሪት የተሞላ ሥነ ልቦናዊ ችግር ሊፈጠርበት ይችላል፡፡ ለምን ቢባል ሃይማኖትን ያህል ታላቅ ነገር አስለውጦ ለማሳመን በቅቶ የለ?

ይህም ባይሆን "አምኛለሁ" ብሎ የተሸነፈው ወገን "እኔ ለልጆቼና ለትዳሬ ስል ሃይማኖቴን እስከ መተው ደርሻለሁ፤ አሁን ተራው የእርሱ (የእርሷ) ነውና፤ እኔን መስማት አለበት (አለባት)" የሚል ዓይነት ሥነ ልቦናዊ ችግር ይፈጠርበትና ሁል ጊዜ እኔ ብቻ ልሰማ በማለት ለያዥ ለገራዥ የሚያስቸግር ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ያሳመነው ወገን ገና ለገና ሊኮራ ይችላል





እያሉ በማሰብ የሚያደርጉት ነገር የበለጠ ችግር ፈጣሪ ሆኖ ይገኛል፡፡

ከላይ በሁለቱም ጥንዶች መካከል ሊፈጠር ይችላል በሚል የተጠቀሰው ሥነ ልቡናዊ ችግር ሊቀረፍ የሚችለው በሁለቱም በኩል ሊፈጠር የሚችለው ስነ ልቡናዊ ችግር መፍትሔ ሲያገኝ ነው፡፡ አንደኛ ያሳመነው ወገን እርሱ በግል ችሎታው እንዳሳመነ ባይቆጥርና ‹‹በእግዚአብሔር ኃይል ነው›› ብሎ ቢያምን በተጨማሪም ‹‹የኔ ሃይማኖት መታመን ስላለባት እንጂ እኔ አሳማኝ ሆኜ አይደለም›› ቢል ሁለተኛ አዲሱ አማኝ ደግሞ ‹‹ያመንኩት ለትዳሬ ብዬ ነው ከማለት ይልቅ ማመን ስላለብኝ አመንኩ›› ብሎ ቢቀበል ለዚህም ማመኑን እንደተሸናፊነት ባይቆጥረው ነው፡፡

በሃይማኖት ተለያይቶ ጋብቻ መፈጸም የሚያስከትለው ችግር ለዚህ ዓለም ምሁራንም ግልፅ ከመሆኑ የተነሣ ምሁራኑ የሃይማኖትን ነገር ወደ ጎን በመተው ፍጹም ሥጋዊ ምክር በመምከር ላይ ናቸው፡፡ እነዚህ ምሁራን የሚታያቸው የወንዱና የሴቷ የፍቅር ጉዳይ እንጂ የሃይማኖት፣ የመንፈስና የነፍስ እውነታ አይደለም፡፡ ስለሆነም በሃይማኖት የተለያዩ ወንድና ሴት ተፋቅረው ለመጋባት ከወሰኑ ለራሳቸውና ለልጆቻቸው ሰላምና ደስታ ሲሉ ከሚከተሉት አምስት አማራጮች የተስማማቸውን መርጠው እንዲጓዙ ይመክራሉ፡፡

፩ኛ. ሁለቱም ሃይማኖታቸውን እርግፍ አድርገው ይተዉት

፪ኛ. ሁለቱም ከየሃይማኖታቸው የተመቻቸውን መርጠው በማዳቀል ይመሩ

፫ኛ. ሁለቱም የየራሳቸውን በመተው ወደ ሌላ የእምነት ድርጅት ይዛወሩ

፬ኛ. ሁለቱም ባለሁለት ሃይማኖት ይሁኑና በየተራ አንዱ የአንዱን እየፈጸሙ ይኑሩ ወይም

፭ኛ. አንዱ ተለውጦ በሌላኛው ሃይማኖት ይኑር፡፡

በክርስትና ሃይማኖት የሚመከረውና የሚታዘዘው ባልና ሚስት በአንድ ሃይማኖት መኖራቸው ነው፡፡ ስለዚህ በክርስትና ያለው ወገን ክርስቲያን ያልሆነውን አስተምሮ በማሳመንና ለጥምቀት እንዲበቃ በማድረግ ማግባት ይኖርበታል፡፡ ይህን ማድረግ የማይቻል ከሆነ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታና ድርድር ተለያይቶ የወደፊት ሕይወትን በሚገባ አቅጣጫ መምራት ያስፈልጋል፡፡

ክርስቲያኖች በዚህ ዓለም ሲኖሩ ሃይማኖታቸውንና መልካም ምግባራቸውን ከሚያጠፋና ወደ ክፉ ሥራ ከሚመራቸው የጋብቻ ጎዳና ሁሉ መጠበቅ አለባቸው፡፡ እንኳን ከፍተኛ ጫና ማሳደር የሚችለው ጋብቻ ይቅርና ባልንጀርነትም ቢሆን ካልተጠነቀቁበት መልካሙን አመል ያጠፋል፡፡ ‹‹አትሳቱ፤ ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋል›› ተብሏልና፡፡ (፩ቆሮ፲፭÷፴፫) ከማያምኑ ጋር የሚደረግ ጋብቻ ደግሞ ከ‹‹መልካም አመል›› አልፎ ሃይማኖትንም ያጠፋል፡፡

## ‹‹ከማያምኑ ጋር›› ላለመጋባት የሚከፈል መሥዋዕትነት

ለጋብቻ የምንፈልገው ሰው ከሃይማኖቱ ልውጥነት የተነሣ ወይም እኛ እንደምናምነው ካለማመኑ የተነሣ እርሱን ላለማግባት ስንወስን እኛ የምናጣው ወይም የሚቀርብን ብዙ ነገር መኖሩ አይጠረጠርም፡፡ በሥጋዊ ዓይን ብቻ ካልተመለከትነው ያም ሰው ቢሆን እኛን ባለማግባቱ የሚቀርበት ነገር መኖሩ አይጠረጠርም፡፡ ነገር ግን የበለጠ ማሰብ ያለብን በሃይማኖት የማይመስለንን ያንን ሰው ባለማግባታችን የቀረብን ነገር በሙሉ ቢመዘን ከሃይማኖታችን እንደማይበልጥ ነው፡፡

ስለሃይማኖታችን ስንል የከፈልነው ማንኛውም መሥዋዕትነት በፈጣሪ ዘንድ ከቁጥር ውስጥ ይገባና ዋጋ ያሰጠናል፡፡ ለጊዜው ነው እንጂ የቀረብንን ነገር ሁሉ ደግሞ



www.ethiopianorthodox.org



በተሻለ መልኩ በሌላ መንገድ ልናገኘው እንችላለን፡፡ *‹‹ስለስሜም ቤቶችን ወይም ወንድሞችን ወይም እኅቶችን ወይም አባትን ወይም እናትን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን ወይም እርሻን የተወ ሁሉ መቶ እጥፍ ይቀበላል፡፡ የዘላለምንም ሕይወት ይወርሳል፡፡››* (ማቴ፲፱÷፳) የሚለውን ቃል በዚህ መልኩ ለመፈጸም ዕድሉን ካገኘን ደስ ሊለን ይገባል፡፡

በሃይማኖት ለመኖር ሲባል የሚከፈል መሥዋዕትነት አለ፡፡ ከዚያ ውስጥ አንዱ የሚወዱትንም ሰው ሳያገቡ መቅረት ሊሆን ይችላል፡፡ የሚወዱትን ሰው ሳያገቡ መቅረት ድንቅ ነገር አይምሰላችሁ! የዚህ ዓይነት አጋጣሚ ብዙ ጊዜ በሌላም ተራ ምክንያት ሳንወድ በግድ ሊከሠት የሚችል ነው፡፡ ለምሳሌ፡- አንተ ነፍስ እስኪወጣ የምትወዳት ሴት እርሷ አልፈልግህም ወይም አላገባህም ብትልህ ምን ትሆናለህ? ሳታገባት ቀረህ ማለት አይደለምን? ታዲያ በሃይማኖትህ ምክንያት የምትወዳትን ሴት ሳታገባት ስለቀረህ ለምን ታዝናለህ? አንቺስ ብትሆኚ የወደድሽውን ወንድ በሃይማኖቱ ልውጥነት የተነሣ ስላላገባሽው ቀኑን ሙሉ ለምን በትካዜ ትመላለሻለሽ? እንጀራሽንስ ከእንባሽ ጋር ከምን ትበያለሽ? ባይገርማችሁ! በሃይማኖት ልዩነት ብቻ ሳይሆን በሌሎች ልዩ ልዩ ምክንያቶች በዚህ ዓለም ከልብ የወደዱትን ሰው ለማግባት ዕድል የሚያገኙ ጥቂቶች ብቻ ናቸው፡፡

ይህን ሐሳብ ስጽፍ አንድ ያነበብኩት ነገር ትዝ አለኝ፡፡ ጋዜጣው ስምዓ ጽድቅ ሲሆን ታሪኩ በምሥጢሬን ላካፍላችሁ ዓምድ ላይ የወጣ ነው፡፡ ከእስልምና እምነት ተከታይ ወንድ ጋር በፍቅር የወደቀች ወጣት ሴት ክርስቲያን እንዲሆን ለማሳመን ሞክራ አልመጣ ሲላት ‹‹ተይው ሳትሉኝ መፍትሔውን ግለጹልኝ!›› በማለት ጥያቄዋን አቅርባለች፡፡ ምን ታድርግ ግራ ቢገባት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሐቁን መጋፈጥ እንጂ መሸሽ አንችልም፡፡ ሃይማኖትን ላለማጣት የሚከፈለው መሥዋዕትነት እስከዚህ መሆን ካለበት ግድ ነው፡፡ ይህ የብዙዎች ፈተና ነውና፡፡

ይልቅ የሚበጀው አስቀድሞ መጠንቀቅ ነበር፡፡ (ስምዓ ጽድቅ ጥር ፲፰ ፲፱፻፺፯ዓ.ም)

ለስም፣ ለክብር፣ ለዝና፣ ለባል ወይም ለሚስት ወይም ለሌላ ቁሳዊ ነገር ሲባል ሃይማኖትን ቸል ማለት አይገባም፡፡ በአንዳች መጥፎ አጋጣሚ በማያምን ሰው መጠለፍ፣ መደፈር፣ ክብርን ማጣትና መጽነስ ሁሉ ሊከሠት ይችላል፡፡ ቢሆንም ተስፋ በመቁረጥ ስሜት "ከዚህ በኋላ ምን አደርጋለሁ" በማለት በሃይማኖት ከማይመስለን ሰው ጋር በጋብቻ ለመኖር መወሰን ስሕተት ነው፡፡

በአንድ ወቅት የያዕቆብ ልጅ ዲና ተጠልፋና ተደፍራ ነበር፡፡ ቢሆንም ግን ቤተሰቦቿ "ከዚህ በኋላ ምን እናደርጋለን?" በማለት ልጃቸውን እግዚአብሔርን ለማያውቅ ሰው ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ አሳልፈው አልሰጧትም፡፡ (ዘፍ፴፬÷፲፰-፲፱) ሴቲቱ ተጠልፋ በአህዛቡ በሴኬም እጅ ያለች ቢሆንም ቤተሰቦቿ ሃይማኖታቸውን እስከበሩ እንጂ ተስፋ በመቁረጥ "ከዚህ በኋላ ራሱ ያግባት እንጂ ምን ለማድረግ እንችላለን?" ብለው ያለ ምንም ቅደመ ሁኔታ የፈቃድ ቃላቸውን አልሰጡም፡፡ ከዚህ ታሪክ የማያምኑ ሰዎችን እንድናገባ የሚፈትን አጋጣሚ ቢፈጠር እንኳን መውሰድ የሚኖርብን እርምጃ ምን መሆን እንዳለበትና የሚከፈል መሥዋዕትነት መኖሩን እንማራለን፡፡ ለምሳሌ በማያምን ወንድ ድንግልናን ማጣት፣ ማርገዝ፣ ጥልቅ በሆነ የፍቅር ስሜት ውስጥ መግባት ወዘተ ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

ሐዋርያት ስለ ፈጣሪያቸው ስም ሲሉ ያላቸውን ሁሉ ነገር ተዉ፡፡ ከእነርሱ መኻል ትዳሩንም ጨምሮ የተወ አለ፡፡ ስምዖን ይባል የነበረው ቅዱስ ጴጥሮስ ለሐዋርያነት ከመጠራቱ በፊት ባለትዳር እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል፡፡ ‹‹የስምዖንም አማት በብርቱ ንዳድ ታማ ነበር›› ይላልና፡፡ (ሉቃ፬÷፴፰) አማት ከነበረችው ትዳር እንደነበረችው መገንዘብ እንችላለን፡፡ ስለዚህ ጴጥሮስ ፈጣሪውን የበለጠ በማገልገል ደስ ለማሰኘት ትዳሩን ጭምር ትቶ ተከትሎታል ማለት ነው፡፡





የታደሉ በምክክር፣ በፈቃድ፣ ትዳራቸውንም ስለፈጣሪቸው ይተዋሉ፡፡ የተመረጡና ጥቂቶች ደግሞ ያላገቡና ያላጬ ቢሆኑም ስለፈጣሪያቸው ሲሉ በአንድ ልብ ለማገልገል አለማግባትን ይመርጣሉ፤ ይመነኩሳሉም፡፡ ሌሎች ደግሞ ያጬና ሃይማኖታቸውን የሚያጠፉ መስሎ ሲታያቸው የፍቅር ቅርርባቸውን ያቋርጣሉ፡፡ ይህም ራሱን የቻለ መንፈሳዊ ጥንካሬ ነው፡፡

በሙሉ ልብ ፈጣሪያቸውን ለማገልገል ራሳቸውን ከማግባት ያቀቡ፤ የከለከሉ ቅዱሳን ሌላ ለማግባት ተስፋ ሰንቀው አልነበረም፡፡ አንተ ግን ሌላ ለማግባት ተስፋ እያለህ በሃይማኖት የማትመስለኝን ሴት ለምን አላገባም እያልክ ከልብህ ጋር ትሟገታለህ፡፡ ይህችን ትተህ በሃይማኖት የምትመስልህን አግባ ስለተባልክ ጡት እንዳስጣሉት ሕፃን እምርረህ ታለቅሳለህ፡፡ ፈጽሞ ማግባት እንዳትችል ብትደረግ ምን ልትሆን ነበር? በልዩ ልዩ አደጋና በሽታ ለማግባት ያልታደሉ ሰዎች እንዳሉ አታውቅምን? ፈጣሪ ቢፈቅድ ፈጽሞ ማግባት እንዳትችል ሊያደርግህ አይችልምን?

ሐዋርያት ጋብቻን እስከ መተው የደረሱት ስለሚበልጥ የወንጌል አገልግሎት ሲሉ እንጂ ሚስቶቻቸው በሃይማኖት ስላልመሰሏቸው ወይም አግብተው መኖራቸው ኃጢአት ስለሚሆንባቸው አልነበረም፡፡ አንተ ግን የማታምን ሴትን ካላገባሁ ብለህ ሰማይ ትቧጥጣለህ፡፡ ያንተንና የሐዋርያትን ለፈጣሪ የመታዘዝ ልዩነት አየህን?

በሃይማኖት የማትመስልህን ሴት አታግባ ከማለትና አግባ ከማለት የቱ ይከብዳል? በሃይማኖት የማትመስልህን ሴት እንድታገባ ታዘህ ቢሆን ኖሮ ሊከብድህ ይገባ ነበር፡፡ የማትመስልህን አታግባ ማለት ግን ቀላልና ምቹ ራስህንም የሚጠቅም ጎዳና መሆኑን ተገንዝበህ ልትሄድበት ያስፈልጋል፡፡

የምታፈቅራት ሴት ካለች በሃይማኖት ካልመሰለችህ እርሷ አልፈልገህም እስክትልህ መጠበቅ የለብህም፡፡ የሃይማኖት

ልዩነታችሁን ንቀህ አንተ እየቀረብካት እርሷ አልፈልግህም ብላህ ብትለያዩ ትርፉ ትዝብት ነው፡፡ መለያየታችሁ ሳይቀር ሃይማኖትህን በልቡናህ አዋረድካት ማለት ነውና፡፡ ስለዚህ እሷ ስላልፈቀደችህ ብቻ ሳይሆን ብትፈልግህም ሃይማኖቷን ሳታስተካክል ላታገባት ለፈጣሪህ ቃል ልትገባ ይገባሃል፡፡ አንቺም እኅቴ! በምንም ዓይነት ምክንያት ቢሆን በሃይማኖት የማይመስልሽን ሰው ላለማግባት የልብ ውሳኔ ይኑርሽ፡፡ ለፈጣሪ ሲባል የሚወዱትንም ነገር መተው ይገባልና፡፡ ያለዚያማ የሰማዕታት ልጆች መሆናችን በምን ይታወቃል፡፡ ስለፈጣሪ ብሎ የሚወዱትን ነገር ጨክኖ መተው የሰማዕታት ጠባይ ነውና፡፡

ይህን ለመወሰን ልባችን መጨከን ካቃተው ስለፈጣሪያችን ብለህ ምን ልንተው እንችላለን? አባታችን አብርሃም የሚወደውን ልጁን እስከመሠዋት ደርሶ ለፈጣሪው መታዘዙ ለእኛ ምንም አያስተምረንምን? እንዴታ! ማንም ቢሆን ከዚህ ትሑት አባት ስለእግዚአብሔር ብሎ የሚወዱትን ሁሉ እስከማጣት ድረስ የሚከፈል መሥዋዕትነት እንዳለ ሊማር ይገባዋል፡፡ (ዘፍ፳፪÷፩-፲፬)





# ምዕራፍ ሦስት

## ‹‹ከማያምኑ ጋር›› ጋብቻ

## በዘመነ ሕገ ልቦና

የሕገ ልቡና ዘመን የሚባለው በሊቀ ነቢያት በሙሴ አማካኝነት ሕገ ኦሪት ከመሰጠቱ በፊት ያለው ዘመን ነው፡፡ በዚያ ዘመን የነበሩት ሰዎች ከፈጣሪ የተሰጣቸው የተጻፈ ሕግ አልነበራቸውም፡፡ ራሳቸውን ይመሩ የነበረው በልቡናቸው በተፈጥሮ ተቀርጾ በሚገኝ ዕውቀት ነበር፡፡ ይህም ሕገ ልቡና ይባላል፡፡ ስለዚህ ምንም የተጻፈ ነገር ባያገኙም ብዙ ሰዎች በዚህ ሕገ ልቡና እየተመሩ ለፈጣሪያቸው የማይገዙትንና መልካም ነገርን ለማድረግ የማይወዱትን ሰዎች ከማግባት ይቆጠቡ ነበር፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ በሕገ ልቡና ዘመን የነበሩ ሰዎች የነበራቸውን ሃይማኖታዊ ገጽታ ምን እንደሚመስል መዝግቦ ይዟል፡፡ እነዚያንም የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች በሚገባ ያጠናና ያስተዋለ ሰው በሃይማኖት የማይመሳሰሉ ሰዎች ጋብቻ መፈጸማቸው ተገቢ አለመሆኑን ይረዳል፡፡

በዘመናችን ከማያምኑ ጋር ጋብቻ የፈጸሙ ሰዎችን ለምን እንደዚያ እንዳደረጉ ብትጠይቋቸው ከማግባታቸው አስቀድሞ ስለሃይማኖት አብራርቶ ያስተማራቸው ሰው አለማግኘታቸውን በመግለጽ ድርጊታቸውን የሚያስተባብሉ በርካቶችን ታገኛላችሁ፡፡ በእርግጥ አባባላቸው መጠነኛ እውነትነት ይኖረዋል፡፡ ሆኖም ይህ ማስተባበያ ምክንያት ጥፋተኛ ከመሆን አያድናቸውም፡፡ ምክንያቱ ከማያምኑ ጋር እንዳንጋባ በማስረጃ የተደገፈ ጥልቅ ትምህርተ ሃይማኖትን መማር ግድ አይጠበቅብንም፡፡ ምክንያቱም ራሳችንን በሕገ ልቡና ዘመን እንደነበሩትና ምንም የሃይማኖት መጻሕፍትንና ትምህርትን ለማግኘት ዕድል እንደሌላቸው ሰዎች ብንቆጥር እንኳን የማያምኑትን እንዳናገባ ለመወሰን ሕሊናችን ብቻ በቂ ነውና፡፡

www.ethiopianorthodox.org

በዚሁም ላይ ነፍስ የምትድንበትን የሃይማኖት መንገድ አለማፈላለግና ጠይቆ አለመማርም በራሱ ጥፋት መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ በአጭሩ መምህራን ወደ እኛ ባይመጡም እኛ ራሳችን እነርሱን አፈላልገን አለመማራችንም ተጠያቂ ሊያደርገን እንደሚችል ማወቅ አለብን፡፡ ሰው ወደሚሻለውና ወደሚበልጠው ነገር አስተውሎና መርጦ መሄድ የሚችል ፍጥረት ነውና፡፡ ይህን ባለማድረጉ ብቻ እንኳን ከተጠያቂነት አይድንም፡፡ አውቆ ያጠፋ ‹‹እጅግ ይገረፋል›› ሳያቅ ያጠፋ ደግሞ ‹‹በጥቂቱ›› ይገረፋልና፡፡ (ሉቃ፲፪፥፵፯-፵፰) ያስተማረን አካል ኖረም አልኖረ ስናጠፋ በጥፋታችን ከመጠየቅ ልንድን አንችልም፡፡ ኃላፊነት ተሰጥቶት ሳያስተምር የቀረም እንዲሁ ተጠያቂ መሆኑ ጥርጥር የሌለው ነገር ነው፡፡

በሕገ ልቡና ተመርተው ከማያምኑ ሰዎች ጋር ላለመጋባት የተጠነቀቁ ሰዎች ታሪክ ምንም እንኳን የሰው ልጅ ትምህርተ ሃይማኖትን የሚያገኝበት ዕድል ባያገኝም ከማያምኑና በእምነት ከማይመስሉት ሰዎች መኻል አጭቶ ማግባት እንደሌለበት ያስተምረናል፡፡ የሰው ልጅ ፈቃደኛ ቢሆን፣ ቢያስተውልና ልቡናውን አሳውሮ ስሜቱን ብቻ ባይከተል በሃይማኖት ተለያይቶ መጋባት ተገቢ አለመሆኑን ለመረዳት አይቸገርም፡፡ በሕገ ልቡና ዘመን የነበሩ አበው ያደረጉትም እንደዚሁ ነው፡፡

የአበው ኑሮና ምክር ለኛ መልካም መመሪያ ነው፡፡ በሕገ ልቡና ይኖሩ የነበሩ ቅዱሳን አበው ቤተሰቦቻቸውን እንደ ካህንና ነቢይ በመሆን አስተዳድረዋል፡፡ ስለሆነም በዘመኑ የተጻፈ መንፈሳዊ ሕግ ስላልነበረ መመሪያ የሚፈልቀው ከነዚህ ቅዱሳን አበው የሕይወት ምሳሌነት ነበር፡፡ እነዚህ አባቶች ከማያምኑ ጋር መጋባትንም በተመለከተ የነበራቸው አቋም ግልጽና ጥብቅ ነበር፡፡

ለምሳሌ፡- አባታችን አብርሃም ልጁን ሊድር በፈለገ ጊዜ ሎሌውን እርሱ ከተወለደባትና ካደገባት አገር ለልጁ ሚስት ይዞለት እንዲመጣ የላከው ልጁን በሃይማኖት ከማይመስሉት





ሰዎች ወገን ላለማጋባት ሲል ነው፡፡ ይህም ዘርንና አጥንትን መቁጠር ሳይሆን ለሃይማኖት ቅድሚያ መስጠትን ያስተምራል፡፡ አብርሃም እውነተኛ ፈጣሪውን መከተል ሲጀምር ከሌላው የዓለም ክፍል ይልቅ ስለአብርሃም አምላክ በቅድሚያ የሰሙና የተሳቡ በአብርሃም ዙሪያ የነበሩ ወገኖቹ ነበሩና፡፡ በእርግጥም ለይስሐቅ ሚስት የሆነችው ርብቃና ቤተሰቦቿ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሆነው መገኘታቸው የተሰጠው ማብራሪያ ልክ እንደሆነ ያረጋግጣል፡፡ ስለዚህ አብርሃም ለልጁ የተመኘው ሁሉ ተሳክቶለታል፡፡ (ዘፍ፳፬፥፩-፷፯)

የርብቃ ቤተሰቦች ሃይማኖተኛነት ሴት ልጃቸውን የጠየቃቸውን ሽማግሌ (የአብርሃም ሎሌ) ሳያሳፍሩ «ነገሩ ከእግዚአብሔር ዘንድ መጥቶአል፡፡ ክፉም በጎም ልንመልስልህ አንችልም፡፡» በማለታቸው ይታወቃል፡፡ ቀጥለውም «ርብቃ እነኋት በፊትህ ናት፡፡ ይዘሃት ሂድ፥ እግዚአብሔር እንደተናገረ ለአብርሃም ልጅ ሚስት ትሁን፡፡» ብለዋል፡፡ (ዘፍ፳፬፥፶-፶፩)

በተመሳሳይ መንገድ ይስሐቅ ደግሞ ልጁ ያዕቆብን እንዲህ ብሎ አዞታል፡- «ከከነዓን ሴቶች ልጆች አታግባ፡፡» (ዘፍ፳፰፥፩) ያዕቆብም አባቱ እንዳዘዘው አድርጓል፡፡ ዔሳው የተባለው የይስሐቅ ልጅ ግን ሆን ብሎ አባቱ የማይወደውን ሥራ ለመሥራትና አባቱን ለማሳዘን ፈልጎ ከከነዓን ሴቶች ልጆች ጋር ተጋብቷል፡፡ (ዘፍ፳፰፥፮-፱)

በዘመኑ ለነበሩ ለቅዱሳን አበው ቃል አለመታዘዝ ለነቢይና ለካህን ቃል ያለመታዘዝ ያህል ነበር፡፡ ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ከማያምኑ ጋር መጋባትን አስመልክቶ የምትሰጠውን ትምህርት ሰምተው የሚታዘዙ አባታቸውን የሰሙ ይስሐቅንና ያዕቆብን ይመስላሉ፡፡ ከማያምኑ ጋር የሚጋቡ ደግሞ ዔሳውን ይመስላሉ፡፡ ከዚህም የተነሣ ዔሳው ያልተባረከ ጎስቋላና ሰላም የሌለው ሰው ሲሆን ይስሐቅና ያዕቆብ ግን አርአያ የሚሆኑ መንፈሳዊ አባቶች ለመሆን በቅተዋል፡፡

በሕገ ልቡና ዘመን የሚኖሩ ደቂቀ ሴት (ሴት በመባል የሚታወቀው የአዳም ልጅ ወገኖች) ሕገ ልቡናን ከሚጥሱ ከቃየል ዘሮች ጋር ሳይጋቡ ራሳቸውን ጠብቀው ለብዙ ዘመን ኖረዋል። በኋላ ግን «የእግዚአብሔር ልጆች» የተባሉ የሴት ዘሮች "የሰው ልጆች" ከተባሉት የቃየል ወገኖች "ሚስቶችን ለራሳቸው በመውሰዳቸው" እግዚአብሔር ተቆጥቶ ዓለም እስክትጠፋ ድረስ ታላቅ መቅሠፍት ማምጣቱ ተመዝግቧል። (ዘፍ፮÷፩-፳፪፤ ፯÷፩-፳፬፤ ፰÷፩-፳፪) ይህም ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላቸው ሰዎች እግዚአብሔርን ከማይፈሩ ሰዎች ጋር በጋብቻ አንድ መሆናቸው ለራሳቸው ኑሮ ጥሩ ካለመሆኑም ባሻገር ምን ያህል እግዚአብሔርን እንደሚያሳዝነው ያሳያል።

ዳግመኛም ከዚያው ከሕገ ልቦና ዘመን ሳንወጣ የያዕቆብ ልጆችን ታሪክ እናነባለን። አብርሃም አባታችን በእግዚአብሔር አመነ፤ ለማመኑም ምልክት ይሆን ዘንድ እርሱና ቤተሰቡ እንዲገረዙ ታዘዘ። እርሱም በታላቅ ትጋት ይህንን አደረገ። የአብርሃም የልጁ ልጅ ያዕቆብ እንደ አባቱ እግዚአብሔርን የሚያምን ስለነበር ከነልጆቹ ግዝረትን ፈጽሟል። ሆኖም ሴኬም የተባለ አህዛባዊ ወጣት የያዕቆብን ሴት ልጅ ለጋብቻ በጠየቀ ጊዜ የቤተሰቦቿ ምላሽ ምን እንደነበረ ታውቃለህን?

የያዕቆብ ልጆች «እኅታችንን ላልተገረዘ ሰው ለመስጠት ይህንን ነገር እናደርገው ዘንድ አይቻለንም» ብለው ግልጽ መልስ ሰጥተዋል። ምክንያቱንም ሲገልጹ "ይህ ነውር ይሆንብናልና" ብለዋል። (ዘፍ፴፬÷፲፬) ከማያምኑ ጋር መጋባት ነውርነቱ ለተጋቢዎቹ ብቻ ሳይሆን ለቤተሰቦቻቸው ሁሉ ነው። ይህም የዲና ቤተሰቦች "ነውር ይሆንብናልና" ብለው በሰጡት የመልስ ቃል ይታወቃል። (ዘፍ፴፬÷፲፬)

አንቺ ሴት ከማያምን ሰው ጋር ብትጋቢ «ነውር» እንደሚሆንብሽ አታውቂምን? «ነውረኛ» ሆነሽ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት አትችዪም። አንተስ ክርስቲያን





ከማታምን ሴት ጋር ለምን ትጋባለህ? የአህዛብንና የመናፍቃን ሴቶችን ብብትስ ለምን ታቅፋለህ? ይህን ነውርህን ወዴት ልትሸከመው ትችላለህ? «ነውረኛ» ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንደማይገባ ከቅዱስ መጽሐፍ አላነበብክምን? (ራእ፳፩÷፳፯)

# ምዕራፍ አራት
# ‹‹ከማያምኑ ጋር›› ጋብቻ
# በዘመነ ኦሪት

ከዘመነ ሕገ ልቦና ወደ ዘመነ ኦሪት ስናልፍ ደግሞ የሚያምኑ ከማያምኑ ሰዎች ጋር ጋብቻ እንዳይፈጽሙ ሕግ ሆኖ መቀመጡን በግልጽ እናነባለን። ሕገ ኦሪት የሚባለው በነቢዩ ሙሴ አማካኝነት የኦሪት ሕግ ከተሰጠ ወዲህ እስከ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት ያለው ዘመን ነው። እግዚአብሔር እስራኤልን በሙሴ አማካኝነት እየመራ ወደ አህዛብ ሀገር ሲያስገባቸው የመጀመሪያ ማስጠንቀቂያው ከአህዛብ ጋር ቃል ኪዳን እንዳያደርጉና ጋብቻ እንዳይፈጽሙ ነበር።

ከማያምኑ ጋር ጋብቻን የሚከለክለው ትእዛዝም እንዲህ የሚል ነበር። “ከእነርሱም (ከአህዛብ) ጋር ቃል ኪዳን አታድርግ . . ከእነርሱም ጋር አትጋባ። ሴት ልጅህን ለወንድ ልጁ አትስጥ ሴት ልጁንም ለወንድ ልጅህ አትውሰድ። ሌሎችንም አማልክት (ጣዖታትን) እንዲያመልክ ልጅህን ያስታልና የእግዚአብሔር ቁጣ ይነድባችኋል ፈጥኖም ያጠፋችኋል።” (ዘዳ፯÷፪-፬)

ይህ ትእዛዝ ከማያምኑ ጋር መጋባትን የሚከለክል ብቻ ሳይሆን ሌሎች ሁለት ዓበይት ነጥቦችን አያይዞ አንሥቷል። ይኸውም አንደኛው ከማያምኑ ጋር መጋባት ሃይማኖትን እንደሚያቀዘቅዝና ወደ ክህደት እንደሚያደርስ “ሌሎችንም አማልክት እንዲያመልክ ልጅህን ያስታልና” በማለት የጠቀሰው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከማያምኑ ጋር በጋብቻ አንድ መሆን የሚያስከትለውን ቅጣት ለመግለጽ “የእግዚአብሔርም ቁጣ ይነድድባችኋል ፈጥኖም ያጠፋችኋል።” በማለት ያሰፈረው ነው።

ከማያምኑ ጋር መጋባት ፈጣሪህን እንዴት እንደሚያስቆጣና በሥጋና በነፍስ “ጥፋት” ሊያመጣ መቻሉን ተመለከትክን?





ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ያለውን ይህን የአምላክ ትእዛዝ ለእስራኤላዊያን የተቀበለ ነቢዩ ሙሴ ራሱ ከማያምኑ ጋር ጋብቻ ፈጽሟል ማለት ሐሜት ነው። አንዳንዶች ሙሴ ኢትዮጵያዊቷን ሴት በማግባቱ እኅቱና ወንድሙ እንደተቃወሙት የሚተርከውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በመጥቀስ ሙሴን መክሰስ ያምራቸዋል። (ዘኍ፲፪÷፩-፲፮) በዚህም አካሄዳቸው ኢትዮጵያን ከአሕዛብ ጎራ ሊያሰልፏት ይጥራሉ። አለማወቃቸው እንጂ ኢትዮጵያ እግዚአብሔርን በማመን ከእስራኤል ትቀድማለች እንጂ አትከተልም። ለዚህም ነው ሙሴ ኢትዮጵያዊቷን ያገባው። የገዛ ቤተሰቦቹ አሮንና ማርያም ቢቃወሙትም እግዚአብሔር ግን ፈረደባቸው። ሙሴ ያላመነችውን በማግባት ጥፋት ሠርቶ ቢሆን ኖሮ ፈጣሪ አያግዝለትም ነበር። እግዚአብሔር ኢትዮጵያን በሃይማኖት ከእስራኤል አስበልጦ ‹‹እናንተ እስራኤላውያን ለእኔ እንደ ኢትዮጲያውያን አይደላችሁምን?›› ማለቱን አንዘንጋ! (አሞፅ፱÷፯) ስለዚህ ‹‹ከአሕዛብ ጋር አትጋቡ›› እስራኤላውያንን ያስተማረ ሙሴ ኢትዮጵያዊቷን ምእመን አገባ እንጂ ከአሕዛብ ጋር ተጋባ አይባልም።

እውነት ለመናገር አንተ ከጠቢቡ ሰሎሞን አትበልጥም። ምንም ዐዋቂና በመንፈሳዊ ሕይወትህ ጠንካራ ዓይነት ሰው ብትሆን ከማያምኑ ጋር በፍቅር መተሳሰርህ ሳያሳስትህ አይቀርም። ጠቢቡ ሰሎሞን ቤተ መቅደስ በሠራበት እጁ ቤተ ጣዖት እስከ መሥራትና ጣዖት እስከማምለክ የደረሰው ከማያምኑ ሰዎች ጋር በነበረው ጋብቻና የፍቅር ግንኙነት ነበር። (፩ነገ፲፩÷፩-፲፫)

እንደ ጠቢቡ ሰሎሞን ሁሉ የሶምሶንም ልብ እውነተኛ ሃይማኖት በሌላት በደሊላ ፍቅር በመማረኩ የእግዚአብሔር ቁጣ እንዴት እንደነደደበት ተጽፏል። (መሳ፲፮÷፬-፴፩) ይህን ሁሉ ያስተዋሉ ሰዎች ራሳቸውን በማያምኑ ሰዎች ከሚመጣ የእግዚአብሔር ቁጣ ጠብቀው ኖረዋል። ነገር ግን ዘመናት እያለፉ



www.ethiopianorthodox.org

በሄዱ ቁጥር ምእመናን ሃይማኖት ከሌላቸው ከከሃዲያንና ከመናፍቃን ጋር ጋብቻ እስከ መፈጸም የሚያደርስ ቅርርብ ሲፈጥሩና ሲጋቡ መመልከት እየተለመደ መጥቷል፡፡ አይሁድ ግን ከተሰጣቸው ሕግ በመነሣት እስከ ሐዲስ ኪዳን መግቢያ ድረስ ከአህዛብ ጋር እንኳን ጋብቻ ይቅርና ሌላም ዓይነት ሃይማኖትን የሚያቀዘቅዝ ወደ ክህደት የሚወስድ ቅርርብና ትብብር እንዳልነበራቸው የሚስረዳ ቃል እናገኛለን፡፡ ቃሉም «አይሁድ ከሳምራውያን ጋር አይተባበሩም ነበርና» ይለናል፡፡ (ዮሐ፬÷፱)

የእስራኤል ሕዝቦች ከማያምኑ፣ ከአህዛብ ጋር ወይም እንደ መጽሐፉ አገላለጥ ከእንግዳ ሴቶች ጋር በመጋባታቸው ምክንያት የደረሰባቸውን ለማወቅ መጽሐፈ ዕዝራን ማንበብ በእጅጉ ይጠቅማል፡፡ በተለይ ደግሞ በምዕራፍ ዘጠኝና ዐሥር ላይ ከአህዛብ ጋር የተጋቡት ሰዎች በልዩ ልዩ መንገድ ተለይተው እንደታወቁ ከእነዚያም ውስጥ ከካህናቱም ወገን እንደነበሩበት ይተርክልናል፡፡ ቀጥሎም ከእንግዳ ሴቶች ጋር የተጋቡ እንዲፋቱ መደረጉንና ይህንንም የተቃወሙ አንዳንዶች እንደነበሩ ያወሳል፡፡ ፈቃደኞቹ ደግሞ እንዴት በዕዝራ አማካኝነት ኃጢአታቸውን እንደተናዘዙና ዐመፀኞቹን ለመለየት መማማላቸውን ጨምሮ ያስነብበናል፡፡ (ዕዝ፱÷፩-፲፭፤ ፲÷፩-፵፬)

ከማያምኑ ጋር ከተጋቡ ወይም ተዋደው ከተቀራረቡ በኋላ ይህን ሕግ ተግባራዊ ለማድረግ ትዕግሥት፣ ጥረትና ብዙ ጊዜ ይጠይቃል፡፡ በእርግጥ የእስራኤል ጉባኤ እንደተናገረው ይህ ‹‹የአንድ ወይም የሁለት ቀን ሥራ አይደለምና፡፡›› (ዕዝ፲÷፲፫) ስለዚህ ከሁሉም ይልቅ የሚበጀው ከማያምኑ ጋር ወደ ጋብቻ የሚወስድ ግንኙነት እንዳይኖረን ከወዲሁ መጠንቀቅ ነው፡፡



www.ethiopianorthodox.org



# ምዕራፍ አምስት
# ‹‹ከማያምኑ ጋር›› ጋብቻ
# በዘመነ ወንጌል

እስከዚህ ድረስ የቀረቡት ማስረጃዎች በሕገ ልቡናና በሕገ ኦሪት የተጠቀሱ ነበሩ፡፡ በአዲስ ኪዳንም ከማያምኑ ጋር ጋብቻ መፈጸም ተገቢ አለመሆኑን የሚያስረዱ በርካታ ጥቅሶች ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በቆሮንቶስ መልእክቱ ‹‹ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ፡፡›› ብሏል፡፡ (፪ቆሮ፮÷፲፬)

«አትጠመዱ» የሚለው ቃል እጅግ ምሥጢራዊ ነው፡፡ ይህም በግልጽ ከማያምኑ ጋር አትጋቡ በሚል ይተረጎማል፡፡ እንደሚታወቀው «መጥመድ» የሚለው ቃል እንደአገባቡ ብዙ ፍቺ ቢኖረውም በዋናነት ሁለት በሬዎችን ለእርሻ ሥራ ማዘጋጀትን ያሳያል፡፡ ይኸውም ለማረስ፣ ለመዝራትና ፍሬ ለማፍራት ነው፡፡ ስለዚህ «አትጠመዱ» የሚለው ቃል ጋብቻን ያመለክታል፡፡

በሬዎችን እንደ መጥመድ ጋብቻም ሁለት ሰዎች ማለትም ወንድና ሴት (ባልና ሚስት) በሩካቤ አንድ ለመሆንና ዘር ለመተካት የሚጠመዱበት የውዴታ፣ የሃይማኖት፣ የተስፋና የፍቅር ገመድ ነውና፡፡ ባልየው እንደ ገበሬ ሲሆን ዘሩም የወንድ ዘር ነው፡፡ የሴቲቱ ማኅፀን ደግሞ የሕይወት እርሻ ነው፡፡ በሩካቤ አንድ መሆን ደግሞ «ብዙ ተባዙ» የሚለውን የአምላክ ቃል ለመፈጸም የሚካሄድ የግብርና ሥራ ነው፡፡ በዚህ ምሥጢር መሠረት «ከማያምኑ ጋር አትጠመዱ» ማለት ጋብቻ አትፈጽሙ ማለት ነው፡፡

በዓለም እስካለን ድረስ ከማያምኑ ሰዎች ጋር በብዙ መንገድ ልንገናኝ እንችላለን፡፡ ከማያምኑ ጋር በአንድ አካባቢ መኖር፣ በአንድ መሥሪያ ቤት መሥራት፣ በአንድ ቦታ መዝናናት፣ በአንድ ትምህርት ቤት መማር ያለ ነገር ነው፡፡ በአንድ ዕድር

በአንድ ዕቁብ መጠቀም ሲሠራበት የኖረ በወንጌልም የተደገፈ ነው። ነገር ግን ከእነርሱ ጋር በጋብቻ መጣመር ሐዋርያው እንደተናገረው "የማያመች አካሄድ" ነው።

ሰውን ከበሬ ጋር ብንጠምደው ለማረስ ይመቻልን? ወይስ በሬን ከሌላ እንስሳ ጋር ለምሳሌ ከአህያ፣ ከፈረስ ወይም ከበቅሎ ጋር ቢጠምዱት ለማረስ ይመቻልን? እውነት ለመናገር በሬን እንኳን ከሌላ እንስሳ ጋር ይቅርና አባት በሬን ከወይፈን ጋር ብንጠምደው እንኳን ወይፈኑ ይገራ እንደሆነ ነው እንጂ ለማረስ አይመችም። እንደዚሁም ሁሉ ከማያምኑ ጋር መጋባትም "የሚመች አካሄድ" አይደለም። የሚያምን ከማያምን ጋር መጋባት ለማረስ ብሎ በሬን ከፈረስ ወይም ከበቅሎ ወይም ከሌላ እንስሳ ጋር እንደመጥመድ ይቆጠራል።

የጋብቻ ጉዞ የሚመች መሆን አለበት። በመጽሐፍ ቅዱስ ቅድስት ሥላሴ "ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም።" በማለት ለአዳም "የሚመቸውን ረዳት" ሔዋንን ፈጥረው የሰጡት ስለዚህ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ «በማይመች አካሄድ አትጠመዱ» ሲል በኦሪት "የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት" በማለት ሥሉስ ቅዱስ ከተናገሩት ቃል ጋር በማያያዝ ስለ ጋብቻ ለመናገር ፈልጎ መሆኑን ማስተዋል ይገባል። በኦሪት ዘፍጥረት ሥላሴ ‹‹የምትመቸውን›› ሲሉ የተናገሩት ቃልና ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹በማያመች›› በማለት የተናገረው ቃል የአንድ ግሥ ዝርዝር መሆናቸውን አስተውል። ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ቃል የተናገረው ስለ ጋብቻ ነው ብሎ ማሰር አስተዋይነት ነው።

ስለዚህ ከማያምኑ ጋር መጋባት የሚመች አይደለምና መሞከርም የለበትም። አለመመቸቱም ለነፍስ ነው እንጂ ለሥጋ አይደለም። ለነፍስ ያልተመቸ ነገር ደግሞ ለሥጋም አይመችም። ለሥጋ ቢመችም እንኳን ለነፍስ እስካልበጀ ድረስ ለሥጋ መመቸቱ ብቻ ከቁጥር የሚገባ ነገር አይደለም። ‹‹ሰው ዓለምን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱን ግን ቢከስር ምን ይጠቅመዋል›› (ማቴ፲፮÷፳፮)





ሐዋርያው "ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ" ካለ በኋላ አያይዞ የማያምኑና የሚያምኑ ሰዎችን ልዩነት ሲያስረዳ "ጽድቅ ከዓመፅ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና? ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው? ክርስቶስ ከቤልሆር (ከሰይጣን) ጋር ምን መስማማት አለው? ወይስ የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው? የእግዚአብሔር ታቦትንስ በጣዖት ቤት ውስጥ የሚያኖር ማን ነው?" ይለናል። (፪ቆሮ፮÷፲፬÷፲፮)

ከማያምኑ ጋር መጋባት ታቦትን በጣዖት ቤት እንደማኖር ነው። በተለይ ቅዱስ ጳውሎስ ከተናገረው ‹‹የእግዚአብሔር ታቦትንስ በጣዖት ቤት ውስጥ የሚያኖር ማን ነው?›› የሚለውን ስንመለከት ከማያምኑ ጋር ጋብቻ ተገቢ አለመሆኑን ለማሳየት ተጨማሪ ማስረጃ ይሆነናል። መቼም አገላለጹ ምሳሌያዊ እንደሆነና ከማያምኑ ጋር ሲኖረን ስለሚገባው ግንኙነት እየተናገረ እንደሆነ ግልጽ ነው። ታቦትን በጣዖት ቤት የሚያሳድር ሳይሆን ‹‹የሚያኖር›› ማን ነው ይላል። ይህ ቃል ደግሞ መግለጽ የተፈለገው ስለ ትዳር እንጂ ስለ ጉርብትና ወይም ሌላ ዓይነት ጓደኝነት አለመሆኑን ያስረዳናል። ቃሉ ‹‹የሚያኖር›› ይላልና። በአንድ ቤት መኖር ደግሞ ትዳርን እንጂ ጉርብትናን ወይም ጓደኝነትን አያሳይም። ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ ከፍ ብሎ የተጠቀሰውን ኃይለ ቃል የተናገረው ስለ ጋብቻ መሆኑን ማስተዋል ይገባል።

ጋብቻ በሁሉም ረገድ አብሮ መኖር ነው። በቤት ከሚኖሩት ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዙት ባልና ሚስት ናቸው። አንድ ሰው ቤቴ ሲል ‹‹ትዳሬ›› ማለቱ ነው። ሚስቱ ለማለት ባለቤቱ እንደምንለው ማለት ነው። ይህም ‹‹እኔና ቤቴ እግዚአብሔርን እናመልካለን›› ከሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ጋር ይዛመዳል። እረ ለመሆኑ ባልና ሚስት የተለያየ ሃይማኖት ይዘው ሳለ እንደ ነቢዩ ኢያሱ ‹‹እኔና ቤቴ እግዚአብሔርን እናመልካለን›› ለማለት እንዴት ይችላሉ? (ኢያ፳፬÷፲፰)

ሌላውና የመጨረሻው የሐዲስ ኪዳን ኃይለ ቃል ከማያምኑ ጋር መጋባት እንደማይገባ በግልጽ የተነገረ ነው፡፡ ይኸውም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ባል ስለሞተባት ሴት በተናገረበት አንቀጽ የገለጠው ሲሆን ቃሉም እንዲህ የሚል ነው፡- "ሴት ባልዋ በሕይወት ሳለ የታሰረች ናት፤ ባልዋ ቢሞት ግን በጌታ ይሁን እንጂ የወደደችውን ልታገባ ነጻነት አላት፡፡" (፩ቆሮ፯÷፴፱)

ከላይ የተጠቀሰው የቅዱስ ጳውሎስ ቃል ባሏ የሞተባትን ሴት "የወደደችውን" እንድታገባ ነጻነት ያጎናጽፋል፡፡ ነገር ግን "የወደደችውን" የሚለውን ቃል ብቻ ይዛ በሃይማኖት የማይመስላትን ለማግባት ልቧ እንዳይከጅል ደግሞ "በጌታ ይሁን እንጂ" በማለት በሩን ይዘጋባታል፡፡

"በጌታ ይሁን እንጂ" ማለት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ የተጠመቀ፣ ሕጉንና ሥርዓቱን የሚጠብቅ፣ በአጠቃላይ ሃይማኖትና ምግባር ያለው እውነተኛ ክርስቲያን ይሁን እንጂ የወደደችውን መርጣ ልታገባ ነጻነት አላት ማለት ነው፡፡

የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ "በጌታ ይሁን እንጂ" የሚለውን ቃል በግዕዙ ብናነበው ግልጽ ከመሆኑ የተነሣ ይህን ያህል ማብራሪያ እንኳን አይፈልግም፡፡ የግዕዙ ሐረግ "*ወባሕቱ እምእመናን*" ይላል፡፡ ይህም ባል የሞተባቷ ሴት መርጣ ስታገባ «ከምእመናን ወገን ይሁን» ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ የሐዋሪያው ቃል በመነሣት አንድ ምእመን መርጦ ማግባት የሚችለው ከምእመናት ወገን የሆነች ሴትን ብቻ ነው፡፡

ይህ የሐዋርያው ቃል ባል ለሞተባት ሴት ብቻ ሳይሆን ላላገቡና ማግባት ለሚፈልጉ ወጣቶች ሁሉ ይሠራል፡፡ በተጨማሪም ለሴቲቱ ብቻ ሳይሆን ለወንዱም ቢሆን ድንጋጌው አይለወጥም፡፡ ሰው ሁሉ "በጌታ ይሁን እንጂ" የወደደውን የማግባት ነጻነት አለውና፡፡

ባል የሞተባትን ሴት ነጥሎ በመጥቀስ ከሚያምኑ ወገን ይሁን እንጂ የወደደችውን ለማግባት ነጻነት አላት ማለቱ ደግሞ





ሌላ ነገር እንድናስተውል ግድ ይለናል፡፡ ይኸውም ባል የሞታት ሴት «ከዚህ በኋላ ማን ያገባኛል?» በሚል ቀቢጸ ተስፋ ተይዛ የመጣላትን ባል ‹‹ሃይማኖትህ ምንድር ነው?›› ብላ ሳትጠይቅ ለማግባት እንዳትሽቀዳደም ማስጠንቀቁ ነው፡፡

ሰዎች የማግባት ዕድላቸው ጠባብ እንደሆነ እያሰቡና ተስፋ እየቆረጡ በመጡ ቁጥር «እኔን ደግሞ ማን መራጭ አደረገኝ!» እያሉ የመጣውን ማንኛውንም ዓይነት ሰው ተቀብሎ ለማግባት ራሳቸውን ያዘጋጃሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ሃይማኖት የሌለውንም ሰው ቢሆን ከማግባት አይመለሱም፡፡ ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ ባል የሞታትን ሴት ሲያስጠነቅቅ «በጌታ ይሁን እንጂ›› የወደደችውን መርጣ ማግባት ትችላለች አለ፡፡ ባል የሞተባትና መርጦ ለማግባት ጠባብ ዕድል ያላት ሴት በሃይማኖት የማይመስላትን እንዳታገባ ይህ ዓይነት ገደብ ከተጣለባት በሌሎች ክርስቲያኖች ላይ ሕጉ የበለጠ የሚጠነክር መሆኑን መገመት ይቻላል፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

## ‹‹ከማያምኑ ጋር›› ስለመጋባት

## በቀኖና ቤተ ክርስቲያን የተጻፈ

እስካሁን ስናይ የመጣነው ከሕገ ልቡና በመነሣት እስከ ሕገ ወንጌል ያለውን ነበር። አሁን ደግሞ ከማያምኑ ጋር ስለመጋባት ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ምን እንደሚል እንመለከታለን።

የማያምንን ስለማግባት ፍትሐ ነገሥት መንፈሳዊ እንዲህ ይላል፦ *«ብእሲት ማእምንት ለእመ ተወሰበት ለብእሲ ኢአማኒ ትሰደድ እምጉባኤ። ወለእመ ነስሐት ወተከልአት እምኔሁ ይትወከፍዋ በከመ ይትመየጥ ከሃዲ እም ክህደቱ። ወእምድኅረ ነጽሐት ይደልዋ ተደምሮ ምስለ ምእምናን ወየሃብዋ ቁርባነ።»*

በላይኛው አንቀጽ የሰፈረው የግዕዝ ገጸ ንባብ ነጠላ ትርጓሜ እንደሚከተለው ነው። «ያመነች ሴት ያላመነውን ወንድ ብታገባ ከምእመናን ትለይ። ከሱ ተለይታ ንስሐ ብትገባ ከክህደቱ እንደተመለሰ ሰው አድርገው ይቀበሏት። በንስሐ ሥርዓት ከነጻች በኋላ ከምእመናን ጋር ትቀላቀል። ሥጋውንና ደሙንም ያቀብሏት።» (ፍት መን አንቌ፬)

"ሃይማኖትን የካዱ የመናፍቃንን ሥራቸውን ሁሉ፤ መለየትን ሁሉ፤ ሕግ መለወጥንም እንጸየፋለን። እነርሱ በእኛ ዘንድ የተጠሉ ናቸውና።" በማለት እንኳን በጋብቻ ልንተባበራቸው ይቅርና ክፉ ሥራቸውን ሁሉ ማውገዝ እንዳለብን ሐዋርያት በጻፉት አመክንዮ መክረዋል። (አመክንዮ ዘሐዋርያት ፳÷፳) በሃይማኖት የማይመስሉንን ማግባት ለሃይማኖታቸው ዕውቅና እንደመስጠት ይቆጠራል።

አስገድደው፣ አባብለው፣ አታለውና በልዩ ልዩ መንገድ ገፋፍተው ምእመናንን ከማያምኑ ሰዎች ጋር እንዲጋቡ ስለሚያደርጉ ሰዎች ደግሞ እንዲህ ተጽፏል። «አማኒ (ክርስቲያን ወላጅ፣ አሳዳጊ ወይም ጠባቂ) ኢአማኒ እንደሆነ ሳያውቁ ወይም



www.ethiopianorthodox.org



ሳይወዱ እኅቱን ወይም ልጁን ለማያምን ሰው ቢያጋባ ከጉባኤ (ከቤተ ክርስቲያን) ይለይ። ከምእመናን አንድነትም ይከልከል። እርሷን ግን አይለይዋት። እርሱ (ወላጅ፣ አሳዳጊ ወይም ጠባቂ) ቢመለስ ግን ከባሏም እንድትለይ ቢያደርጋት እንደ ዓቅሙ ቀኖናውን ይስጡት። ከዚያ በኋላ ይቅር ይበሉት።» (ፍት መን አንቌ፬)

ትዳር ንግድ በሆነበትና የትዳር አጋርን ለማግኘት የሚደረግ ሩጫ በ«ፖስታ»፣ በ«ስልክ»፣ በ«ኢ-ሜይል»ና በልዩ ልዩ መገናኛ ብዙኀን በሆነበት በዚህ ዘመን ሃይማኖታቸውን ሳይተዋወቁና ሳይጠያየቁ የመጋባት አደጋ በዝቷል። ለዚህ ደግሞ የባልና የሚስት አማጮች፣ የአጋቢዎችና የአስተዋዋቂዎች ድርሻ ከፍተኛ ነው። ከላይ በተጠቀሰው የፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ መሠረት ልጅና እኅትን ብቻ ሳይሆን ጓደኞቻችንንም ቢሆኑ በሥጋዊ ሐሳብ የጠቀምናቸውና ዕድላቸውን ያሰፋንላቸው መስሎን ከማያምን ሰው ጋር ጋብቻ እንዲመሠርቱ ግፊት ብናደርግባቸው ተጠያቂዎች እንሆናለን። ለሃይማኖት ግድ ሳይኖራቸው ቪዛ ስለማግኘት፣ ስለ ኑሮ መሻሻልና፣ ስለትምህርት ዕድል ብቻ እያሰቡ በሃይማኖት አንድ ያልሆኑ ሰዎች እንዲጋቡ ግፊት የሚሳድሩ ሰዎች ብዙ ናቸው።

በሃይማኖት ትምህርት ቅርብ የሆነ የሥጋ ዝምድና ያላቸው ሰዎች መጋባታቸው ሕገ ወጥ ድርጊት መሆኑ በሚገባ ይታወቃል። የቅርብ ዘመዳሞችን ጋብቻ ዘመናዊ ሳይንስም ቢሆን ከስነ ልቡናና ከሚወልዱት ልጅ ተፈጥሮአዊ የጤና አጠባበቅ አንጻር በማየትና በሌሎችም ምክንያቶች ይቃወመዋል። ስለዚህ ወንድምና እኅት እንኳን ተጋብተው ሊኖሩ ይቅርና ለአንድ ዕለት እንኳን በዝሙት ቢወድቁ እጅግ አሳፋሪ ነው። አባት ከልጁ ጋር የሚፈጽመው ሩካቤም እንዲሁ እጅግ ነውር ነው። ይህ እንዳለ ሆኖ ጉዳዩን በትምህርተ ሃይማኖት ለሚመለከተው ሰው ከዚህ በላይ የሚከፋው ግን ከማያምኑ ሰዎች ጋር መጋባት ነው።

ይህን የሚስረዳ የጻድቅ ሰው ታሪክ በአዋልድ መጻሕፍት ተጽፎ ይገኛል፡፡

ዲሜጥሮስ የተባለ ሰው አህዛብ በሚበዙበት ሀገር ከቤተሰቦቹ ጋር ይኖር ነበር፡፡ በዚያ ከአጎቱ ልጅ በቀር እንደ እርሱ ለጋብቻ የደረሰች ክርስቲያን ሴት አልነበረችም፡፡ በመጨረሻም ወላጆቻቸው በዚህ ሀገር ለልጆቻችን የሚሆኑ ወንድና ሴት ክርስቲያኖች የሉም፡፡ ስለዚህ ልጆቻችን በሃይማኖት ከማይመስሏቸው ጋር ተቀራርበው ኃጢአት ሳይሠሩ ሁለቱን እናጋባቸው ብለው መከሩ፡፡ ምንም ዘመዳሞች ቢሆኑ "ሕንጻ ሃይማኖት ከሚፈርስ ሕንጻ ሥጋ ይፍረስ" ብለው አጋቧቸው፡፡

ሆኖም ዲሜጥሮስና ሚስቱ ጻድቃን ስለነበሩ ተማክረው ለሠላሳ ዘጠኝ ዓመት አብረው ሲኖሩ በባልና በሚስት ወግ አይተዋወቁም ነበር፡፡ የእግዚአብሔር መልአክ በንጽሕና ይጠብቃቸው ነበርና፡፡ አብሮ ለመኖር የወሰኑትም ቢለያዩ ወላጆቻቸው ለሌላ ሰው ሳይድሯቸው እንደማይቀሩ ስለሰጉና የጋብቻ ዓላማ ስላልነበራቸው እንጂ እነርሱ መጋባት ፈልገው አልነበረም፡፡

ወላጆቻቸው "ሕንጻ ሃይማኖት ከሚፈርስ ሕንጻ ሥጋ ይፍረስ" በማለት ዝምድናቸውን አፍርሰው ያጋቧቸው ልጆቻቸውን ለአህዛብ ላለመዳር ሲሉ ነው፡፡ ይህ ምን ያሳያል? ከማያምኑ ጋር መጋባት እጅግ የከፋ ነገር መሆኑን አይደለምን? በርካቶች ግን በልማድ እንጂ በመንፈሳዊ ዕውቀት ስለማይመሩ ከባድ ጥፋት ሆኖ የሚታያቸው ከሃይማኖት ይልቅ የሥጋ ዝምድና መፍረሱ ነው፡፡

ዛሬ በአገራችን በስመ ክርስቲያን እየኖሩ ከቅርብ የሥጋ ዘመዳቸው ጋር ከተጋቡ ሰዎች ይልቅ ከማይምኑ ሰዎች ጋር የተጋቡ ሰዎች ቁጥር እጅግ የተራራቀ ነው፡፡ ይህም አጋጣሚ ሳይፈጠር ቀርቶ ሳይሆን ዘመድን ማግባት የማያምንን ከመግባት በላይ እንደ ነውር ስለሚቆጠር ነው፡፡ የሥጋ ዘመድን ማግባት





ነውር አይደለም ለማለት ሳይሆን ምን ጊዜም ቢሆን የሚበልጠውን ግን አብልጦ ማየት ያስፈልገናል፡፡

ቤተ ክርስቲያን ከአህዛብ ጋር እንዳይጋቡ ልጆቿን ማስተማር ኃላፊነቷ ነው፡፡ ይህንንም በሚገባ ተወጥታለች፤ ይህም ሕገ ልቡና ሕገ ኦሪትንና ሕገ ወንጌልን ዋቢ አድርጋ በሠራችው የጠራ ማስረጃ መረዳት ችለናል፡፡ እንደምታስተምረው እንዲሁ ደግሞ ማድረግ ከእርሷም ይጠበቃል፡፡ እርሷም እንደ ማኅበር፣ እንደ ተቋም ወይም እንደ አንድ ሃይማኖታዊ አካል ከማያምኑ መንግሥታትና ነገሥታት ጋር ያላት ግንኙነት እንደባልና ሚስት አንድነት ያህል መሆን የለበትም፡፡

ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖት ከሌላቸው መንግሥታትና ነገሥታት ጋር የሚኖራት ግንኙነት ልኩን የጠበቀና ማንኛውም አንድ ክርስቲያን ሃይማኖት ከሌላቸው ሰዎች ጋር ሲኖረው እንደሚገባው ዓይነት ልከኛ ግንኙነት መሆን አለበት፡፡ ይህን ለማድረግ ጥበብ ያስፈልጋል፡፡ ክብሯ እንዲጠበቅ፣ መኖሯ እንዳይዘነጋና ጥቅሟንም እንዳታጣ ብዙም ሳትርቅ፣ ማንነቷ ተበላሽቶ፣ ስሟ ጠፍቶ በልጆችዋ እንዳትጠላ መንፈሳዊ ሳይሆን መንግሥታዊ ተቋም ብቻ መስላ እንዳትታይ ደግሞ ያለመጠን ሳትቀርብ መኀዝ ይኖርባታል፡፡ ሁሉም ነገር ልክ አለውና፡፡

# ምዕራፍ ሰባት

## ‹‹ከማያምኑ ጋር›› ጋብቻን በተመለከተ ልዩ ልዩ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

ጥያቄ ፩.

ከማያምኑ ጋር መጋባት አይቻልም? ያ ከሆነ ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹የማታምን ሚስት ያለችው አይተዋት ያላመነ ባል ያላት አትተወው›› ሲል ለምን ጻፈ?

በእርግጥ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በቆሮንቶስ መልእክቱ "ከወንድሞቹ ወገን ያላመነች ሚስት ያለችው ቢኖር እርስዋም ከእርሱ ጋር ለመቀመጥ ብትስማማ አይተዋት፤ ያላመነ ባል ያላት ሚስትም ብትኖር ይህ ከእርስዋ ጋር ሊቀመጥ ቢስማማ አትተወው" የሚል ዐረፍተ ነገር ጽፏል። (፩ቆሮ፯፥፲፪-፲፯)

ከላይ የተጠቀሰውን የቅዱስ ጳውሎስን መልእክት አንዳንድ ሰዎች "ከማያምኑ ጋር መጋባት ምንም ችግር እንደሌለው ሐዋርያው በዚህ አገላለጡ አስረድቷል።" በማለት መልእክቱን ለእነርሱ እንደመሰላቸውና ለፈለጉት ዓላማ በሚስማማ መንገድ አዛብተው ለመተርጎም ይጥራሉ፡፡ እውን ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ የሚያምኑ ከማያምኑ ጋር እንዲጋቡ የሚፈቅድ ወይም ለመጋባት መብት የሚሰጥ ነውን? በጭራሽ አይሰጥም። ታዲያ ምሥጢሩ ምን ይሆን?

ምሥጢሩን ለመረዳት የተጠቀመባቸውን ቃላት ፍቺ በየተራ እንመልከት። ከላይ በሰፈረው ጥቅስ ሐዋርያው ‹‹ወንድሞች›› በማለት የጠራቸው ወንዶች ክርስቲያኖችን ነው። ሴቶች ደግሞ ‹‹እኅቶች›› ይባላሉ። የምእመናን አባት እግዚአብሔር ስለሆነ ክርስቲያኖች ሁሉ ወንድምና እኅት ናቸውና። መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያኖችን በነጠላ ቁጥር ‹‹ወንድም›› ፣ ‹‹እኅት›› ሲላቸው እናገኛለን። ለዚህም ሐዋርያው ‹‹ወንድም ቢሆን ወይም እኅት›› በማለት ያሰፈረውን ሐረግ መጥቀስ ብቻ ይበቃናል። (፩ቆሮ፯፥፲፭)





ሐዋርያው ‹‹ከወንድሞች ወገን ያላመነች ሚስት ያለችው ቢኖር አይተዋት›› ሲል ከክርስቲያን ወንዶች መካከል ክርስቲያን ያልሆነች ሚስት ያለችው ሰው ቢኖር አይፍታት ማለቱ ነው። (፩ቆሮ፯፥፲፪)

እንደዚሁም ‹‹ያላመነ ባል ያላት ሚስትም ብትኖር ይህ ከእርስዋ ጋር ሊቀመጥ ቢስማማ አትተወው።›› ሲል ደግሞ ለክርስቲያን ሴት ክርስቲያን ያልሆነ ባል ካላት በሃይማኖት እኔን ካልመሰልክ ብላ አትፍታው ማለቱ ነው። (፩ቆሮ፯፥፲፫)

ሐዋርያው ይህን መልእክት ባስተላለፈበት አንቀጽ የተናገረው በትዳሩ ውስጥ የሃይማኖት ልዩነት ሳይኖር ቀደም ብሎ ስለተፈጸመ ጋብቻ ነው። ስለዚህ ቃሉ የሚመለከተው አስቀድሞ የተጋቡ ሰዎችን ነው ነው እንጂ ወደፊት የሚጋቡትን አይደለም።

ፍቺ የሚኖረው ጋብቻ ሲኖር ነው። ቀድሞ ጋብቻ ሳይኖር ፍቺ ሊኖር አይችልም። ሌላው ሐሳብ ደግሞ ፍቺ ከጋብቻ ጋር እንጂ ከመተጫጨት ጋር በምንም ሊዛመድ አይችልም። ስለዚህ ይህ የሐዋርያው ቃል ላልተጋቡ ሰዎች ሊጠቀስ አይችልም። ማለትም ያላመነች እጮኛ (ፍቅረኛ) ያለችው አይተዋት ወይም ያላመነ እጮኛ (ፍቅረኛ) ያላት አትተወው ማለት አይደለም። ስለዚህ የሐዋርያው ገለጻ ቀደም ሲል የተጋቡትን የሚመለከት በመሆኑ ከማያምኑ ጋር ለመጋባት ልባቸው እያወቀ የሚዘጋጁትን የሚደግፍ ወይም የሚያበረታታ አይደለምና ከማያምኑ ጋር መጋባት አሁንም ቢሆን በክርስትና ሃይማኖት የተነቀፈ ነው።

እንደ ሐዋርያው አገላለጥ "አይተዋት፣ አትተወው" ማለት "አይፍታት፣ አትፍታው" ማለት ነው። አንቀጾቹም ስለ መፋታት የሚያወሱ አንቀጾች መሆናቸውን መዘንጋት አይገባም። የተጫጩ ወንድና ሴት ባለመግባባት ሲለያዩ ተፋቱ አይባልም። ሐዋርያው በዚህ መንገድ እያዘዘ ያለው አስቀድሞ ተጋብተው እየኖሩ ስላሉ ባልና ሚስት መሆኑን የምናውቀው "ያላመነች ሚስት ያለችው" እና "ያላመነ ባል ያላት" እያለ በመጻፉ ነው።

www.ethiopianorthodox.org

ሐዋርያው ሲጽፍ "ሚስት ወይም ባል" እያለ መሆኑ የሚጽፈው ቀደም ብሎ ጋብቻቸው ስለተፈጸመ ሰዎች መሆኑን በግልጽ ያሳያል፡፡ የሐዋርያው መልእክት ያልተጋቡ ወንድና ሴትን የሚመለከት ቢሆን ኖሮ "የማታምን እጮኛ ወይም ፍቅረኛ ያለችው ሰው ቢኖር" ይል ነበር እንጂ ‹‹ሚስት››፣ ‹‹ባል›› እያለ አይጽፍም ነበር፡፡ ያልተጋቡ ፍቅረኛሞች "ያጨ፣ ያጨች፣ ያጩ፣ የተጫጩ ወይም እጮኛሞች" ይባላሉ እንጂ ባልና ሚስት አይባሉምና፡፡

በዘመነ ቅዱስ ጳውሎስ የክርስትና ሃይማኖት ለዓለም እንግዳ እንደመሆኗ መጠን በደንብ መስፋፋት ስትጀምር በሃይማኖት የተለያዩ ባልና ሚስት በአንድ ቤት ውስጥ መገኘታቸው የሚያስደንቅ ነገር አይደለም፡፡ ከባልና ከሚስቱ አንዱ ወገን ብቻ የሐዋርያትን ትምህርት አምኖ በመቀበሉና ክርስቲያን በመሆኑ በመካከላቸው የሃይማኖት ልዩነት ሊፈጠር ችሏል፡፡

ታሪኩ እንዲህ ነው፡፡ በዚያ ዘመን ሁለት ክርስትናን የማያውቁ ወይም የማያምኑ ወንድና ሴት ተጋብተው ይኖራሉ፡፡ ከጊዜ በኋላ ከሁለት አንዳቸው ክርስትናን የማወቅ፣ ፈቅዶና አምኖ የመጠመቅ ዕድል ይገጥማቸዋል፡፡ በባልና በሚስቱ መካከል የሃያማኖት ልዩነት ተፈጠረ ማለት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ እንደ ሐዋርያው ትምህርት ከሁለቱ ወደ ክርስትና የመጣው ወገን ባልየው ቢሆን ሚስቱን "ሊተዋት" ወይም "እኔ ክርስቲያን ሆኛለሁና ወይ እንደ እኔ አምነሽ ተጠመቂ እምቢ ካልሽ ደግሞ መፋታት አለብን!" ማለት የለበትም፡፡ ይህንን ለመደንገግ ሐዋርያው ‹‹ያላመነች ሚስት ያለችው ቢኖር አይተዋት›› በማለት ጻፈልን፡፡

ዛሬም ቢሆን ተጋብተው እየኖሩ ሳለ ከጊዜ በኋላ ወደ ክርስትና ሃይማኖት የሚመጡ ሰዎች የትዳር አጋራቸው እንደ እነርሱ ለማመን ፈቃደኛ ላይሆን ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ ሃይማኖቱን ባይቀበልም አብሮ ለመኖር ፈቃደኛ እስከሆነ ድረስ ወደ ክርስትና የገባው ወገን የሃይማኖት ልዩነትን ሰበብ አድርጎ የፍቺ ሐሳብ እንዳያመጣ የሚያስጠነቅቅ ቃል ነው፡፡ ከጋብቻ በኋላ ወደ ክርስትና





የሚጠሩ ሁሉ ይህን የቅዱስ ጳውሎስን ትምህርት በሚገባ መማር አለባቸው፡፡ ይህ ቃል የሚመለከተው እነርሱን ነውና፡፡

ከላይ የሰፈረው የሐዋርያው መልእክት ሙሉ ሐሳብ ይኸው ነው፡፡ ከዚህ አልፎ ሐዋርያው ‹‹ያላመነች ሚስት ያለችው አይተዋት፣ ያላመነ ባል ያላት አትተወው›› እያለ ቀደም ሲል የተጋቡ ባልና ሚስትን ያስተማረበትን አንቀጽ ይዞ ‹‹ከማያምኑ ጋር መጋባትን ቅዱስ ጳውሎስ ሰብኳል›› ማለት በሐዋርያው ላይ የሐሰት ምስክር መሆን ነው፡፡

ይህ የሐዋርያው መልእክት አንድ ክርስቲያን በሃይማኖት የማትመስለውን ሴት ልቡ እያወቀ እምነቷን እንደያዘች እንዲያገባት የሚያበረታታ አይደለም፡፡ ወይም ክርስቲያኗ ሴት ከማያምን ወንድ ጋር እንድትጋባ አላደፋፈረም፡፡ አበው ‹‹ዱባና ቅል ለየቅል›› እንደሚሉት የሐዋርያው መልእክት ከዚህ እጅግ በጣም የራቀ ሐሳብ ያለው ነው፡፡ ሐዋርያው በሌላ ስፍራ ከማያምኑ ጋር መጋባት እንደማይገባ ‹‹ከማያምኑ ጋር ጋብቻ በአዲስ ኪዳን›› በሚለው ርእስ ስር ያሰፈረውን ኃይለ ቃል ልብ ይሏል፡፡

ስለዚህ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በቆሮንቶስ መልእክቱ "ከወንድሞቹ ወገን ያላመነች ሚስት ያለችው ቢኖር እርስዋም ከእርሱ ጋር ለመቀመጥ ብትስማማ አይተዋት፤ ያላመነ ባል ያላት ሚስትም ብትኖር ይህ ከእርስዋ ጋር ሊቀመጥ ቢስማማ አትተወው" በማለት የጻፈው ኃይለ ቃል በዋናነት ሁለት ነገሮችን ያመለክታል፡፡

፩ኛ. አስቀድመው የተጋቡትን ሰዎች

፪ኛ. ወደ ክርስትና ለመምጣት አዲስ የሆኑትን ሰዎች

በርካታ ሰዎች ባለማወቅ ኃይለ ቃሉን በአጋዥነት የሚጠቅሱባቸው የተሳሳተ ሐሳቦች፡-

፩ኛ. ይህ የሐዋርያው መልእክት የተጋቡትን እንጂ ወደፊት የሚጋቡትን አይመለከትም ማለት ነው፡፡ በሃይማኖት ተለያይቶ መጋባትን አያበረታታም፡፡

፪ኛ. ከባልና ከሚስት አንዳቸው ከጋብቻቸው በኋላ ከኢአማኒነት ወደ ክርስትና የሚመጡትን ሰዎች እንጂ ክርስቲያን ሆነው ሳለ ልባቸው እያወቀ ከማያምን ሰው ጋር ስለተጋቡ ሰዎች አይናገርም፡፡ (፩ቆሮ፯÷፲፪-፲፮)

፫ኛ. አስቀድመው የተጋቡ እንደመሆናቸው መጠን የሃይማኖት ልዩነቱ የተፈጠረው ከሁለቱ አንዱ ወደ ክርስትና በመምጣቱ እንጂ አንዱ ወደ ክህደት በመሄዱ አይደለም፡፡ ስለዚህ የሐዋርያው ቃል ክርስቲያን ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ አንዱ ወገን በመካዱ ምክንያት የሚፈጠረውን የሃይማኖት ልዩነት አይመለከትም፡፡

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሦስት ነጥቦች አንደኛ ወደ ፊት ለመጋባት ለሚዘጋጁ ሁለተኛ ክርስቲያን ሆነው ሳለ ከማያምን ጋር በድፍረት ለተጋቡ ሦስተኛ ክርስቲያን ሆነው ተጋብተው ሳለ አንዱ ወገን ወደ ክህደት ሲሄድ ሐዋርያው ‹‹ያላመነች ሚስት ያለችው አይተዋት፣ ያላመነ ባል ያላት አትተወው›› በማለት የጻፈው ጥቅስ ያለ አገባቡ በማስረጃነት ሊጠቀስ እንደማይገባው ያሳያሉ፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ "ከወንድሞቹ ወገን ያላመነች ሚስት ያለችው ቢኖር እርስዋም ከእርሱ ጋር ለመቀመጥ ብትስማማ አይተዋት፤ ያላመነ ባል ያላት ሚስትም ብትኖር ይህ ከእርስዋ ጋር ሊቀመጥ ቢስማማ አትተወው" ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ ከላይ ምላሹ ተብራርቷል፡፡ ነገር ግን ሐዋርያው ለምን እንዲህ እንዳስተማረና ወደ ክርስትና የመጣው ወገን አስቀድሞ የፍቺ ጥያቄ በጭራሽ ማንሣት እንደሌለበት ያስጠነቀቀበትን ጥልቅ ምሥጢር ማወቅ ከፈለግህ ከዚህ ቀጥሎ ከ‹‹ሀ›› እስከ ‹‹ተ›› የተዘረዘሩትን ነጥቦች በእርጋታ አንብብ!

ሀ) ሐዋርያው "አንቺ ሴት ባልሽን ታድኚ እንደሆንሽ ምን ታውቂያለሽ? ወይስ አንተ ሰው ሚስትህን ታድናት እንደሆንህ ምን ታውቃለህ?" በማለት እንዳስገነዘበው አስቀድመው ከተጋቡት ባልና ሚስት በኋላ ክርስቲያን የሆነው ሰው እርሷ አብራው ለመኖር እስከፈቀደች ድረስ እንደ እርሱ ባታምንም እንኳን እርሷን ፈትቶ





ካላባረራት የእርሱን ሃይማኖት ማለትም ክርስትናውን የማየት የመማር፣ የመማረክና የማመን ዕድል ሊኖራት ይችላል፡፡

በእርግጥ ይህ የሚሆነው ባልየው ክርስቲያን በመሆኑ ብቻ ሳይሆን በትክክል በክርስትናው መንገድ የሚጓዝና መልካም አርአያነት ያለው ክርስቲያን ከሆነ ብቻ ነው፡፡ እርሱ ክርስትናን እንደተቀበለ ወዲያውኑ እንደእርሱ ያላመነች ሚስቱን "እንደኔ አላመንሽምና ሂጂልኝ" ብሎ ቢያሰናብታት ግን ክርስትናን አምና የምትቀበልበትን አንድ በጎ ዕድል አሳጣት ማለት ነው፡፡

ይህም ብቻ ሳይሆን ባሏ ክርስቲያን ሲሆን ያባረራት ሴት በሌላ መንገድ ስለክርስትና የምትሰማበት አጋጣሚ ቢኖር እንኳን ባሏን ያሳጣትና ትዳሯን ያፈረሰባት የክርስትና ሃይማኖት እንደሆነ በመቁጠር ክርስቲያን ለመሆን የተከፈተ ልብ ላይኖራት ይችላል፡፡ እንዲያውም ለክርስትና ሃይማኖት በጠላትነት ልትሰለፍ ትችላለች፡፡

ስለዚህ አስቀድሞ ክርስቲያን ያልነበሩና ተጋብተው ያሉ ሰዎች አንደኛው ክርስቲያን የመሆን ዕድል ሲገጥመው አብሮ ለመኖር ፈቃደኛ እስከሆነ ድረስ ያላመነውን ወገን እንዳይፈታ ከታዘዘበት ምክንያቶች አንደኛው በጋብቻ ምክንያት ያላመነው ወገን ሊያምን የሚችልበት ሁኔታ ስለሚፈጠር ነው፡፡

ለ) ዳግመኛም ወደ ክርስትና የመጣው ሰው ተሸርሽሮ ወደ አለማመን ይሄዳል የሚል ስጋት ባለመኖሩ "ያመነው ወገን ያላመነችውን ሚስቱን አይፍታት" ተብሏል፡፡ አዲሱ ክርስቲያን ወዳላመነችው ሚስቱ ይሳባል እንዳይባል ቀድሞ የኖረበት እምነት በመሆኑ ምን አዲስ ነገር አግኝቶ ይሳባል? ያመነው ባል ወደ እርሷ እምነት ይሳባል ከማለት ይልቅ የእርሷ ወደባሏ ሃይማኖት ማለትም ለትዳራቸው አዲስ ወደሆነው ወደ ክርስቲያንነት የመሳብ ዕድሏ በጣም የሰፋ ነው፡፡ ምክንያቱም የእርሱ ክርስትና ለእርሷ አዲስ ነገር ሲሆን የእርሷ እምነት ግን ለእርሱ የኖረበት በመሆኑ ነው፡፡

ሐ) አንድ ባለትዳር ሰው ክርስቲያን ለመሆን ፈልጎ ሲመጣ ‹‹ሚስትህንም አሳምነህ ማምጣት፤ ካልሆነ ደግሞ ሚስትህን

መፍታት አለብህ!›› ቢባል ምን ሊሰማው ይችላል? ክርስቲያን ለመሆን “በግድ ከትዳሬ መፈናቀል አለብኝን?” ብሎ ሊጠይቅና ሊያፈገፍግ አይችልምን? ለአዲስ ክርስቲያን ከሃይማኖቱ ሚስቱ ብትበልጥበት የሚያስደንቅ ነገር አይደለም። ስለዚህ አበው “ከሚሰበር ይሰንጠር” እንዲሉ። ይህ ሰው ክርስቲያን ሳይሆን ከሚቀር ምንም ሚስቱ ተከትላው እንደ እርሱ ባታምንም የእርሱ ብቻ ማመን መንፈሳዊ ትርፍ ነውና ሐዋርያው “የማታምን ሚስት ያለችው ቢኖር አይተዋት” አለ። (፩ቆሮ፯÷፲፪)

መ) አንድ ባለትዳር ሰው ክርስትናን ለመቀበል በመጣ ጊዜ ሚስቱ ለማመን ካልፈቀደች “ልትፈታት ይገባሃል” ቢባል ለምን ማለቱ ይቀራልን? ታዲያ ምን መልስ ሊሰጠው ይችላል? እንበልና “ሚስትህ ወደ ቀደመህ የተሳሳተ እምነትህ ልትመልስህ፣ ልትስብህ ወይም ልታረክስህ ትችላለች” ቢባል ምን ሊሰማው ይችላል?

በመጀመሪያ ይህ አመላለስ ለአዲስ ክርስቲያን አእምሮ የሚመች አይደለም። ቀጥሎም መልሱ ሌሎች ቀጣይ ጥያቄዎችን ለማንሣት ይጋብዛል። ለምሳሌ፡- “እኔ የተሻለ እምነት አገኘው ብዬ ወደ ክርስትና መጣሁ። የእርሷ እምነት ማለት የኔ የቀድሞ እምነት ነው። ታዲያ የእርሷ እምነት እኔን ሊያረክስ እንዴት ይችላል? ከዚያ ይልቅ አሁን የተቀበልሁት የእኔ ክርስትና እርሷን መቀደስ አይገባውም ነበርን?” እያለ በመጠየቅ ያመነባት የክርስትና እምነት እርሱን በቅድስና ለመጠበቅ ብቃት እንደሚጎድላት እንዲያስብና ከማመን ይልቅ እንዲጠራጠር ያደርገዋል።

በአንጻሩ “በርታ! ሚስትህ ምንም እንዳንተ ባታምንም እንደረከሰች አትቁጠራት፤ በአንተ እምነት ሚስትህ ትቀደሳለችና። ውሎ አድሮ ደግሞ ያንተን ሃይማኖት እንድትከተል ልታሳምናት ትችላለህ።” ቢባል ግን የራሱ የልቡና እምነት ከማደጉም በተጨማሪ እርሷን ሳይጠየፍ መቅረቡ እንዲያሳምናት የተመቻቸ ዕድል ይፈጥርለታል። ስለዚህ የአዲሱን አማኝ ማለትም የባልየውን የልቡና እምነት ለማጠናከር ሲባል “የማታምን ሚስት ያለችው ቢኖር አይተዋት” ተብሎ ተጻፈ። (፩ቆሮ፯÷፲፪)





ሠ) ከጨለማ ብርሃን ይበረታል። ይህም ጨለማ በነገሠበት ቤት ውስጥ አንዲት ሻማ ስትበራ ጨለማ በመሸሹ ይታወቃል። ቅድስናም ከርኩሰት ይበረታል። ለዚህም ነው ሐዋርያው “ያላመነ ባል በሚስቱ ተቀድሷል፤ ያላመነች ሚስትም በባልዋ ተቀድሳለች፤ አለዚያ ግን ልጆቻችሁ ርኩሳን ናቸው። አሁን ግን የተቀደሱ ናቸው።” (፩ቆሮ፯÷፲፬) በማለት የተናገረው ካላመኑ ባልና ሚስት አንዳቸው ሲያምኑ ለቤታቸው ሁሉ ቅድስና ምክንያት ይሆናሉ።

ረ) ያመነው ባል ያላመነች ሚስቱን አይተዋት። ለምን ቢባል ልጆቻቸው “ርኩሳን” እንዳይሆኑ ይህ ማለት በኦሪት ከሕግ ጋብቻ ያልተወለደ “ዲቃላ” እንደ ርኩስ ተቆጥሮ ወደ ቤተ መቅደስ አይገባም ነበር። ያመነ ባል ያላመነች ሚስቱን ከፈታት የቀደመ ጋብቻውን ሕገ ወጥ ማድረጉ ነው። እንዲህ ከሆነ ደግሞ ልጆቹም ከሕጋዊ ጋብቻ ያልተገኙ ‹‹ዲቃሎች›› ወይም ‹‹ርኩሳን›› መሆናቸው ነው። ስለዚህ እንዲህ እንዳይሆን ያመነ ባል ሚስቱን አይፍታት፤ ልጆቹንም ‹‹ዲቃሎች›› ወይም “ርኩሳን” እና ወላጅ አልባ አያድርጋቸው።

ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ጋብቻ ላልተጋቡ ሰዎች ለትዳራቸው የቅድስና ማዕርግ አትሰጥም። ይሁን እንጂ እውቅና አትከለክልም። ስለዚህ ሃይማኖት ኖራቸውም አልኖራቸውም ተጋብተው የመጡ ሰዎችን አምነው እስከመጡ ድረስ ተቀብላ ተገቢውን ሥርዓት በመፈጸም ጋብቻቸውን ታጸናለች። ማለትም አምነው ሳለ በመንፈሳዊ ሥርዓት ያልተጋቡትን ንስሐና ቅዱስ ቁርባንን በመስጠት ጋብቻቸውን ስታጸና ሃይማኖት ሳይኖራቸው ተጋብተው የመጡትን ደግሞ በንስሐ ተቀብላ አጥምቃ በማቁረብ ጋብቻውን ታጸናለች።

ቅድስና ባይኖረውም ጋብቻ ተብሎ የተፈጸመ ሥርዓት ሁሉ ባልና ሚስቱን አንድ ያደርጋል። እንኳን ‹‹ተራ›› ወይም በሃይማኖታዊ ሥርዓት ያልተፈጸመ ጋብቻ ይቅርና ዝሙትም የሥጋ አንድነትን ይፈጥራል። ሐዋርያው “ወይስ ከጋለሞታ ጋር የሚተባበር አንድ ሥጋ እንዲሆን አታውቁምን? ሁለቱ አንድ ሥጋ

ይሆናሉ ተብሏልና፡፡" በማለት የጻፈው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ (፩ቆሮ፮÷፲፮)

በዚህ ሥፍራ ሐዋርያው ሁለቱ ‹‹አንድ ሥጋ ይሆናሉ›› ተብሎ ለባልና ለሚስት የተነገረውን ቃል ከጋለሞታ ጋር ዝሙት ስለሚፈጽሙ ሰዎች እንደጠቀሰው አስተውል፡፡ ዝሙትም የሥጋ አንድነት ይፈጥራልና፡፡ ዝሙት እንዲህ ከሆነ ማንኛውም ዓይነት ‹‹ተራ›› ጋብቻ ቅድስና አያሰጥም እንጂ የሥጋ አንድነትን መፍጠር ይችላል፡፡ ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን በቁርባን ላልተጋቡ ሰዎች ጋብቻ ቅድስና ባትሰጥም እውቅና ግን አትከለክልም፡፡ ይህ ዓይነቱ ትዳር ቅዱስ የሚሆነው ባልና ሚስቱ ንስሐ ገብተው ሥጋ ወደሙን በመቀበል ሲያጸኑት ብቻ ነው፡፡

ሰ) ሐዋርያው "ያላመነች ሚስት ያለችው ባል ቢኖር አይተዋት" በማለት አዟል፡፡ ነገር ግን ያመነ ሰው ያላመነች ሚስቱን እንዲፈታት ሐዋርያው ፈቅዶ ቢሆን ኖሮ ምን ሊከሠት ይችል እንደነበር ታውቃለህ?

እኛ ክርስቲያኖች የምንመራባቸውን ክርስቲያናዊ ሕጋጋት ጠንቅቀው የሚያውቁ ብዙ ሃይማኖት የሌላቸው ሰዎች አሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች በትዳራቸው ደስተኛ ሳይሆኑ በቀሩ ቁጥር "ክርስቲያን ሆነናል" እያሉ ትዳራቸውን ለማፍረስ የክርስትና ሃይማኖትን እንደ ምክንያት ይጠቀሙባት ነበር፡፡ እንዲህ ሲሆን ደግሞ የክርስትና ሃይማኖት ማኅበራዊ አኗኗርን የምታናጋ አፍራሽ ሚና ያላት ተቋም ትሆን ነበር፡፡ ስለዚህ ይህን ሁሉ ሳይሆን በፊት የሚያውቅ መንፈስ ቅዱስ አንዳንዶች ትዳራቸውን ለማፍረስ ክርስትናን ምክንያት እንዳያደርጉና የክርስትና ሃይማኖትም እንዳይነቀፍ በሐዋርያው አማካኝነት "ያላመነች ሚስት ያለችው ባል ቢኖር አይተዋት" በማለት ደነገገ፡፡

ሸ) እዚህ ላይ ማስተዋል የሚያስፈልገው አንድ ጉዳይ አለ፡፡ ይኸውም ከላይ ክርስቲያን የሆነው ወገን የፍቺ ሐሳብ ቀድሞ ማንሣት አይችልም የተባለው ያለምክንያት አይደለም፡፡ አስቀድሞ ሁለቱም በሌላ ዓይነት አምልኮ የነበሩ ናቸው፡፡ በዚያም አምልኮ





ተስማምተው ተጋብተዋል፡፡ የክርስትና ሃይማኖት ለእነዚህ ሰዎች ትዳር እንግዳ ነገር ነው፡፡ ከመጋባታቸው በፊት አያውቁትም ነበርና፡፡ ስለዚህ ከሁለቱ አንዱ ክርስትናን ሲቀበል ይህ ሰው በትዳራቸው ቀድሞ ያልነበረ አንድ እንግዳ ነገር አመጣ ማለት ነው፡፡ ለትዳራቸው እንግዳ የሆነውን የክርስትና ሃይማኖት ወደ ትዳራቸው ይዞ ያመጣው ክርስቲያኑ በመሆኑ ልዩነት የፈጥረው እርሱ ሆኖ ሳለ ፍቺ ጠያቂውም እርሱ መሆን አይችልም፡፡

ክርስቲያን የሆነው አካል ቀድሞ ፍቺ ከጠየቀ ሚዛናዊ ያልሆነ የመብት አጠቃቀም ይንጸባረቃል፡፡ ሁለት ተዛማጅ መብቶች ለአንዱ አካል ተሰብስቦ መሰጠት የለበትም፡፡ እስኪ እናንተ ፍረዱ! ክርስቲያን በመሆን ልዩነቱን ያመጣው እርሱ ሆኖ ሳለ ፍቺ ጠያቂውም እርሱ መሆን እንዴ ይገባዋል? ይህ አካሄድ እራሱ ገርፎ ራሱ እንደሚጮኽ ጅራፍ አያስቆጥርምን? ይህ እንዳይሆን ሐዋርያው ‹‹ያላመነች ሚስት ያለችው አይተዋት›› አለ፡፡

ቀ)የክርስትና ሃይማኖት ሚዛናዊ የሆነ የመብት አጠቃቀም የሚንጸባረቅባት ሃይማኖት ናት፡፡ ማንንም በግድ እመን አትልም፡፡ ሌላው ቀርቶ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ተጽዕኖ በማንም ላይ በማሳደር እንዲያምኑ አታስገድድም፡፡ ለዚህም ነው ያመነው ወገን ያላመነውን ወገን በግድ እመን ያለዚያ ግን እንፋታለን የሚል ትምህርት የሌላት፡፡ ካላመንክ እንፋታለን ማለት ራሱ ማስገደድ ነውና፡፡ ሰው ማመን ያለበት ተረድቶ ካወቀ በኋላ በራሱ ፈቃድ መርጦ ነውና፡፡ ከተጋቡ በኋላ አንዱ ወገን ሲያምን ሌላው አላመነም ማለት ትዳሩን አልፈለገም ማለት አይደለም፡፡ አላምንም ስላለ ትዳሩን ማጣት ደግሞ የለበትም፡፡ ትዳሩን ማፍረስ ግን በግድ እንዲያምን ተጽዕኖ ማድረግ ነው፡፡

በ) ሁለት ክርስቲያን ያልነበሩ ወንድና ሴት ከጋብቻ በኋላ አንዱ ወገን ብቻ ወደ ክርስትና ሃይማኖት በመጠራቱ ምክንያት የሃይማኖት ልዩነት ሲፈጠር ወደ ክርስትና ያልመጣው ወገን ጋብቻው እንዳይፈርስ አብሮ ለመኖር እስከፈቀደ ድረስ አደጋ የሌለው አማራጭ ይህ ብቻ ነው፡፡

ሐዋርያው ከባልና ከሚስት አንዱ ወገን ለብቻው ሲያምን ‹‹ጋብቻው መፍረስ አለበት ወይም ይፋቱ›› በማለት ግዴታ አስቀምጦ ቢሆን ኖሮ ብዙ ነገሮች ይወሳሰቡ ነበር። እየተፈቃቀዱ ተፋቱ ማለት ስሜታቸውን በእጅጉ ይጎዳል። ልጆች ይበተናሉ፣ ሀብት ይባክናል ወዘተ... ስለዚህ ክርስቲያናዊ ሕይወትን ምቹና ቀላል ለማድረግ መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያው አድሮ "ያላመነች ሚስት ያለችው ባል ቢኖር አይተዋት" በማለት የፍቅር ሥርዓት ሠራልን።

ተ) በመጨረሻም የዚህ ሁሉ መደምደሚያ በዚያው ምዕራፍ በተደጋጋሚ ሐዋርያው "እያንዳንዱ በተጠራበት መጠራት እንደዚሁ ይኑር" በማለት የተናገረው ቃል ነው። የክርስትና ሃይማኖት መመሪያ አንድ ሰው ክርስቲያን ሲሆን በሃይማኖቱ አመካኝቶ ባህሉን ወይም በሰዎች መካከል አቀማመጡን እንዲለውጥ ከቶ አያስገድድም። በእርግጥ ለክርስትና ተጻራሪ የሆኑና ጎጂ ነገሮችን በመቅረፍ በሕይወት ለውጥ ማምጣት ተገቢ ነገር ነው። ነገር ግን አግብቶ የተጠራ በትዳሩ ጸንቶ ይኑር ሳያገባ የተጠራ በሕጉ መሠረት ያግባ። "በተጠራበት መጠራት" መኖር ማለት ይህ ነውና። (፩ቆሮ፯÷፳)

ጥያቄ ፪.

በክርስትና መፋታት እንዴት ይታያል?

ፍቺን የተመለከተ ይህ አጭር የማስገንዘቢያ ትምህርት ለቀጣዩ ጥያቄና መልስ እንደ መንደርደሪያ ሊታይ ይችላል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከላይ የተናገረውን ቃል ባሰፈረበት በ፩ኛቆሮንቶስ ምዕራፍ፯ ከቁጥር፲ ጀምሮ የሚናገረው ስለ ፍቺ ነው። ባልና ሚስቱንም ከሃይማኖት አንጻር በሁለት ወገን መድቧቸዋል።

በአንደኛው መደብ ባልና ሚስት ሁለቱም ክርስቲያኖች ሆነው ሳለ በመካከላቸው አለመግባባት ሲፈጠር ፍቺን በተመለከተ ምን መደረግ እንዳለበት የሚያወሳ ነው።



www.ethiopianorthodox.org



በሁለተኛው መደቡ ደግሞ ከሁለቱ ማለትም ከባልና ከሚስቱ አንዳቸው ሃይማኖታቸው ከቀናች የክርስትና ሃይማኖት ውጪ ሲሆን ፍቺን በተመለከተ ምን መደረግ እንዳለበት የሚያስረዳ ነው። ለሁለቱም መደብ ምን መደረግ እንዳለበት ያሰፈረውን ውሳኔ በየተራ እንዘረዝራለን።

፩ኛ ባልና ሚስቱ ሁለቱም ክርስቲያን ሲሆኑ

እንደ ሐዋርያው መልእክት ባልና ሚስቱ ሁለቱም ክርስቲያኖች ከሆኑ ምንም ባይግባቡ መፋታት አለመቻላቸው ምንም ጥርጥር የሌለበት ነገር ነው። ለዚህም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ባልም ሚስቱን አይተዋት ብዬ የተጋቡትን እዛቸዋለሁ" በማለት የተናገረው ቃል ብቻ በቂ ነው።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መፋታት እንደማይቻል ያስተማረው ትምህርት ለክርስቲያናዊ ጋብቻ ቋሚ መሠረት ነው። (ማቴ፲፱÷፫-፱) በተጨማሪም ፍቺን አስመልክቶ ከላይ ሐዋርያው ካሰፈረልን ቃል በመነሣት ቤተ ክርስቲያን ሥጋውንና ደሙን ሰጥታ፣ ጸሎተ ተክሊል አድርሳ ያጋባቻቸው ባልና ሚስት ‹‹አልተግባባንም ወይም ተስማምቶ ለመኖር አልቻልንም።›› ብለው ቢመጡ ለፍቺያቸው እውቅና አትሰጥም።

ሐዋርያው ‹‹ባልም ሚስቱን አይተዋት›› እያለ በባል በኩል ሆኖ ቢናገርም ቃሉ የሚመለከተው ሁለቱንም ወገን ማለትም ባልና ሚስቱን ነው። ለዚህም ‹‹እዛቸዋለሁ›› ይላል እንጂ ባልን ብቻ ለይቶ ‹‹እዘዋለሁ›› አይልም።

ሐዋርያው በክርስቲያኖች ዘንድ መፋታት እንደማይቻል በተጠቀሰው መንገድ ካዘዘ በኋላ ይህን ትእዛዝ እርሱ በግሉ ወይም ከሥጋና ከደም ፈቃዱ ያመነጨው ሳይሆን ቀደም ሲል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረውና በወንጌል የሰፈረ ትእዛዝ መሆኑን ሲያስረዳ "እኔ ግን አላዝም ጌታ እንጂ" በማለት ጨምሮ ገልጧል። (፩ቆሮ፯÷፲-፲፩) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌል ባልና ሚስት "አይለያዩ" ብሎ አዟልና። (ማቴ፭÷፴፪፤፲፱÷፱)

ሃይማኖት ባላቸው ባልና ሚስት መካከል ፍቺን አስመልክቶ ያለው ሕግ ግልጥ ነው። ክርስቲያኖችም ለዚህ ሕግ ይገዛሉ። ማለትም ሳይለያዩ መኖር ይኖርባቸዋል። ክርስቲያን ሆኖ በዚህ መልኩ በጥንቃቄ የተሠራውን ይህን ሕግ አለማክበር ነፍስን መበደል ሥጋንም መጉዳት ነው።

ለዚህ ሕግ አልገዛም በማለት ከባልዋ የምትለይ ክርስቲያን ሴት ካለች "ከባልዋ ትታረቅ" ይላል። መታረቅ አሻፈረኝ ካለች ደግሞ "ሳታገባ ትኑር" በማለት እገዳ ይጥልባታል። ባል ሚስቱን መፍታት እንደሌለበት ደግሞ "ባልም ሚስቱን አይተዋት" በማለት ያዘዋል። ሳይግባቡ ቀርተው ባል ሚስቱን እተዋለሁ ካለ በሚስቲቱ እንደተጣለው እገዳ ሁሉ እርሱም ‹‹ሳያገባ ይኑር›› መባሉ ግድ ነው።

ሐዋርያው ‹‹ሚስትም ከባልዋ አትለያይ ብትለያይ ግን ሳታገባ ትኑር›› በማለት የደነገገው ቃል ለፍቺ እውቅናን የሚሰጥ አይደለም። በክርስቲያኖች ዘንድ ፍቺ በምንም መልኩ አይፈቀድም። ይሁን እንጂ ሌሎችን መንፈሳዊ ሕግጋት የማያከብሩ ክርስቲያኖች እንዳሉ ሁሉ የፍቺንም መንፈሳዊ ሕግ ሳያከብሩ ቀርተው በራሳቸው ፈቃድ የሚፋቱ ክርስቲያን የሆኑ ባልና ሚስት መኖራቸው ይታወቃል። ስለዚህ ከቤተ ክርስቲያን ሕግ ውጭ በፈቃዳቸው የሚፋቱ ባልና ሚስትን ሁለተኛ ጥፋት እንዳይፈጽሙ ለማሰር ‹‹ብትለያይ ግን ሳታገባ ትኑር፤›› በማለት ደነገገ። ለባልየውም እንዲሁ ነው። ‹‹ብትለያይ ግን›› የሚለው ሐረግ ራሱ እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ለፍቺ እውቅና እንደማትሰጥ ያሳያል። በራሷ ፈቃድ እምቢ ብላ ከተለያየች ግን እንደማለት ነውና።

ክርስቲያን ባልና ሚስቶች መፋታት አይችሉም። በፈቃዳቸው ግድ እንፋታለን ካሉ ደግሞ በእነርሱ ላይ የሚጣል ልዩ ተጨማሪ ሕግ ይኖራል። ይኸውም ሌላ ማግባት እንደማይችሉ ማስረዳትና ማዘዝ ነው። ሐዋርያው ‹‹ብትለያይ ግን ሳታገባ ትኑር›› ያለው ስለዚህ ነው። ብዙዎች ክርስቲያን ባልና ሚስቶች መፋታት እንደሌለባቸው እያወቁ ‹‹አልቻልኩም›› እያሉ ይፋታሉ። ከተፋቱ





በኋላ ሌላ ማግባት እንደሌለባቸው የሚያውቁ ግን እምብዛም አይገኙም። የክርስቲያን ሕግ መፋታትን ብቻ ሳይሆን ከፍቺ በኋላ የሚደረግንም ጋብቻ ያወግዛል።

የዚህ ተጨማሪ ሕግ ጠቀሜታ ደግሞ ምናልባት ሰዎች ትዳራቸውን ሲያፈርሱ ሲሉ ‹‹እንጋባ›› የሚላቸው ሌላ አይዞህ ባይ ካገኙ ለመፋታት ይፋጠናሉና ይህንን በር ለመዝጋት ነው። ወይም ከኑሮ አጋራቸው በአንድ ነገር ይሻላል ያሉት ሰው ለትዳር ሲጠይቃቸው ትዳራቸውን ለማፍረስ ይነሣሣሉ። እንዲያውም እውነት ለመናገር ብዙ ሰዎች የሚፋቱት በትዳራቸው የተፈጠረውን ችግር መሸከም አቅቷቸው ሳይሆን ‹‹የተሻለ›› ብለው ያሰቡትን ነገር ልባቸው ሲከጅል ነው። ስለዚህ ‹‹ብትለያይ ግን ሳታገባ ትኑር›› የሚለው ሕግ ይህንን ክፍተት በመዝጋት ሌላ የማግባት ተስፋን ያጨልማል።

ማን ያውቃል? ለመፋታት ያሰቡ ሰዎች ‹‹የወደዱትን ሲያጡ የጠሉትን ይቀላውጡ›› እንደሚባለው ሌላ የማግባት ዕድል እንደሌላቸው ሲነገራቸው ተመልሰው ይታረቁ ይሆናል። ወይም ጊዜ ሲያስተምራቸውና ብቸኝነት የበለጠ ጉዳት ሲሆንባቸው የጠሉትን ትዳር ያመሰግኑት ይሆናል። ያም ባይሆን ፍቺን ያስመለከታቸው ባለጋራ ሰይጣን ሲሸነፍና አፍሮ ሲሄድ ልብ ይገዙና ወደ ትዳራቸው ይመለሱ ይሆናል።

ከዚህም ባለፈ የየግል ጥቃታቸውና ጉዳታቸው ብቻ ታይቷቸው ፍቺን የመረጡ ባልና ሚስት ብዙ ጊዜ የፍቺ አሰቃቂነትና የልጆቻቸው ጉዳትና የወደፊት ዕጣ ፋንታ የሚታያቸው ከፍቺ በኋላ ተረጋግተው ሲቀመጡ ነው። በዚህ ጊዜ ምናልባት ስለልጆቻቸው ብቻ እንኳን ሲሉ መፋታት እንዳልነበረባቸው ሊገነዘቡ ይችላሉ። ይህ ከሆነ ቸኩለው ሌላ ካላገቡ የመመለስና ትዳራቸውን እንደገና የማደስ ዕድል ይኖራቸዋል። ከተፋቱ በኋላ ቸኩሎ አለማግባት በብዙ መንገድ ጥቅም አለውና። ሐዋርያው "‹‹ብትለያይ ግን ሳታገባ ትኑር››"

ያለው ስለዚህ ነው። ይሁን እንጂ መፈፋታት በክርስትና ምንም እውቅና የለውም።

### ፪ኛ ከባልና ከሚስት አንዳቸው ክርስቲያን ካልሆኑ

ከባልና ከሚስቱ አንደኛው ወገን ያላመነ ከሆነ ግን ፍቺን በተመለከተ ያለው ሐሳብ አስቀድሞ ካየነውና ሁለቱም ክርስቲያን ሲሆኑ መወሰን ካለበት ለየት ያለ ነው። ይኸውም ከሁለቱ ሰዎች ክርስቲያን የሆነው በክርስትና ሕግ የታሰረ በመሆኑ ከላይ የተጠቀሰው ‹‹መፋታት አይቻልም›› የሚለው ሕግ በክርስቲያኑ በኩል እንደ ጸና ይቀራል። ስለዚህ ምን ጊዜም ቢሆን ክርስቲያኑ የፍቺን ሐሳብ ማንሣት፣ መወጠንና የነገሩ አንሺ መሆን አይችልም። ይህ ሁሉ የሚሆነው ግን ያላመነው ወገን ከክርስቲያኑ ጋር አብሮ ለመኖር እስከፈቀደ ድረስ ብቻ ነው። ያላመነው ወገን ፈቃድ ለጋብቻው መጽናትም ሆነ መፍረስ እንደቅድመ ሁኔታ ይታያል።

እውነተኛ ክርስቲያን የሆነ ሰው ያላመነች ሚስት ካለችው እርሷ አብራው ለመኖር እስከፈቀደች ድረስ እርሱ እርሷን ፈትቶ ክርስቲያን የሆነችውን አገባለሁ ማለት አይችልም። እንደዚሁም ክርስቲያን የሆነች ሴት ያላመነ ባል ካላት እርሱ አብሯት ሊኖር ፈቃደኛ ሆኖ ሳለ እርሱን ፈትቼ ክርስቲያን የሆነ ባል አገባለው ብትል ሐሳቧ በክርስትና ሃይማኖት ተቀባይነት የለውም። የቅዱስ ጳውሎስ ትምህርት የሚያስረዳን ይህንን ነው።

የክርስትና ሕግ የሚመለከተውና የሚያዘው ክርስቲያኖችን ነው። ለምሳሌ ፦ ላመነ ባል ያላመነች ሚስት ብትኖረው የክርስትና ሕግ ያላመነችውን ሚስት በግድ አብረሽው ኑሪ ወይም ባልሽን አትፍቺው አይላትም። ለምን ቢባል አላመነችምና። ባላመነችበት የክርስቲያኖች ሕግ እንዴት ትመራለች? የክርስትና ሕግም ያላመነችውን እርሷን ከማዘዝ ይልቅ በክርስትና ያመነውን ባሏን "አትፍታት" ይላል። እርሷ ግን ያላመነች እስከሆነች ድረስ ከክርስትና ሕግ ነጻ ናት። የክርስትና ሕግና ሥርዓት በእርሷ ላይ





አይሠራም። በክርስትና ያላመነችን ሚስት ከባሏ ጋር የሚያኖራት የግል ፈቃዷ ነው እንጂ የክርስትና ሕግ አይደለም። ስለዚህ አብሮ መኖር ከወደደች ትኖራለች ካልወደደች ግን ትታው ለመሄድ ወይም ለመለየት ትችላለች ማለት ነው።

ዳግመኛም "የማያምን ግን ቢለይ ይለይ። ወንድም ቢሆን ወይም እኅት (ክርስቲያኑ ወገን) እንዲህ በሚመስል ነገር አይገዙም" ይላል። (፩ቆሮ፯÷፲፭) በተለይም "አይገዙም" የሚለው ቃል የመለያየት ሐሳብ ካላመነው ወገን የሚመጣ ከሆነ ያመኑ ሰዎች ጋብቻውን ለማጽናት ግዴታ እንደሌለባቸው ያመለክታል።

ያመነው ወገን ጋብቻውን ለማጽናት ሞክሮ ሳለ ያላመነው ጋብቻውን ቢያፈርስ ጥፋቱ ያላመነው ሰው ነውና ያመነው ከተጠያቂነት ነጻ ነው። ከባልና ከሚስት ያላመነው ወገን ተለይቶ መሄድ ወይም መፋታት ሲፈልግ ያመነው ወገን ‹‹ባሳምናት መልካም ነበር››፣ ‹‹ባሳምነው ይድን ነበር›› በሚል አጉል ተስፋ ተይዞ ጋብቻውን ለማጽናት መታገሉ ከንቱ ድካም ነው።

ያመነው ወገን ወደ መፋታት የሚመራውን የመጀመሪያ እርምጃ አይራመድ እንጂ የማያምነው ወገን መፋታት ቢወድ ይለያዩ። ያላመነው ባልየው ቢሆንና ሚስቲቱ ክርስቲያን በምትሆንበት ጊዜም ከላይ የተጠቀሰው ሐሳብ ሁሉ አይለወጥም። ማለትም በወንድም ሆነ በሴቲቱ በኩል ቢሆን ሕጉና ሥርዓቱ አንድ ነው።

በዚህ ንዑስ ርእስ ሥር የተጻፉትን አንቀጾች ሐሳብ በአጭሩ ስናስቀምጠው ፦ ወደ ክርስትና ከመምጣታቸው አስቀድሞ ጋብቻ የፈጸሙ ባልና ሚስት ከሁለቱ አንዱ ወደ ክርስትና ቢመጡ ያላመነው ወገን ጋብቻውን ሊያፈርስም ሆነ ባለበት ተቀብሎ ሊኖር ሙሉ ሥልጣን አለው። ወደ ክርስትና የመጣው ግን ጋብቻውን የማፍረስ ምንም ሥልጣን የለውም። ወደ ክርስትና የመጣው ወገን ጋብቻውን የማፍረስ ሥልጣን ያላገኘበትን ምክንያት ‹‹ልዩ ልዩ ጥያቄና መልስ›› በሚለው ክፍል ውስጥ ተብራርቷል።

ጥያቄ ፫.

### ከክርስቲያን ባልና ሚስት አንዱ ወገን ሃይማኖቱን ሲክድ ምን ይደረጋል?

ቀደም ሲል ሳያምኑ የተጋቡ ሰዎች ከሁለቱ አንዱ ወደ ክርስትና ሃይማኖት ሲመጣ የሚፈጠረውን ችግር ለመፍታት የሚወሰደውን እርምጃ ተመልክተናል። ባልና ሚስት ክርስቲያኖች ከጋባቻቸው በኋላ አንዱ ወገን ለብቻው ወደ ክህደት ቢያዘነብል ምን ማድረግ ይገባል?

በክርስትና ሃይማኖት የሚኖሩ ወንድና ሴት ከተጋቡ በኋላ አንደኛው ወገን ከሃይማኖት ሊያፈገፍግና መናፍቅና ከሃዲ ሊሆን የሚችልበት አጋጣሚ አለ። በዚህ ዓይነት ማዕበል እየተገፉ ያሉ በርካታ ቤቶች ይገኛሉ። በዚህ ጊዜ በባልና በሚስት መካከል አለመግባባትና ከፍተኛ የርእዮተ ዓለም ልዩነት መፈጠሩ አይቀርም።

ያላገባች ሴት ካገባች በኋላ በቆይታ ባሏ መናፍቅ ወይም ከሀዲ ሊሆን እንደሚችል አስቀድማ የምታውቅበት ምንም መንገድ የላትም። ለባልየውም ቢሆን እንደዚሁ ነው። ይህ ዓይነት አደጋ ሲፈጠር አስቀድማችኁ ለምን አልተጠነቀቃችሁም ማለት አይቻልም። አስቀድመን ሃይማኖታችንን ለመጠበቅ አስፈላጊውን ጥናቃቄ በማድረግ ሊያገረሹ የሚችሉ ችግሮችን በመንቀስ ካጠራን በኋላ የኑሮ አጋራችንን ከመረጥን ውሎ አድሮ በአንዱ ወገን ለተፈጠረ ከሀዲነት ተጠያቂ አይደለንም። ከሕሊና ወቀሳም ነጻ እንሆናለን።

ከጋብቻ በፊት የትዳር አጋርን የሃይማኖት ይዞታ ማጥናት ብቻ በቂ እንዳልሆነ መረዳት ያስፈልጋል። ባልና ሚስት በሃይማኖታቸው እንዲጸኑ ከጋብቻ በኋላም ስለ ሃይማኖታቸው ምክክርና ክትትል ሊለያቸው አይገባምና። ከጋብቻ በኋላ ሊያገረሹ የሚችሉ ጥርጣሬዎችንና አካሄዶችን ነቅሶ በማውጣት እስኪሽሩና ፈጽመው እስኪድኑ ድረስ በትጋት መኖር ያስፈልጋል።



www.ethiopianorthodox.org



ከዚህ ሁሉ ጥንቃቄና ጥረት በኋላ አንዱ ወገን ወደ ክህደት ሲሳብ "አምላኬ ምን በደልኩህ? እኔ ሃይማኖቴን እወዳለሁ ከዚህ ዓይነት ከሃዲ ጋር ለምን አገናኘኸኝ?" እያሉ ነጋ ጠባ ፈጣሪን ከማማረር መፍትሔ ማፈላለግ ቀዳሚ ስፍራ ሊሰጠው ይገባል። ከጋብቻ በኋላ አንደኛው አካል ሃይማኖቱን ክዶ ሲገኝ በሃይማኖት የጸናው ወገን ከፍቺ አስቀድሞ ሰፊ ትዕግሥት ማሳየት ይጠበቅበታል። ይህም ትዕግሥት የካደውን ለመመለስ በሚደረግ ጥረት መደገፍ አለበት።

ፍቺን መሰል ጉዳዮችን በተመለከተ መጻሕፍተ ቤተ ክርስቲያን ሲመክሩ «ወኢይኩን በጉጉኣ›› ይሉናል። ይህም ‹‹በችኮላ አይሁን›› እንደማለት ነው። ስለዚህ ይህን መሰል ፈተና የገጠመው ባለትዳር ምእመን ለመፋታት ሳይቸኩል ጉዳዩን በትዕግሥት መከታተል አለበት። በዚህ ጉዳይ ትዕግሥት ማጣት ሰበብ እስኪያገኙ እንጂ ቀድሞውንም ጋብቻቸውን ያልፈለጉት ያስመስላልና።

ሁኔታዎች በሚገባ ተጠንተው የካደውን አካል ለመመለስ አስፈላጊው ጥረት ሁሉ ከተደረገ በኋላ አልመለስም ካለ ግን በሃይማኖት ጸንቶ የተገኘው ወገን ፍቺ የመጠየቅ መብት አለው። እንደ አስፈላጊነቱም ፍቺ ሊካሄድ ይችላል። ምክንያቱም በሃይማኖቱ ጸንቶ ለተገኘው ወገን በማሰብ ነው። እርሱም ሆነ ልጆቹ ከሃዲው ባመጣው የምንፍቅና መርዝ መመረዝ የለባቸውምና።

ሲጋቡ ከነበራቸው አቋም ለየት ያለ ነገር ያመጣው ማለትም አዲስ እምነት ይዞ በመምጣት ልዩነት የፈጠረው ወገን ለጋብቻው መፍረስ ኃላፊነቱን ይወስዳል። ሲጋቡ ከነበራቸው ሃይማኖት ወጥቶ እንግዳ ሃይማኖት ማምጣት በጋብቻ ውላቸው መሠረት አለመመራትን ያመለክታል። በዚህ ደግሞ ተጠያቂ የሚሆነው ውል አፍራሽ መሆኑ ግልጽ ነው።

ፍቺው ግድ ሲሆን ያለ ምክረ ካህን መደረግ የለበትም። ይህን ጉዳይ በተመለከተ ያለ ምክረ ካህን የሚደረግ ማንኛውም ውሳኔ

በሃይማኖት ተቀባይነት አይኖረውም። (፩ቆሮ፯፥፩-፯) ቤተ ክርስቲያን ለመንፈሳዊ ጋብቻ ዋና ተዋናይ እንደመሆኗ መጠን ፍቺ ግድ ሲሆንም ኃላፊነቷን ለመወጣት ዕድል ማግኘት አለባት።

በቅዱስ መጽሐፍ እንደተጻፈው ሞትና አመንዝራነት የአንድነት ማሰሪያውን በመበጠስ ጋብቻን ያፈርሱታል። በዚህ ጊዜ በሕይወት የተረፈው ሌላ የማግባት ሥልጣን ይኖረዋል። ስለ ሁለቱም ጉዳዮች ማለትም ስለሞትና አመንዝራነት በቅዱስ መጽሐፍ እንዲህ የሚል ቃል እናገኛለን። ስለዝሙት ወይም አመንዝራነት ‹‹ያለዝሙት ምክንያት ሚስቱን ፈትቶ ሌላዪቱን የሚገባ ሁሉ ያመነዝራል።›› ሲል ስለ ሞት ደግሞ ‹‹ባልዋ ቢሞት ግን ስለ ባልዋ ከሆነው ሕግ ተፈትታለች።›› እንደገናም ‹‹ባልዋ ቢሞት ግን ከሕጉ አርነት ወጥታለች›› ይላል። እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ሞትና አመንዝራነት የጋብቻን ማሰሪያ ለመበጠስ የሚችሉ ነገሮች መሆናቸውን ያስረዳሉ። (ማቴ፲፱፥፱፤ ሮሜ፯፥፪፤ ፯፥፫)

ሞት ባልና ሚስትን ማለያየት መቻሉ ማብራሪያ የሚያሻው ነገር አይደለም። አንድ ባለትዳር ወንድ ሌላ ሚስት ማግባት የሚችለው ሚስቱ ስትሞት ብቻ ሆኖ ሳለ እርሷ ሳትሞት ወደ ሌላ ሴት ሄዶ ካመነዘረ ሚስቱን እንደሞተች ቆጥሯታል ማለት ነው። ስለዚህ በሕይወት ያለች ሚስቱን እንደ ሞተች ቆጥሮ ዝሙት ስለፈጸመ እንደ ሐሳቡ ይደረግበታል። ማለትም እርሱ ራሱ እንደሞተ ይቆጠርና ትዳሩ ፈራሽ ይሆናል። በዚህ ምክንያት ሚስቲቱ አመንዝራ ባሏን ለመፍታት ከእግዚአብሔር ዘንድ መብት ታገኛለች። በባልም በኩል እንዲሁ ነው።

አመንዝራነት የትዳርን ማሰሪያ የሚበጥሰው በዚህ ምሥጢር መሠረት ነው። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን በሐሜትና በአሉባልታ ወይም በመሰለኝና በጥርጥር ሳይሆን አንዱ ወገን ዝሙት መፈጸሙን ራሱ ሲያምን ወይም በብዙ ማስረጃ በተጨባጭ ማረጋገጥ ሲቻል ነው። በዚህ ረገድ ዝሙት የተፈጸመው በወንዱም ሆነ በሴቲቱ በኩል ቢሆን ውሳኔው አንድ ዓይነት ነው።





በገዛ ሰውነቱ ላይ ለግሉ ሥልጣን ያለው ያላገባ ሰው ብቻ ነው። ምንም እንኳን ባልና ሚስት የየራሳቸውን ሥጋ የተሸከሙ ቢሆንም ማናቸውም ቢሆኑ በሰውነታቸው (በሥጋቸው) ላይ ሥልጣን የላቸውም። ሐዋርያው በቆሮንቶስ ክታቡ ‹‹ሚስት በገዛ ሥጋዋ ላይ ሥልጣን የላትም፥ ሥልጣን ለባልዋ ነው እንጂ እንዲሁም ደግሞ ባል በገዛ ሥጋው ላይ ሥልጣን የለውም ሥልጣን ለሚስቱ ነው እንጂ›› ይላል። (፩ቆሮ፯፥፬)

ስለዚህ ካገቡ በኋላ ያለ ትዳር አጋር በራስ ፈቃድ መመራት ‹‹አላገባውም፤ ትዳር የለኝም›› እንደማለት ይቆጠራል። በዚህ መሠረት ባለትዳር ሲያመነዝር ‹‹ትዳር የለኝም›› ማለቱ ነው። ስለዚህ እንደ ሥራውና እንደሕሊናው ይደረግበታልና ትዳሩ በገዛ እጁ ይፈርሳል። አመንዝራነት ትዳርን ያፈርሳል የተሰኘው ለዚህ ነው። ዘማዊው ግለሰብእ ከቃል በላይ በድርጊቱ ‹‹ትዳር የለኝም›› እያለ እንዴት ትዳር ይኖረዋል? ወይም ትዳሩ እንዴት ይጸናል?

ሌላው ሐሳብ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንደሚነግረን መጠራጠርና ሃይማኖትን መካድ አመንዝራነት ነው። አመንዝራነት በትዳር አለመወሰን እንደሆነ ሁሉ ብ‹‹አንዲት ሃይማኖት›› አለመወሰንም አመንዝራነት ይባላል። ሳያምኑ ቀርተው ብዙ ምልክቶችን የፈለጉ አይሁድ ‹‹ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክትን ይሻል›› ተብለው የተገሠጹት ከሴት ጋር ዝሙት ሠርተው ሳይሆን በዚህ አገባብ መሠረት ነው። (ማቴ፲፪፥፴፱)

ሃይማኖትን መካድ አመንዝራነት ብቻ ሳይሆን ሞተ ነፍስም ነው። ሰው ሃይማኖቱን ሲክድ በነፍሱ እንደሞተ ይቆጠራል። ከላይ እንደተብራራው ሞትና አመንዝራነት ደግሞ ጋብቻን ያፈርሳሉ። ታዲያ እንደሞትና አመንዝራነት የሚታየው ሃይማኖትን መካድ ጋብቻን ቢያፈርስ ምን ይደንቃል? ሃይማኖትን መካድ ከአመንዝራነት ያንሳልን? ወይስ ሃይማኖትን መካድ ዝሙትና ሞት የሚያስከትሉትን ያህል ጥፋት የማያስከትል ይመስላችኋልን?

ክህደትና አመንዝራነት ጋብቻን ያፈርሳሉ ሲባል ጋብቻን ሊያፈርሱ የሚችሉ ተግባራት መሆናቸውን ለማሳየት ነው እንጂ

ይህ ክፉ አጋጣሚ የወደቀበት ጋብቻ ሁሉ መፍረስ አለበት ማለት አይደለም። ወይም አንዱ ወገን ያመነዘረውን (የካደውን) ወገን እንዲፈታው የተቀመጠ ትእዛዝ ወይም ድንጋጌ አይደለም። መፍታትና አለመፍታት የተበዳይ መብት ነው።

በዝሙትና በክህደት ምክንያት የተበደለው ባለትዳር መታገሥ እስከቻለ ድረስ ጋብቻው ሊጸና ይችላል። ስለዚህ እነዚህ ምክንያቶች የተዘረዘሩት ተበዳይ መብቱ የት ድረስ እንደሆነ እንዲያውቅ ነው። የቻለውን ያህል ታግሦ ፍቺ የመጠየቅ መብት አለው። ነገር ግን ተበዳዩ ወገን አብሮ ለመኖር እስከፈቀደ ድረስ በዳይ በራሱ ክህደትም ሆነ አመንዝራነት ጠንቅ የፍቺ ጥያቄ የማቅረብ መብት የለውም። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አንድ ባለ ትዳር ራሱ በድሎ ራሱ ፍቺ ጠያቂ መሆን አይችልም። የሁለት ተጻራሪ መብቶች ባለቤት መሆን አይችልምና።

በተጨማሪም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹የማያምን ግን ቢለይ፤ ይለይ።›› ብሏል። (፩ቆሮ፯፥፲፭) ሐዋርያው ይህን ያለው ስለ መብት ድልድል ነው። ሁለት ያላመኑ ሰዎች ከተጋቡ በኋላ አንዱ ወደ ክርስትና ቢመጣ ያልመጣውን ወገን ለመፍታት መብት የለውም። ለምሳሌ፦ ወደ ክርስትና ያልመጣው ወገን ባልየው ቢሆን እርሱ በትዳሩ ለመቆየት እስከፈቀደ ድረስ ክርስቲያን የሆነችው ሚስቱ ልትፈታው መብት የላትም። ለምን ቢባል ሃይማኖቷን የቀየረችው እሷ ሆና ሳለ ፍቺ ጠያቂዋም እሷ መሆን ኣትችልምና ስለዚህ ነው። ባልየው ግን ክርስቲያን ሚስቱን የመፍታት መብት አለው። ሐዋርያው ‹‹የማያምን ግን ቢለይ፤ ይለይ።›› ያለው ይህን ሲያመለክት ነው። በሴቲቱም በኩል ቢሆን የዚህ ቃል ውሳኔ አይለወጥም።

ከላይኛው አንቀጽ የምንረዳው ከጋብቻ በፊት በነበራቸው ሃይማኖት ላይ ለውጥ ያመጣው ወገን የመፍታት መብት የሌለው ሲሆን በዚያው ሃይማኖቱ ጸንቶ የተገኘው ግን ከፈቀደ መፍታት መብቱ መሆኑን ነው። ካልፈቀደ ደግሞ አብሮ መኖር ይችላል።



www.ethiopianorthodox.org



በአጠቃላይ የዚያ ጋብቻ ዕጣ ፈንታ የሚወሰነው በሃይማኖቱ ጸንቶ በተገኘው ወገን ነው።

እንደዚሁም ሁሉ ሁለት ክርስቲያኖች ጋብቻ ከፈጸሙ በኋላ አንደኛው ወገን የቀድሞውን ሃይማኖቱን ቢተው የዚያ ጋብቻ የወደፊት ዕጣ ፈንታ መወሰን ያለበት በሃይማኖቱ ጸንቶ በተገኘው ወገን ነው። እርሱ ከፈቀደ ፍቺ የመጠየቅ መብት አለው። ሁኔታዎችን ታግሼ እኖራለሁ ካለ ደግሞ ዐቅሙ እስከፈቀደለት ድረስ ታግሶ ይቆያል ማለት ነው።

በዚህ ሁሉ ሂደት የካህናት ሚና ከፍተኛውን ቦታ ይይዛል። ሐዋርያው ‹‹የትዳር ጉዳይ ይቅርና በመላእክት እንኳን እንድንፈርድ አታውቁምን?›› በማለት ችግር በተፈጠረበት ትዳር የካህናት ብይን ካላቸው ሥልጣን አንጻር ሲታይ እጅግ አነስተኛው መሆኑን ጠቁሟል። ካህናት የነፍስ አባት እንደመባላቸው መጠን በሕይወታችን ከዚያም በላይ ኃላፊነትና ሥልጣን አላቸውና። (፩ቆሮ፮፥፫)

በዚህ አጋጣሚ ካህናት የተበደለው ሰው ትዕግሥት እንዳያጣና በችኮላ ትዳር እንዳይፈርስ ተበዳይን ያረጋጋሉ፣ ያስተምራሉ። በዳይን ገሥጸው ለመመለስ ጥረት ያደርጋሉ። ተበዳይ ፍቺ ለመጠየቅ የሚያበቃውን ምክንያት ቢያገኝም ሰበብ ፈልጎ በችኮላ ወደ ፍቺ እንዳይሄድ ፍቺ መጠየቅ የሚኖርበትን ትክክለኛ ጊዜ እንደ ጥፋቱ ዓይነት መርምረው ጊዜ ይወስናሉ። ወይም ተበዳይ ምን ቸገረኝ ብሎ ዝሙትና የሃይማኖት ክህደት ሲፈጸምበት ዝም ብሎ በመቀመጥ የዝሙትና የክህደት ተባባሪ እንዳይሆን ያደርጋሉ። መውሰድ ያለበትንም ውሳኔ ደረጃ በደረጃ ያሳያሉ።

ጥያቄ ፬.

ለምን እኛ ብቻ እነርሱ ለምን አይጠነቀቁም?

ኢአማንያንና መናፍቃን እኛን ከማግባት ለምን አይጠነቀቁም እኛ ብቻ ለምን እንጠነቀቃለን? የሚለው ጥያቄ የብዙ ሰዎች ነው። መልሱ አጭርና ግልጽ ነው። የሞተ አህያ ጅብ ይፈራልን?

የበሰበሰስ ዝናብ ይፈራልን? እንደዚሁ ከሃዲ ክህደትን አይፈራም። ወይም ለሃይማኖቱ ግድ አይኖረውም።

በልዕልና ነፍስ ያለ ሰው እወድቃለው ብሎ ይፈራል። ወድቆ ገደል ውስጥ ያለ ሰው እወድቃለሁ ብሎ ይፈራልን? ገንዘብ ያለው እዘረፋለሁ ብሎ ይሰጋል። ምንም የሌለው ደሀ እዘረፋለሁ ብሎ ይሰጋልን? በጭራሽ አይሰጋም። ቢሰጋም መሠረት የሌለው ከንቱ ስጋት ነው። ወይም አንድ ከሃዲ ሰው በሃይማኖት ከማይመስሉት ጋር ለመጋባት ሲቀርብ ‹‹ማን ያውቃል?›› የማይፈራበት ሌላ ዓላማ ይኖረው ይሆናል። ስለዚህ አንተ መጠንቀቅ የሚኖርብህ ሃይማኖትህ የቀና በመሆኑና የበርካታ መንፈሳዊ ጸጋዎች ባለቤት ስለሆንክ ነው።

በሃይማኖት ከማይመስሉት ሰው ጋር አለመጋባት እውነተኛ ሃይማኖት አንዲት ብቻ መሆኗን ከማመን ይመነጫል። ቅዱስ ጳውሎስ እውነተኛ ሃይማኖት አንዲት ብቻ መሆኗን ሲስረዳ ‹‹አንዲት ሃይማኖት›› ብሏል። (ኤፌ፬÷፬) አንተ በዚህ ሐዋርያ ቃል ከልብ ታምናለህን? ወይስ እንደ በርካታ መናፍቃን በመጽሐፍ ቅዱስ ይመን እንጂ ‹‹ሁሉም ክርስቲያን ነው›› ትላለህ? በእርግጥ ሃይማኖት አንዲት ብቻ መሆኗን ካመንክ በሃይማኖት ከማይመስሉህ ጋር መጋባት የለብህም።

ሌሎች የእምነት ድርጅቶች ለምን ተከታዮቻቸውን ከሌላ ሃይማኖት ተከታይ ጋር እንዳይጋባ አያግዱትም እያሉ መጠየቅ ምንም ፋይዳ የለውም። ማወቅ ያለብን እኛ ወደ ኢአማንያን መሄድ የማይኖርብን ለምን እንደሆነ እንጂ እነርሱ ለምን እንደሚመጡ አይደለም። እኛ ሃይማኖታችን የቀናች ናት ብለን እስካመንን ድረስ አንድ ኢአማኒ ወይም መናፍቅ ወደ እኛ እምነት ሲመጣ አመነ እንጂ ካደ አይባልም። አንድ ምእመን ግን ወደማያምኑ ሰዎች ሲሳብ ካደ ይባላል። ይኸም ባይሆን አንድ ምእመን መጠየቅ ያለበት ስለራሱ እንጂ ሌሎች የሃይማኖት ተቋማት ስላላቸው አቋም ሊሆን አይገባም።





ጥያቄ ፳.

በሃይማኖት የማይመስለኝ እጮኛ (ፍቅረኛ) አለኝ ምን ማድርግ ይገባኛል?

ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖታዊ ሥርዓቶቿን ስትፈጽምና ሥጋ ወደሙን ለምእመኖቿ ስታቀብል በጥንቃቄ ነው። ስለዚህ አንድ ኢአማኒ ከአንድት የቤተ ክርስቲያን ልጅ ጋር በመንፈሳዊ ሥርዓት ጋብቻ ለመፈጸም ፈቅዶ ሊመጣ ይችላል። ይሁን እንጂ ሙሉ በሙሉ ሃይማኖቱን እስካልተቀበለና ተገቢውን ሃይማኖታዊ ሥርዓት እስካልፈጸመ ድረስ ቤተ ክርስቲያን በጋብቻ አትቀበላቸውም።

ለማግባት የተሰናዳው ክርስቲያን የሚጠበቅበት ያላመነውን ወገን ማሳመን እንጂ እንዲሁ በደፈናው ቁርባንን እንዲቀበል ማስማማት ብቻ አይደለም። ማሳመን እና ማስማማት እጅግ የተለያዩ ነገሮች ናቸውና። ይሁን እንጂ ይህን በሚገባ ካለማወቅ ሃይማኖቱን ሳይቀበሉ ቅዱስ ቁርባንን ለመቀበል ብቻ ፈቃደኛ የሆኑ ባል ወይም ሚስት አገኘን እያሉ ይዘው በመምጣት ቤተ ክርስቲያንን የሚያውኩ በርካታ ሰዎች አሉ።

አስቀድሞ እንደተገለጸው በሃይማኖት የተለያዩ ወንድና ሴት በአጋጣሚ ተቀራርበው ለመጋባት ቢወስኑ በእውነተኛ ክርስትና የሚገኘው ወገን ሌላኛውን ወገን እንዲያምንና እንዲጠመቅ የማድረግ ኃላፊነት አለበት። እንዲያምን ማድረግ ማለት በሚገባ ተረድቶ ሃይማኖቱን በፈቃዱ እስኪቀበለው ድረስ ግንዛቤ ማስጨበጥ ማለት ነው። በዚህ መንገድ ማሳመኑና ማስጠመቁ ከጋብቻቸው በፊት ቀደም ብሎ መከናወን ይኖርበታል።

አማኒው ግለሰብእ ለዚህ ዓላማ ይረዳው ዘንድ ከጋብቻቸው ሥርዓት በፊት ወደ ሩካቤ ከሚያመሩ ከማንኛውም ግንኙነቶች መቆጠብ አለበት። ቅድመ ጋብቻ ሩካቤ መፈጸም ያላመነው ወገን እንዲያምን የሚደረገውን ጥረት ግቡን እንዳይመታ የማድረግ ኃይሉ ከፍተኛ ነውና። በእርግጥ በክርስትና በማንኛውም ሁኔታ



www.ethiopianorthodox.org

ቅድመ ጋብቻ ሩካቤ ኃጢአት ነው፡፡ በሃይማኖት በተለያዩ ሰዎች መኻል ደግሞ እጅግ በጣም በአጽንዖት ይወገዛል፡፡

ያዕቆብ ሴት ልጁን አህዛባዊ ለሆነው ለሴኬም ከመስጠቱ በፊት የእምነት ምልክት የሆነውን ግርዛት እንዲፈጽም አድርጓል፡፡ ስለዚህ ያላመነን ወንድ ወይም ያላመነችን ሴት አሳምኜ አገባለሁ ያለ ማንም ቢኖር ማሳመን ብቻ ሳይሆን የእምነት መገለጫ የሆነውን ጥምቀተ ክርስትና ከጋብቻው አስቀድሞ እንዲቀበሉ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ (ዘፍ፴፬÷፲፫-፲፱)

አበው "የአፍ ዘመድ በገበያም አይገድ" እንደሚሉት ካልተጠመቁ በአፍ ብቻ አምኛለሁ ማለት አይረባም፡፡ አምኛለው ያለ ሰው ሃይማኖቱን እስከ መጠመቅ ደርሶ ግልጽ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ያዕቆብ ሴት ልጁን ሲሰጥ አማቹ ሴኬም ማመኑ ብቻ አልበቃውም፡፡ ግዝረት እንዲፈጽም አድርጎታል፡፡ ግዝረት ደግሞ ቅዱስ ጳውሎስ እንደገለጠው የጥምቀት ምሳሌ ነው፡፡ (ቆላ፪÷፲፩) ስለዚህ ያመነ ሰው እንደ ሴኬም ሁሉ እምነቱን በመጠመቅ መግለጥ አለበት፡፡

"ከተጋባን በኋላ ይጠመቃል (ትጠመቃለች)" የሚል ማሳበቢያ በሃይማኖት ተቀባይነት የለውም፡፡ ካላመነ (ካልተጠመቀች) ጋብቻውስ በምን መልኩ ሊፈጸም ይችላል? ጋብቻ መፈጸም ያለበት በክርስቲያናዊ ሥርዓት በቅዱስ ቁርባን ነውና፡፡ አሳማኝ የሚመስሉ በርካታ ምክንያቶች ቢደረደሩም "ከጋብቻችን በኋላ ይጠመቃል (ትጠመቃለች)" በማለት የሚፈጸም የተስፋ ጋብቻ ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት ጋር አብሮ ስለማይሄድ ተቀባይነት የለውም፡፡

በቁርባን ላለማግባት «ወደ ፊት በደንብ ስለ ቁርባን ተምረን፣ አውቀንና ተዘጋጅተንበት እንቆርባለን፡፡» በሚል ሰበብ ያለ ቁርባን የተጋቡ ብዙ ምእመናን አሉ፡፡ ሆኖም የሚበልጡት ከጋብቻቸውም በኋላ ደግሞ የማያልቅ ምክንያት እየደረደሩ ያለ ሥጋ ወደሙ ይኖራሉ፡፡ ይህ ምሳሌ የጽድቅን ሥራ ለነገ ማሳደር ምንም እንደማይጠቅም ያስተምራል፡፡ ታዲያ «ነገ ያምናል ከነገ ወዲያ





ይጠመቃል» የሚል ተስፋ ብቻ ሰንቆ ካላመነ ሰው ጋር ጋብቻ መፈጸም እንዴት ይቻላል?

ሳያምን ‹‹አምኛለሁ›› በማለት ጥምቀቱንም ሆነ ሌላውን ምሥጢር እስከመፈጸም ድረስ የሚደፋፈር ሰው ካለ በራሱ ላይ የእሳትን ፍም የሚሰበስብ ሰው ነው፡፡ በሥራው የአርዮስ አምሳያ ነውና፡፡ ከአማንያን የሚጠበቀው ፍርድን ለፈጣሪ በመተው ያላመነው እስኪያምንና እስኪጠመቅ ድረስ መትጋት ነው፡፡ አምነው እስከመጠመቅ ያልደረሱትንም ከማግባት መቆጠብ ሃይማኖትን ማክበርና መጠበቅ ነው፡፡

ልማድና ሃይማኖት የተለያዩ ነገሮች ናቸው፡፡ በሀገራችን ባለው ልምድ ብዙ ጊዜ ሴቶች ወደ ባላቸው ሃይማኖት ይሳቡና የራሳቸውን ሃይማኖት ሲተዉ ይስተዋላል፡፡ ከዚህም በመነሣት ወንድ ልጅ ወደ ሴቲቱ ሃይማኖት የተሳበ ከሆነ "አፈር ይብላ! እርሱ ምን ወንድ ነው?" ይባላል፡፡ በዚህ ልማድ ተጽዕኖ ሥር የወደቁ ሴቶች እንዲህ ዓይነት ነገር ሲገጥማቸው ባላቸውን ወደ እነርሱ ሃይማኖት ለመሳብ ይቸግራቸዋል፡፡ ሆኖም ግን እነርሱ የሚኖሩባት ሃይማኖት እውነተኛዋ መሆኗን እስካመኑ እስከተረዱ ድረስ በጾታ ጉዳይ ታስሮ ሃይማኖትን መተው "ስለወጋችሁ የእግዚአብሔርን ሕግ ትሽራላችሁ" በሚለው የፈጣሪ ቃል ማስወቀሱ አይቀርም፡፡ (ማቴ፲፭÷፫)

## ወንዶችን ለማሳመን የሴትነት ኃይል

ሴቶችን ሳይወዱ በግድ በባላቸው ፈቃድ ሥር ለመኖር እንዲገደዱ የሚያደርገውን ማኅበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ችግር ብቻ መመልከት ስሕተት ላይ ይጥላል፡፡ ሴቶች ከሚኖርባቸው ምጣኔ ሀብታዊና ማኅበራዊ ችግር ይልቅ የሚበረታና የወደዷቸው ወንዶች እንዲገዙና እንዲታዘዟቸው የሚያደርግ ጸጋ በተፈጥሮ ተጎናጽፈዋል፡፡ ከዚህ ጸጋ አንጻር ሴት አፍቃሪዋን ማሳመንና በበጎ ትምህርት እንዲኖር ለማድረግ ብቃት አላት፡፡ ሴቶች ይህ ብቃት እያላቸው ምን ላድርግ ‹‹ሴት ሆኜ ተፈጥሬ ነው›› እያሉ ወደ ክህደት ጎዳና ከተሳቡ ተፈጥሮአቸውን እንኳን አላወቁም ያሰኛል፡፡



www.ethiopianorthodox.org

ሚስቶች ሃይማኖትና ምግባር የሌላቸውን ባሎች ሳይሰብኩና ሳያስተምሩ በንጹሕ አኗኗራቸው ማርከው ወደነሱ ማምጣት እንዳለባቸው ሲመክር ቅዱስ ጴጥሮስ እንዲህ ብሏል፦ ‹‹እንዲሁም እናንተ ሚስቶች ሆይ ከባሎቻችሁ አንዳንዶች ለትምህርት የማይታዘዙ ቢኖሩ በፍርሃት ያለውን ንጹሑን ኑሮአችሁን እየተመለከቱ ያለ ትምህርት በሚስቶቻቸው ኑሮ እንዲገኙ ተገዙላቸው፡፡›› (፩ጴጥ፫፥፩-፪)

ባልና ሚስት የተለያየ ሃይማኖት በሚኖራቸው ጊዜ አንደኛው ወገን ግድ ወደ ‹‹አንዲቷ›› የክርስትና ሃይማኖት መመለስ የሚኖርበት ርትዕት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖት እውነተኛዋ ሃይማኖት ስለሆነች ነው እንጂ በማሸነፍና በመሸነፍ መንፈስ ወይም ጾታዊ ጉዳይ እንደ አጀንዳ እየታየ አይደለም፡፡ በሁለቱ ማለትም በባልና በሚስት መካከል አሸናፊም ተሸናፊም የለም፡፡

እውነትነት ያላትን ሃይማኖት አምኖ መቀበል ማሸነፍ እንጂ መሸነፍ እንዴት ይባላል? እውነትን አመላካቹም ግለሰብእ ቢሆን ለእርሱ በቅድሚያ ሃይማኖት ጸጋ ሆና ስለተሰጠችው ለሌላው ለመመስከር ቻለ ይባላል እንጂ እርሱን አሸናፊ ማን አደረገው? ለእርሱም ለራሱ ቢሆን የፈጣሪ ፈቃድ ባይሆንለት ኖሮ እንደሌላው ሰው ሁሉ ከክህደት መውጫ መንገድ ባላገኘ፡፡ ሃይማኖት ጸጋ ሆና የምትሰጥ ናት እንጂ በዕውቀትና በምርምር በራስ ብርታት የምትገኝ አይደለችም፡፡ (ይሁዳ ቁ፫)

## አሳምኖ ማግባትም ችግር ሊኖረው ይችላል

ያላመኑትንና በሃይማኖት የማይመስልን ሰው እንደ ማግባት ችግር እንዳለው ሁሉ ካሳመኑ በኋላ ማግባትም ቢሆን ችግር ሊኖረው ይችላል፡፡ በርካቶች ግን ከተቻለ ያላመኑት አሳምኖ ማግባት ምንም ችግር እንደሌለው አድርገው ያዩታል፡፡ እንደውም አንዳንዶች በቀናች ሃይማኖት የኖሩትን ከማግባት ይልቅ የተሻለና በእግዚአብሔርም ዘንድ የበለጠ ዋጋ የሚያሰጥ ይመስላቸዋል እንጂ ሊያስከትል የሚችለው አደጋ አይታያቸውም፡፡ በአንድ ጎን ብቻ





ሲያዩት ይህ ሐሳብ ልክ ይመስላል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ጉዳይ መታየት ያለበት ከዚህ በተለየ አቅጣጫ ነው፡፡

እንደሚያገረሽ በሽታ ሁሉ ክህደት ተመልሶ ሊመጣ ይችላል፡፡ በሰዓት ተሞልቶ እንደተጠመደ ፈንጂ ጊዜ ጠብቆ የሚፈነዳ የክህደት እርሾ አለ፡፡ ከዚህ ዓይነት አደጋ መዳን የሚቻለው አስቀድሞ እርሾው ካለበት ሰው ራስን በመጠበቅና በመጠንቀቅ ነው፡፡ ወይም ከክህደት የሚመለሱ ሰዎች በችኮላ ከማግባት ረጅም ጊዜ ሰጥቶ ማየት ያስፈልጋል፡፡

ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ሹመት በምትሰጥበት ጊዜ ምንም ሌሎች መስፈርቶችን በሚገባ ያሟላ ቢሆንም ያ ሰው ለክርስትና እንግዳ ወይም "አዲስ ክርስቲያን" ከሆነ በችኮላ ክህነት አትሰጠውም፡፡ ይህም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "አዲስ ክርስቲያን አይሁን" በማለት በደነገገው መሠረት ነው፡፡ (፩ጢሞ፫፥፮)

ይህ የሆነበት ምክንያት ያ ሰው ክርስቲያን የሆነበት ምክንያት በውል እስኪታወቅ ጊዜ ለማግኘት ሲባል ነው፡፡ ዳግመኛም ሌላ ድብቅ ዓላማ ያለው ከሆነም ክፉ ዓላማውን ለማሳካት ቶሎ ዕድል እንዳያገኝ ያደርገዋል፡፡ በተጨማሪም ወዲያው እንደመጣ ለክህነት ሲበቃ በትዕቢት ፃር እንዳይጠቃ ለሰውዬው ሕሊና በማሰብ ነው፡፡

እንደ ክህነት ሁሉ ጋብቻም ባል በሚስት፣ ሚስት ደግሞ በባሏ ላይ ሥልጣን የሚያገኙበት መንፈሳዊ ሥርዓት ነው፡፡ ታዲያ አንዲት ክርስቲያን ሴት ያላመነውን ሰው አሳምና ብታገባው ያ ሰው በሚገባ መንገድ ስለማመኑ በምን እርግጠኛ መሆን ትችላለች? ምክንያቱም ልጁ እርሷን ላለማጣት ብሎ ብቻ ክርስቲያን ለመሆን ወስኖ ሊሆን ይችላልና፡፡

ዳግመኛም "ምን ታመጣለች! ከጋብቻዬ በኋላ ወደ ቀደመ እምነቴ እመለሳለሁ" የሚል ድብቅ ዓላማ ሊኖረውም ይችላል፡፡ ስለዚህ አንዲት ሴት ሃይማኖት ያልነበረውን ሰው አሳምና ብታገባው እንኳን ምናልባት በአንድ ወቅት ሊፈነዳ በሚችል ችግር ውስጥ እየገባች መሆኑን አውቃ መስጋት ይኖርባታል፡፡ የዚህ ዓይነቱ ባል የክህደቱ እርሾ አብሮት ሊቆይ ይችላልና፡፡

በእርግጥ አስቀድሞ ክርስቲያን የነበረ ሰውም ካገባነው በኋላ ሊክድ የሚችልበት ሁኔታ መኖሩ አይካድም፡፡ ነገር ግን ይህን ዓይነቱን ሰው ቢያገቡት ሊክድ ስለመቻሉ ለማወቅ ይቅርና ለመጠርጠር እንኳን ባለመቻላችን ኃላፊነት አንወስድም፡፡ ሃይማኖት ያልነበረውን ሰው ግን ካመነ በኋላ የቀደመ ክህደቱ ቢያገረሽበትስ ብሎ መጠርጠር ተገቢ ነገር ነው፡፡

ስለዚህ ክርስቲያኖች ያላመነ ወዳጅ ቢኖራቸው ችግር ከመሆኑ የተነሣ «ከጀመሩት አይቀር!» በሚል ማስተዛዘኛ «አሳምነው ያግቡ» ይባል እንጂ ክርስቲያን ካልሆነ ሰው ጋር ቢያምንም እንኳን ለጋብቻ መዋዋል በራሱ አንድ የሆነ አደጋ ሊኖረው እንደሚችል አስቀድሞ ሊታሰብበት ይገባል፡፡ ይህን ሲባል ነገርን አስፍቶ ማየት እንደሚገባ ለመጠቆም ነው እንጂ ከኢአማኒነት ወደ ክርስትና የመጡ ሁሉ ቆይቶ ክህደት ያገረሽባቸዋል ማለት እንዳልሆነ ተገንዘቡልኝ፡፡

ስለዚህ ይህን ለሚመስል ችግር ጥሩ መፍትሔው በመጀመሪያ ክርስቲያን ካልሆነ ሰው ጋር ወደ ጋብቻ የሚያመራ ዓይነት ቅርርብ አለመጀመር ነው፡፡ አሳምኜ ላግባው የሚለው ሐሳብ በመጀመሪያ ባልታሰበበት ቅርርብ የተነሣ መለያየት አዳጋች ሲሆን በመጨረሻ የሚደረስበት ውሳኔና አማራጭ ነው እንጂ የተሻለው መንገድ "ከማያምኑ ጋር በማያመች አካሄድ" ከወዲሁ "አለመጠመድ" ነው፡፡ (፪ቆሮ፮÷፲፬)



www.ethiopianorthodox.org



# ምዕራፍ ስምንት

## ‹‹ከማያምኑ ጋር›› ማኅበራዊ ኑሮ

እንደሚታወቀው በዚህ ዓለም ክርስቲያኖች በቦታ ለብቻቸው ተለይተው በአንድ ለእነርሱ ተብሎ በተከለለና በተወሰነ ቦታ ብቻ አይኖሩም፡፡ በልዩ ልዩ መንገድና አጋጣሚ ወደ ኢአማንያን ሀገርና መንደር ገብተው ይኖራሉ፡፡ ወይም ኢአማንያን ወደ እነርሱ ይመጣሉ፡፡ ዓለም የተፈጠረችው ክፉዎችና መልካሞች በአንድነት ሊኖሩባት ነውና፡፡ ስለዚህ በዚህች ዓለም ክርስቲያኖች ከማያምኑ ጋር አብረው ሊኖሩ ግድ ነው፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ምእመናን ‹‹ከሴሰኞች ጋር እንዳትተባበሩ በመልእክቴ ጻፍሁላችሁ›› ካለ በኋላ በመካከላችሁ ከሚገኙ ሴሰኞች እንጂ ‹‹በጠቅላላው የዚህን ዓለም ሴሰኞች… አላልኩም›› ይላል፡፡ ለምን ቢባል ‹‹ይህስ ቢሆን ከዓለም ልትወጡ ይገባችሁ ነበር›› በማለት ንግግሩን ያስራል፡፡ እውነት ነው! ከማያምኑና ከዓለማውያን ሰዎች ጋር በጣም ወሳኝ በሆኑ ርእሰ ጉዳዮች በሃይማኖት፣ በሥርዓተ አምልኮ፣ በማዕድ በጋብቻ ወዘተ በመጠኑ ራሳችን እንለያለን እንጂ በቦታ ከእነርሱ ተለይተን አንኖርም፡፡ እንዲያ ቢሆን ከዚህ ዓለም መውጣን ይኖርብን ነበር፡፡ (፩ቆሮ፭÷፱-፲፫)

እስራኤል በአሕዛብ መኻል እንደኖሩ ክርስቲያኖችም በማያምኑ ሰዎች መኻል መኖራቸው የሚፈለግበት ጎን አለው፡፡ እግዚአብሔር ከግብጽ አውጥቶ እስራኤላውያንን ወደ ምድረ ርስት ሲያገባ በወቅቱ የነበሩትን አሕዛብ ሙሉ ለሙሉ ማጣፋት ይቻለው ነበር፡፡ ነገር ግን የተወሰኑትን ብቻ ካጠፋ በኋላ ሌሎቹ እንዲተርፉ አደረገ፡፡ ይህም እስራኤላዊያን ከአሕዛብ ጋር ተጎራብተው እንዲኖሩ በመፈለጉ ነው፡፡ ለዚህም ሊጠቀሱ የሚችሉ በርካታ ምክንያቶች አሉ፡፡

ቀደም ሲል አሕዛብ ከእስራኤላዊያን በምግባር ተሽለው መገኘታቸው ‹‹የእግዚአብሔር ሕዝብ›› ለተባሉ ወገኖች ታላቅ ዘለፋ ነበር፡፡ ዛሬም ቢሆን በዙሪያችን የሚገኙ ሃይማኖት የሌላቸው

ሰዎች በምግባር ከኛ ከክርስቲያኖች ተሽለው ከተገኙ እንድናፍር የምንዘለፍባቸው ማነጻጸሪያዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ‹‹ብታንሱ ብታንሱ ከአሕዛብ ታንሱን?›› በሚል እንወቀስበታለንና የእኛ የክርስቲያኖች በማያምኑ ሰዎች መካከል መኖር ግድ መሆኑ ሳይቀር ጠቃሚ ገጽታም አለው፡፡

እስራኤል ፈጣሪያቸውን ሲያሳዝኑ በአሕዛብ ይማረኩና ይቀጡ ነበር፡፡ ተጸጽተው ሲመለሱ ደግሞ በታላላቅ ተአምራት ከአሕዛብ ክንድ ይወጡና ፈጣሪያቸውን ያመልኩ ነበር፡፡ ከዚህ አንጻር ስናየው አሕዛብ ለእስራኤል እንደመቅጫ መሣሪያ ወይም እንደ መግረፊያ አለንጋ ነበሩ ማለት ነው፡፡ በክርስቲያኖችም ዘንድ እንዲሁ ነው፡፡ አሕዛብና መናፍቃን በሕገ አምላኩ ለማይኖር ክርስቲያን መቀጫው ናቸው፡፡ በእነርሱ ምክንያት ብዙ ጊዜ አእምሮው ይቆስላል፣ ይቆጣል፣ ይታወካል፣ ሰላም ያጣል፣ ይጨነቃል፣ ይናደዳል፣ ይፈራል፣ ይሰጋል፣ ይጎዳል፣ በስሜት ይቃጠላል፣ ይንጠለጠላል ወዘተ፡፡ ገፋ ካለም ሊጨቆን፣ ሊማረክ፣ ሊታሰር፣ ሊሰቃይና ሊገደልም ይችላል፡፡ ስለዚህ ኢአማንያን ክርስቲያኖችን ከብበው መኖራቸው ሊሆን የሚገባ ነገር ነው፡፡

የማያምኑ ሰዎችን ያለአግባብ ከእኛ ብናርቃቸው ማንን አይተውና ከማን ተምረው ያምናሉ? ተስፋቸውስ ምንድር ነው? ‹‹እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ›› የሚለውስ የፈጣሪ ቃል የት ጥቅም ላይ ይውላል? (ማቴ፭÷፲፬) ታዲያ እኛ ለእነርሱ አብነት እንሆን ዘንድ ከማያምኑ ጋር መኖር አይገባንምን?

የፈተና ብዛት የክርስቲያኖችን ክብር ያበዛዋል፡፡ ምእመናን በአህዛብና በመናፍቃን መኻል ካልኖሩ የሚፈተኑበት መንገድ ይቀንሳል፡፡ ፈተና ሲያንስ ደግሞ የሚገኝ ክብርም ይቀንሳል፡፡ ክርስቲያኖች ፈታኝ ከሆኑ ኢአማንያን ጋር ባላቸው ማኅበራዊ ኑሮ ለሚያጋጥማቸው መሰናክል በሚያሳዩት ቁርጠኝነት ብዙ ጸጋ ያገኛሉ፡፡

ሰይጣን ለምን ኖረ? በዚህ ዓለም ክፋ ነገሮችስ ለምን ይኖራሉ? ብለን ስንጠይቅ የሚቀርብ አመክንዮ ሁሉ ለአሕዛብና ለመናፍቃን በክርስቲያኖች ዘንድ ለመገኘታቸው እንዲሁ ሊጠቀስ





ይችላል፡፡ ማለትም ፈታኝና ጠላት መኖራቸው በጎ ጎን አለው እንደምንለው ሁሉ አሕዛብና መናፍቃንም በዚህ ዓለም ከክርስቲያኖች ጋር መኖራቸው ለምእመናን ጠቀሜታ አለው፡፡ በአንድ ማሳ ላይ እንክርዳድ ከስንዴ ጋር እንደሚኖር ጌታችን በወንጌል ‹‹እስከመከር ጊዜ አብረው ይደጉ›› ብሏልና በእንክርዳድ የተመሰሉ መናፍቃንና አሕዛብ ከክርስቲያኖች ጋር በዚህ ዓለም መኖራቸው ከምጽአተ ክርስቶስ በፊት አይገታም፡፡ (ማቴ፲፫÷፳፬-፴)

ክርስቲያኖች በሕይወተ ሥጋ እስካሉ ድረስ መኖሪያቸው ይህች ዓለም ናት፡፡ በአኗኗር ተለይተው ከክፉ ይሰወራሉ እንጂ በቦታ ከዚህ ዓለም እንደማይርቁ ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ‹‹ከክፉ እንድትጠብቃቸው እንጂ ከዓለም እንድታወጣቸው አልለምንህም፡፡›› ዳግመኛም ‹‹ከዚህ በኋላ በዓለም አይደለሁም እነርሱም በዓለም ናቸው፡፡›› በማለት የተናገረው ትምህርት አዘል የጸሎት ቃል ምስክር ነው፡፡ (ዮሐ፲፯÷፲፭፤ ዮሐ፲፯÷፲፮) አጽራረ ቤተ ክርስቲያን በየትኛውም ዘመን ነበሩ፤ ይኖራሉም፡፡ በሰማይ እንጂ በምድር በሚያምኑና በማያምኑ ሰዎች መካከል የቦታ ልዩነት የለም፡፡

ስለዚህ እኛ ክርስቲያኖች ከማያምኑ ጋር በቦታ ሳንለይ እንኖራለን፡፡ ይህም ማለት በአንድ ዓለም፣ በአንድ አገር፣ በአንድ ሰፍራና መንደር በጉርብትና፣ በአንድ ቢሮ፣ በአንድ ትምህርት ቤት እንሠራለን፤ እንማራለን፡፡ በየብስ፣ በባሕርና በአየር በአንድ ትራንስፖርት በአንድነት እንጓጓዛለን፡፡ የሁሉንም ሃይማኖት ዜጋዎችን በሚያቅፉ ልዩ ልዩ ተቋማት ውስጥ፣ ሁኔታዎች ሲያስገድዱ ደግሞ በአንድ ቤትም ውስጥ ከማያምኑ ሰዎች ጋር መኖር እንዳለም እናውቃለን፡፡ ይህ ሁሉ ኃጢአት አይደለም፡፡ ከማያምኑ ጋር በአንድ ቦታ መኖር ኃጢአት አይደለምና፡፡

እንዲያውም አንድ የራሱን ሃይማኖት በሚገባ የሚያውቅና በፈጣሪው የሚተማመን ክርስቲያን በሥራም ሆነ በትምህርት የማያምኑ ሰዎች ወዳሉበት ቦታ ሲመደብ ፈጣሪ አንድ መንፈሳዊ ሥራ እንደሰጠው ያስባል እንጂ ፈተና ላይ መውደቁ ነው አይልም፡፡ ምንም እንኳን እንደ መናፍቃን የሰውን መብት ጥሶና

ተዳፍሮ ልስበካችሁ ማለት ተገቢ አካሄድ ባይሆንም አብሮ በመኖር በሚፈጠር ዕድል የሃይማኖታችንን እውነታ በቃልም ሆነ በምግባር ላላመኑ ሰዎች ለመግለጥ አጋጣሚ ማግኘት ለኛ ለክርስቲያኖች እጅግ ሊያስደስተን ይገባል።

ክርስቲያኖች ‹‹ከማያምኑ ጋር›› አብረው ሲኖሩ ምን ማድረግና እንዴት መኖር እንዳለባቸው መማር ይኖርባቸዋል። ይህን ጥበብ ካላወቁ የከፋ ችግር ላይ ይወድቃሉ። ከማያምኑ ጋር እስከመጋባት ሳንቀራረብ እንደደመኛም ሳንራራቅ ልከኛ በሆነ አቀራረብ በፍቅር አብረናቸው እንድንኖር ቅዱስ መጽሐፍ ያስተምረናል።

ምን ጊዜም ቢሆን ሰዎች ክፉ ሥራ ሠርተው ስንመለከት ባለማወቅ እንደፈጸሙት እያሰብን ልናዝንላቸው ይገባል። ነገር ግን ክፉ ግብራቸው ግን ወደ እኛ እንዳይዛመትና እንዳይጎዳን መጠንቀቅና ራሳችንን መጠበቅ ያስፈልገናል። መሸሽ የሚኖርብን ክፉ ግብራቸውንና ክህደታቸውን እንጂ ሰብአዊ ተፈጥሯቸውን አይደለምና። የማያምኑ ሰዎች በተፈጥሮ ወገኖቻችን ናቸው።

## ‹‹ከሰው ሁሉ ጋር›› በሰላም መኖር

አማኒ ሆኖ ከማያምኑ ጋር ተጋብቶ መኖር በመንፈሳዊ ሕግ ክልክል ነው። ይሁን እንጂ ምእመናን ከማያምኑ ጋር ሌላ ዓይነት ማኅበራዊ ኑሮ ሊኖራቸው ይችላል። ክርስቲያኖች ሃይማኖታዊ አቋምን በሚያናጉ ጉዳዮች ላይ ጥንቃቄ በማድረግ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም መኖር ይገባቸዋልና። መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ›› ይላልና። (ሮሜ ፲፪፥፲፰) ‹‹ከሰው ሁሉ ጋር›› ሲል ከሚያምኑም ሆነ ከማያምኑ ጋር ማለቱ እንደ ሆነ ግልጽ ነው።

በብርቱ ቢፈልጉና ቢጥሩም ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም መኖር ሊያስቸግር ይችላል። ምክንያቱም ሰላም በይዘቱ ማኅበራዊ ነውና። ስለዚህ የአንዱ ወገን ሰላም ፈላጊ መሆን ብቻውን ሰላምን



www.ethiopianorthodox.org



አያስገኝም። ሐዋርያው ‹‹ቢቻላችሁስ›› ያለው በዚህ ምክንያት ነው። እኛ ብንፈልግም ማን ያውቃል ሰላምን የማይሻ ወይም ስለ ሰላም ምንም ዋጋ መክፈል የማይፈልግ ሰው ይኖር ይሆናል።

እንዲያውም በወንጌል ‹‹የሚገድላችሁ ሁሉ እግዚአብሔርን እንደሚያገለግል የሚመስልበት ጊዜ ይመጣል።›› ተብሎ እንደተጻፈው የሰውን ሕይወት በማጥፋት ጭምር ጽድቅን እንደሚወርሱ የሚያምኑና የሚሰበኩ ሰዎችም ይኖራሉ። (ዮሐ ፲፮፥፪) ዛሬ በዓለማችን ላይ ሌላውን አጥፍተውና ሠውተው ፈጣሪያቸውን ደስ ለማሰኘት የሚሽቀዳደሙ ሰዎች እጅግ ተበራክተው የሚታዩት ከዚህ የተሳሳተ የእምነት ስብከታቸው የተነሣ ነው። ዳሩ የራሱን ሕይወት ክቡርነት ሳያውቅ አጥፍቶ በመጥፋት ከሚያምን ከንቱ ሰው ክብርን፣ ትዕግሥትን፣ ፍቅርንና ሰላምን መጠበቅ ዘበት ነው። ቢሆንም በእኛ በኩል ‹‹ሰላምን እሻ፥ ተከተላትም›› ትእዛዝ አለ። (መዝ ፴፫፥፲፬)

ምንም እንኳን በወሬ ብቻ እንጂ በሥራ ሰላምን የማያውቋት ሰዎች በርካታ ቢሆኑም ወይም ስለ ሰላም ደንታ የሌላቸው ብዙ ሰዎች ሊኖሩ ቢችሉም እኛ ግን በግላችን ማድረግ የሚኖርብን ነገር ይኖራል። በሰላም መደፍረስ ከተጠያቂነት ነጻ የምንሆነው በኛ በኩል ማድረግ የሚኖርብንን በሙሉ አድርገን ስንገኝ ብቻ ነው። ይኸም ሐዋርያው በሰላም ስለመኖር *‹‹በእናንተ በኩል››* የሚቻላችሁን አድርጉ ባለው ቃል ይታወቃል። ስለዚህ እኛ ክርስቲያኖች ከማያምኑ ሰዎችም ጋር ቢሆን በሰላም ለመኖር በእኛና በኩል የሚጠበቅብንን ሁሉ በመፈጸም ጥረት ማድረግ አለብን።

## የማያምኑትን አለመምሰል

በክርስቶስ ክርስቲያን የተሰኙ ምእመናን በሥጋ መኖሪያቸው ይህች ዓለም ብትሆንም አኗኗራቸው ግን ከዓለማዊያን ይለያል። ክርስቲያኖች ከዓለም ተመረጡ እንጂ ከዓለም አይደሉም። (ዮሐ ፲፭፥፲፱) በአመለካከት፣ በምርጫ፣ በሚከተሉት የኑሮ ዘዬ፣ በእምነትና በምግባር ከዚህ ዓለም ልዩ ናቸው። ይሁን እንጂ

የሚኖሩት በዓለም ውስጥ ነው፡፡ የሃይማኖታቸው ራስና ፈጻሚ የኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥት ከዚህ ዓለም እንዳይደለች እነርሱም ምንም በዓለም ላይ ቢኖሩም ከዚህ ዓለም አይደሉም፡፡ (ሉቃ፲፯፥፳፩፤ ዮሐ፲፯፥፲፬-፲፮) ክርስቲያኖች የወልደ አምላክ የኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥት ዜጎች ናቸውና፡፡ ‹‹እኛ አገራችን በሰማይ ነውና›› እንዲል ቅዱስ መጽሐፍ፡፡ (ፊልጵ፫፥፳)

‹‹ይህን ዓለም አትምሰሉ›› የሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሕግ ክርስቲያኖች ዓለማዊ እንዳይሆኑ ብቻ ሳይሆን ዓለምንም እንዳይመስሉ የሚከለክላቸው ነው፡፡ (ሮሜ፲፪፥፪) ራስን ከዓለም ስመለየት ደግሞ በርካታ ነገሮችን ማስተዋልና ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡

እኛ ክርስቲያኖች በሃይማኖታችንና በምግባራችን ከዓለማዊ አኗኗር በተለየ መልኩ እንድንኖር ‹‹ይህን ዓለም አትምሰሉ›› ተብለን ታዘናል፡፡ (ሮሜ፲፪፥፪) ‹‹አትምሰሉ›› ማለት ‹‹ልዩ ሁኑ፤ ወይም ተለዩ›› ማለት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ይህ ግን በቦታ ራቋቸው ማለት ሳይሆን በአመለካከት፣ በቃልና በምግባር ከዓለም ‹‹ልዩ›› ሆናችሁ የራሳችሁን ማንነት ጠብቃችሁ ተገኙ ማለት ነው፡፡

ክርስቲያኖች ዓለምን ባለመምሰላቸው የሚደርስባቸው ጭቆናና ብዙ በደል አለ፡፡ ዓለም የራሱ የሆነውን ይወዳል፤ የራሱ ያልሆነውን ግን ይጠላል፡፡ (ዮሐ፲፭፥፲፱) ክርስቲያኖች በዓለም እየኖሩ ከዓለም ስላይደሉ በዓለም ዘንድ ይጠላሉ፡፡ ይሁን እንጂ ክርስቲያኖች ማንንም በጥላቻ መንፈስ ማየት የለባቸውም፡፡ ጌታችን ‹‹ይህንም የሚያደርጉባችሁ እኔንና አብን ስላላወቁ ነው›› እንዳለ ክርስቲያኖች ክፉ ሲደርስባቸው እንዲህ የሚያደርጉት ፈጣሪን ስለማያቁ ነው ብሎ በማመን ሁሉ ጊዜ አርአያ የሚሆን ሥራ እየሠሩ መታገሥ አለባቸው፡፡ (ዮሐ፲፮፥፫)

ከማያምኑ ጋር እንዴት መኖር እንደሚገባ ማወቅ ግድ ነው፡፡ ይህን ለመረዳት መጀመሪያ የራስን ሃይማኖት ጠንቅቆ ማወቅ ከዚያም በኋላ የኢአማንያኑን አጠቃላይ ይዘት መመርመር ይገባል፡፡ በተፈጥሮ፣ በአስተዳደግ፣ በልምድ፣ በባህል፣ በትምህርት፣ በምጣኔ





ሀብት፣ በዕድሜና በጾታ ወዘተ በዙሪያችን ካሉ ሰዎች ጋር ያለንን አንድነትና ልዩነት ካላወቅን ራሳችንን የት ቦታ ላይ ማስቀመጥ እንዳለብን አናውቅም፡፡ ልዩነታችንን ጠብቀን ከማያምኑ ሰዎች ጋር በምን ዓይነት ርቀት መጓዝ እንዳለብን ማወቅ የምንችለውም አስቀድመን ስለራሳችን ቀጥሎም ስለሌሎች እምነት በቂ ግንዛቤ ሲኖረን ብቻ ነው፡፡

ክርስቲያኖች በአጠቃላይ የአኗኗር ከማያምኑ፣ ከመናፍቃንና ከከሃድያን የተለዩ መሆን አለባቸው፡፡ ምእመናን ከኢአማንያን ሰዎች ጋር ሲኖሩ ለልዩነታቸው ትኩረት ሰጥተው መሆን አለበት፡፡ ስለ ሕገ አምልኮ፣ ስለ ሰላምታ አሰጣጥ፣ አብሮ ስለመመገብ፣ በሕይወት ጉዳይና በሃይማኖታዊ ጽንሰ ሐሳቦች ዙሪያ ከማያምኑ ጋር ስለመወያየት፣ በአለባበስና በበዓላት አከባበር ተለይቶ ስለመታወቅ፣ በአብሮነት ምክንያት አጋንንት ስለያሚመጡት ፈተና፣ ከማያምኑ ጋር የሚደረግ ጋብቻ ስለሚያስከትለው አስከፊ ነገር ወዘተ በሚገባ ሊማሩ ያስፈልጋቸዋል፡፡

በአለባበስ መለየት ማለት የአንገት ክር በማሰር፣ በበዓላት ጊዜ መልካም ምሳሌነት ባለው ነጭ ልብስ በመሸለም፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲሄዱ ደግሞ ነጠላ ለብሶ በማደግደግ ወዘተ ልዩ መሆን ማለት ነው፡፡ በዘወትር አለባበሳችንም ቢሆን የኢአማንያንንና የሴሰኞችን የአለባበስ መንገድ ወደ ጎን በመተው ሐዋርያው እንዳስተማረን ‹‹እግዚአብሔርን ለሚፈሩ›› ማለትም ለክርስቲያኖች እንደሚገባ ብቻ ልናጌጥ (ልንሸለም) ያስፈልጋል፡፡ (፩ጢሞ፪፥፱-፲)

## የማያምኑትን እንዴት እንያቸው?

በመንፈሳዊነት ሰበብ የማያምኑ ሰዎችን ማግለል፣ መናቅና መጠየፍ ስሕተት ነው፡፡ ሃይማኖታችንንም ትዝብት ውስጥ ይጥላል፡፡ እኛንም በፈጣሪ ዘንድ ያስጠይቀናል፡፡ ከሃይማኖት ውጭ የሆኑ ሰዎችን መጥላት፣ ንቆ ማየትንና መጠየፍን ሃይማኖታችን አይፈቅድምና፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስ ለማያምኑ ሰዎች በነበረው የተሳሳተ አመለካከቱ ተወቅሶ ነበር፡፡ (የሐዋ፲፥፲፫-፲፭፤ ፲፥፳፰)

የሃይማኖት ትምህርት ለማያምኑ ሰዎች ያለንን አመለካከት መልክ ያሲዘዋል፡፡ ለማያምኑ ሰዎች ያለን አመለካከት ከቅዱስ መጽሐፍ በጠራ መንገድ በተማርነው እንጂ ከገጠመኞቻችን፣ ካየነውና ከሰማነው ወይም የማያምኑ ሰዎች ከሚያንጸባርቁት የአራዊት ጠባይ አንጻር የተመሠረተ መሆን የለበትም፡፡ ምንም ያህል ግፍ ቢያደርጉብን ቅዱስ መጽሐፍ ደግሞ ‹‹ጠላቶቻችሁን ውደዱ፣ ለሚያሳድዷችሁ ጸልዩላቸው፡፡›› ይለናል፡፡ (ማቴ፭፥፵፬-፵፭)

## ለመልካም ሥራቸው ዋጋ መስጠት

ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ እንደምንረዳው በአንዳንድ ስፍራ አሕዛብ ከእስራኤላዊያን የተሻለ ሥነ ምግባር ያሳዩበት ሁኔታ ነበር፡፡ ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ‹‹እውነት እውነት እላችኋለሁ በእስራኤል እንኳን እንዲህ ዓይነት እምነት አላገኘውም›› ሲል የመሰከረለት ሮማዊው መቶ አለቃ ያሳየው የእምነት ብቃት በዘመኑ እምነት ከሚጠበቅባቸው እስራኤላውያን በላይ ነበር፡፡ (ሉቃ፯፥፱)

በተመሳሳይ መንገድ ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹የዚያም ዓይነት ዝሙት በአሕዛብ እንኳ የማይገኝ ነው፡፡›› በማለት የቆሮንቶስ ክርስቲያኖችን በገሠጸበት አንቀጽ አልፎ አልፎ ከአሕዛብ ጥቂቶቹ ከአንዳንድ ክርስቲያኖች በምግባር ተሽለው የሚገኙበት ቦታና ጊዜ እንዳለ አሳይቷል፡፡ (፩ቆሮ፭፥፩፤) ይሁዳ እስራኤላዊ ሆኖ ሳለ አሕዛባዊቷን ትዕማርን ‹‹ከእኔ ይልቅ እርሷ እውነተኛ ሆነች፡፡›› በማለት የሰጠው ምስክርነት በዚህ አንቀጽ የሰፈረውን ሐሳብ የሚያጸድቅ ነው፡፡ (ዘፍ፴፰፥፳፮)

በእርግጥ ሃይማኖት የሌለው ሰው መልካም ሥራ መሥራቱ ብቻ በፈጣሪ ፊት ጻድቅ አያደርገውም፡፡ ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚነግረን ‹‹ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልምና፡፡›› (ዕብ፲፩፥፮) ቢሆንም እኛ ክርስቲያኖች የማመንን አስፈላጊነት ለመግለጽ ብለን በጅምላ መልካም ሥራን ዋጋ ቢስ አናደርግም፡፡



www.ethiopianorthodox.org



ሃይማኖት የሌላቸው ሰዎች የበጎ ምግባር ባለቤት መሆናቸው ብዙ ጠቀሜታ አለው፡፡ ከክርስቲያኖች አንጻር ካየነው አብዛኛውን ጊዜ የክርስቲያኖች ፈተና የሚመነጨው ከኢአማንያን ክፉ ሥራ እንደመሆኑ መጠን ለክርስቲያኖች ብዙ ፈተና ይቀልላቸዋል፡፡ ከራሳቸው ከአሕዛብ አንጻር ካየነው ደግሞ ማን ያውቃል ፈጣሪ መልካም ምግባራቸውን ተመልክቶ ወደ እውነተኛ ሃይማኖት የሚመጡበትንና የሚድኑበትን መንገድ ያመቻችላቸው ይሆናል፡፡

የኢአማንያን መልካም ሥራ ያለ እውነተኛ ሃይማኖት ብቻውን ጽድቅን ባያመጣም መቼም ቢሆን የሚበረታታ ነገር ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ቢሆን መልካም ሥራን የሚያንኳስስ ትምህርት የላትምና፡፡ የማያምኑ ሰዎችን አለማመንና የልብ ክፋት የምናወግዘውን ያህል መልካም ሥራ ሲናይባቸው ሚዛናዊ በሆነ መንገድ እናበረታታቸው፡፡ ሕጻን ልጅ ሲያበረታቱት ለመቆም ይሞክራል፡፡ የጀመረው እብድ ደግሞ ‹‹እብድ እብድ›› ሲሉት የበለጠ ያብዳልና፡፡

የማያምኑ ሰዎች እግዚአብሔር በተፈጥሮ ለሰው ልጆች የሰጠውን ማስተዋል ተጠቅመው መልካም በመሥራት ቢጸኑ ፈጣሪ ወደሚድኑበት እውነተኛ ሃይማኖት ይመራቸዋል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከነናዊቷ ሴት፣ ቆርኔሌዎስ በአሕዛብነት ሳሉ እጅግ የሚያስመሰግን ሥራ የሠሩ ናቸው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ክርስትና ከመምጣቱ በፊት ለቀደመ እምነቱ የሚቀና ታማኝ ሰው ነበር፡፡ ነገር ግን ፈጣሪውን በመውደድ እንጂ ለግል ጥቅሙና በሰው ፊት ለመመስገን ፈልጎ አልነበረም፡፡ ይህም መንፈሳዊና ንጹሕ ቅናቱ ለድኅነት ጥሪ አበቃው፡፡ (ማቴ፲፭፥፳፩-፳፰፤ የሐዋ፲፥፩-፵፰፤ የሐዋ፱፥፩-፴፫) የደከሙበትን የማይነሣ አምላክ የጽድቅ ሥራቸውን አይቶ ወደሚድኑበት ሃይማኖት ሳባቸው ለጥምቀተ ክርስትናም በቁ፡፡ (ማቴ፲፭፥፳፩-፳፰፤ የሐዋ፱፥፩-፴፫ የሐዋ፲፥፩-፵፰) ስለዚህ ሳያምኑ የሠሩት መልካም ሥራ ብቻውን ባያድንም ዋጋ የለውም ማለት አይደለም፡፡ ወደ እውነተኛዋ ሃይማኖት ለመድረስ መነሻ ምክንያት ይሆናልና፡፡

ክርስቲያኖች የማያኑትን እንደጠላት መቁጠር ሳይሆን መውደድ ይኖርባቸዋል፡፡ ክርስቲያኖች እንደ አህዛብ ለሃይማኖት ያላቸውን እውነተኛ ቅናት የሚያሳዩት ያላመኑትን፣ በመጥላት ፊት በመንሣት በማሳደድና በመግደል አይደለም፡፡ አህዛብ የሚሠሩትን መልካም ሥራቸውን ሁሉ እንደ እኛ ካላመናችሁ ምንም አይረባችሁም እያልን ሚዛናዊነት በጎለው ስብከት ተስፋ ብናሳጣቸው ጉዳቱ ብዙ ነው፡፡ ያሉበት እምነትና መንፈስ ራሱ ሰላም ነስቷቸው ሳለ ‹‹በጨለማ ላይ ጥላ›› እንዲሉ ተስፋ ካስቆረጥናቸው ምንም በጎ ነገር ሊገኝባቸው አይችልም፡፡ ተስፋ ከሌለው ሰው ምን በጎ ነገር ትጠብቃላችሁ?

ይልቅ ለአህዛብ የሚሆነውን የተስፋ ቃል ከወንጌል በመጥቀስ ማስነበብ አለብን፡፡ ጌታችን በወንጌል ‹‹ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ፤ እነርሱን ደግሞ ላመጣ ይገባኛል፡፡›› በማለት የተናገረው ቃል ያላመኑ ሰዎች ያላቸውን ተስፋ የሚያሳይ ነው፡፡ (ዮሐ፲÷፲፮) ያላመኑ ድምፁን ቢሰሙና ቢያምኑ ይድናሉ፡፡ ከመንጋውም ይጨመራሉ፡፡ ‹‹አንድም መንጋ ይሆናሉ እረኛውም አንድ›› (ዮሐ፲÷፲፮)

አሕዛብ ባለማመን የሚኖሩት እኛ ክርስቲያኖች ሁላችንም በየአቅጣጫው ኃላፊነታችንን ባለመወጣታችን ነው፡፡ ስለዚህ በደላቸውን እንካፈላለን ማለት ነው፡፡ አህዛብ ከፈጣሪ ለክርስቲያኖች የተሰጡ የቤት ሥራዎች ነበሩ፡፡ እኛ ለጨለማው ዓለም በሚገባን መጠን ብርሃን አልሆንም፡፡ አልጫውንም ለማጣፈጥ ጨው አልሆንም፡፡ ‹‹እነርሱን ደግሞ ላመጣ ይገባኛል፡፡›› በማለት የተናገረውን ቃል ተግባራዊ አላደረግነውም፡፡ ልናመጣቸው እንደሚገባን አላሰብንበትም፡፡ ታዲያ አህዛብ በሚያደርሱት ጉዳት መወቀስ ያለበት ማን ነው እነርሱ ወይስ እኛ? እነርሱ ‹‹ፍጥረታዊ ሰው›› ናቸው፡፡ በቃ! እኛ ግን የክርስትና መንፈስ ያለን ነን፡፡ አህያን ተራገጠ፣ በሬን ተዋጋ ብሎ የሚከስ ማን ነው? እርግጥ ሰው ምንም ቢሆን ከእንስሳት ይበልጣልና እነርሱም በጥፋታቸው ተጠያቂ እንደሚሆኑ አይካድም፡፡ ይሁን እንጂ የማያምኑ ሰዎች በሚፈጽሙት ኃጢአት ክርስቲያኖች ሳይወቀሱ አይቀሩም፡፡



www.ethiopianorthodox.org



## ወደ መናፍቃን አዳራሽ፣ ወደ መስጊድ እና ጠንቋይ ቤት ስለመሄድ

እኛ ክርስቲያኖች በቦታ ከማያምኑ ሰዎች ሳንለይ በአኗኗር ብቻ ማንነታችንን ጠብቀን መኖር እንዳለብን አስቀድመን ተምረናል፡፡ ይሁን እንጂ በቦታም የምንለይበት ቦታ አለ፡፡ ይኸውም ለምሳሌ፡- ከመስጊድ፣ ከመናፍቃን ‹‹የጸሎት ቤት››፣ ጠንቋይ ቤት፣ ዛርና ባዕድ ነገር ሁሉ ከሚመለክባቸው ቦታዎች ፈጽመን ራሳችንን መጠበቅ አለብን፡፡

ክርስቲያኖች ወደተጠቀሱት ቦታዎች በመሄድ የፈጣሪያችንን ማስጠንቀቂያ አንጥስም፡፡ ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህ ሁሉ ከመሆኑ በፊት አስቀድሞ ‹‹ማንም እነሆ ክርስቶስ ከዚህ አለ ወይም፡- ከዚያ አለ ቢላችሁ አትመኑ›› በማለት ማስጠንቀቂያ ሰጥቶናልና፡፡ (ማቴ፳፬÷፳፫) ስለዚህ እንኳን ሌላ ባዕድ አምላክ ተከትሎ መሄድ ይቅርና ‹‹ክርስቶስ ከዚህ አለ›› ብንባል እንኳን ከቤተ ክርስቲያን ተለይተን የትም መሄድ የለብንም፡፡

፩ኛ. ክርስቲያኖች የማንንም ሃይማኖት ያከብራሉ፤ አይገዳደሩም፡፡ ሳይደርሱባቸው ሌሎች ካሉበት ቦታ ሄደው ሁከት አያስነሡም፡፡ እንዲህ ማድረግ ወንጀልና ኃጢአት ከመሆኑም ባሻገር የመንፈሳዊነት መገለጫ አይደለምና፡፡ ይህን በመሰለ የሥነ ምግባር ጉድለት ክርስቲያኖች ስማቸው መነሣት የለበትም፡፡ ስለዚህ ወደ ባዕዳን የአምልኮ ስፍራዎች ምን ልንሠራ እንሄዳለን?

፪ኛ. ምንም ምክንያት ቢደረደር ወደማያምኑ ሰዎች የአምልኮ ቦታ መሄድ ስለራስ እምነት መጠራጠርን ያሳያል፡፡ እምነትህ ፍጽምትና እውነተኛ መሆኗን ካመንክ ወደሌላ ቦታ ለምን ትሄዳለህ? ያንተ እምነት እውነተኛ ከሆነች ሌሎች ሐሰተኞች መሆናቸውን እርግጠኛ ስለምትሆን የእነርሱ ላንተ አያስፈልግህም፡፡ ልሰብካቸው ነው እንዳትል ሌላው አምልኮቱን በሚፈጽምበት ቦታ ሄዶ ካልሰብክኋችሁ ማለት በራሱ ትልቅ ጥፋት ነውና ልትሞክረው አይገባህም፡፡

እስኪ ልያቸው ትል ይሆናል፡፡ የዚህም መዘዙ ብዙ ነው፡፡ አንተ ማየትህን ብቻ ታውቃለህ ሰይጣን ምን እንደደገሰልህ ግን አታውቅም፡፡ የያዕቆብ ልጅ ዲና የአሕዛብን ልጆች ጫወታ ልታይ ወጣች ነገር ግን ተደፍራ ዕድሏ ሁሉ ተሰነካከለ፡፡ (ዘፍ፴፬÷፩-፴፩) በቀላሉ ልይ ማለት አንተ ከምታስበው ውጭ ውጤት ሊኖረው ይችላል፡፡ የማይገባህን ከማድረግ ራስህን ጠብቅ፡፡

በዚህ ምክንያት ክርስቲያኖች እንደ ቅዱስ ዳዊት ወደ እግዚአብሔር ቤት በመሄድ ደስ ይላቸዋል እንጂ ወደማይገባቸው ቦታ አይሄዱም፡፡ (መዝ፻፳፩÷፩) ባዕድና ክፉ አምልኮ ወደሚፈጸምበት ስፍራ አለመሄድ ለፈጣሪ መታዘዝን፣ ማስተዋልን፣ ግብረ ገብነትና ፍጹም የሆነ የልብ እምነት መኖሩን ያመለክታል እንጂ መፍራትና በራስ አለመተማመን አይደለም፡፡

ጠቢቡ ሰሎሞን ‹‹ኃጢአተኞች ቢያባብሉህ እሺ አትበል፡፡›› እንዳለ መናፍቃን ‹‹ምን ትሆናለህ? ለአንድ ቀን ብቻ ነው፡፡ አብረን እንሄድ፣ ልጋብዝህ፣ አንተ ደግሞ እናንተ ዘንድ ስትጋብዘኝ እመጣለሁ፣ በግድ የሚይዝህ የለም፡፡ ደስ ካላለህ ትተኸው ትወጣለህ፡፡›› ወዘተ እያሉ ቢያባብሉህም ‹‹እሺ አትበላቸው!›› (ምሳ፩÷፲)

ሐዋርያው እንደተናገረው ሰይጣን ‹‹የስሕተት አሠራር›› አለው፡፡ (፪ተሰሎ፪÷፲(፲፪)) ሰይጣን በፈለገው ጊዜና ቦታ ተአምራትን፣ ምልክቶችንና፣ ሐሰተኛ ድንቅ ነገሮችን በማድረግ ሕዝብን እንዳያሳስት እግዚአብሔር ይከለክለዋል፡፡ ነገር ግን ቦታ መድበው በሚያገለግሉትና በሚያመልኩት ሰዎች ዘንድ ይህን ለማድረግ መብት ተሰጥቶታል፡፡ ይህን ሲያስረዳ ‹‹ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል›› ይላል፡፡ (፪ተሰሎ፪÷፲፪) ‹‹ይልክባቸዋል›› የተባለው እግዚአብሔር መሆኑን ልብ በል፡፡ ባልታዘዙት ሰዎች ላይ እንዲያታልላቸው ፈጣሪ ለሰይጣን መብት ይሰጠዋል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ አንተ በመናፍቃን አዳራሽ ስትገኝ የዚህ መብቱ ሰለባ ትሆናለህ፡፡

የሰይጣን ተንኮል በእምነት ጋሻ ካልሆነ በስተቀር በሰው ሥጋዊ ጥበብ አይመከትም፡፡ ‹‹ዓለምን የሚያሸንፈው እምነታችን



www.ethiopianorthodox.org



ነው›› እንዲል፡፡ (፩ዮሐ፭÷፬) ወፍጮ ቤት ገብተህ ዱቄት አይንካኝ ማለት እንደማይሆን ሁሉ ወደ መናፍቃን አዳራሽ ከሄዱ በኋላ ክህደታቸውና መንፈሳቸው አይጠጋኝ ማለት አይቻልም፡፡ ይህን ካልፈቀድህ ለምን ትሄዳለህ?

ሰው በራሱ አቅም እንኳን በሰይጣን አሠራር ይቅርና ለማታለል በተዘጋጁ ሰዎችም ሊታለል የሚችል ደካማ ነው፡፡ በሌቦችና በጠንቋዮች በተደጋጋሚ የሚታለል የሰው ልጅ ‹‹እኔን ሰይጣን አያታልለኝም›› ቢል ራሱን ያሞኛል እንጂ የሚያምነው የለም፡፡

## ‹‹መብል አትብሉ››

ከማያምኑ ጋር አብሮ በመብላት አለመተባበር ባህልም ጭምር ስለሆነ ጉዳዩን በማስረጃ ለመደገፍ ካልሆነ በቀር ጥቅስ መጥቀስ አያሻውም፡፡ ምክንያቱም እስላሙም ሆነ ክርስቲያኑ በኀዘንና በደስታቸው ለክርስቲያንና ለእስላም የሚሆን ምግብ ለብቻው አዘጋጅተው በማቅረብ አንዱ አንዱን ማስተናገድ ጸሐይ የሞቀው እውነታ ነውና፡፡

ክርስቲያኖች ሲመገቡ ስመ እግዚአብሔርን በመጥራት ጸልየው ስለሆነ ለሌላው ሕሊና ላለመክበድና ሌላውም ቢሆን የራሱን ‹‹ስመ አምላክ›› ጠርቶ ሊበላ ስለሚችል ከማያምኑ ጋር በማዕድ አይተባበሩም፡፡ ሠለስቱ ምእት በሃይማኖተ አበው ‹‹ከመናፍቃን ጋር አብረህ አትጸልይ›› ብለዋል፡፡ ይህ የማዕድ ጸሎትንም ይጨምራል፡፡ የማዕድ ጸሎት ጸሎት አይደለም ለማለት ይቻላል?

ቅዱስ ጳውሎስ ኃጢአተኞችንና ጣዖት የሚያመልኩ ሰዎችን በየግብራቸው ከዘረዘራቸው በኋላ ‹‹እንደነዚህ ካለው ጋር መብል እንኳን አትብሉ›› በማለት ክርስቲያኖችን ያዛቸዋል፡፡ ይህ ለዘወትር ስለሚደረግ ምግብ ነው፡፡ ለበዓላቶቻቸውና ለአምልኮ የሚያዘጋጁትን መመገብ እንደማይገባ ደግሞ ‹‹አሕዛብ የሚሠዉት ለአጋንንት›› መሆኑን ከጠቆመ በኋላ ‹‹የጌታን ጽዋና የአጋንንትን ጽዋ ልትጠጡ አትችሉም፡፡›› በማለት ይደመድማል፡፡ ስለዚህ ክርስቲያኖች

ከማያምኑ ጋር በማዕድ አንድ እንዳይሆኑ ጥብቅ ሥርዓት አላቸው ማለት ነው። (፩ቆሮ፭÷፲፩፤ ፩ቆሮ፲÷፳-፳፩)

## ‹‹ሰላም ተባባሉ››

ሰላምታ በዘመናችን ሁለት መገለጫ አለው። አንዱ የጥንቱን ወግ ሳይለቅ ሃይማኖታዊ ይዘቱን የጠበቀ ሰላምታ ነው። ለሰላምታ መሠረቱ ሃይማኖት ነውና። ይህም በየሰዓቱ ‹‹እግዚአብሔር ይመስገን!›› ለማለት ዓይነተኛ መንገድ ሲሆን መጠይቁ ‹‹እንዴት ዋላችሁ? እንዴት አደራችሁ?›› የመሳሰለው ሁሉ ነው። ‹‹የክርስቲያን ደሴት›› በሆነች አገራችን ይህን መሰል ሰላምታ ከመንፈሳዊነቱ አልፎ ብሔራዊ መልክ ይዞ እስከ አሁን ደርሷል።

ሁለተኛው ደግሞ መደበኛም ባይሆን ከማንኛውም ዓይነት ሰው ጋር ተነጋግሮ አንድ ጉዳይ ለመፈጸም እንደ መግቢያና ነገር ማንሻ የምንጠቀምበት ሰላምታ ነው። ይህም እንደምንቀርበው ሰው አገር፣ ቋንቋ፣ ባህል፣ ሃይማኖት ወዘተ ሊለያይ ይችላል። የኛን የሰላምታ አቀራረብ ያልለመዱ ወይም ያልወደዱ ሰዎች ካሉ እስኪረዱን ድረስ የጋራ የሆነውን ይህን መንገድ ተጠቅሞ ግብን መምታት ማለፊያ መንገድ ነው።

ክርስቲያኖች የማይቀበሉትና ምላሽም የማይሰጡት ዓይነት ሰላምታ ይዞ የሚመጣ ሰው አለ። ይኸውም የክህደት ሰባኪ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ መልኩ የማያምኑና ትምህርተ ክርስትናን ይዘው የማይመጡ ሰዎችን ሰላም እንዳንላቸው በቤታችንም እንዳንቀበላቸው ያዛል። ትእዛዙን ሲያጠናክረውም ‹‹ሰላም የሚለው ሰው በክፉ ሥራው ይካፈላልና›› ይላል። (፪ዮሐ፲-፲፩) ይህም ትእዛዝ የወንጌልን የፍቅር እርሻነት ያሳያል።

እስኪ አስቡት! ደጃችሁን ዘግታችሁ በተቀመጣችሁበት ሃይማኖታችሁ ምን እንደሆነ እንኳን ሳያውቁ ለሚዳፈሯችሁ ወይም በአንገታችሁ የክር ማኅተማችሁን እየተመለከቱ ሌላ ሃይማኖት እንስበካችሁ ለሚሉ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹ሰላም አትበሏቸው›› ብቻ ብሎ ማቆሙ ትልቅ አክብሮትና ፍቅርን



www.ethiopianorthodox.org



ማስተማር አይደለምን? እንዲህ ባለ ደፋር ሰው ሌላስ ቅጣት አይገባውም ነበርን? ሌላ ሃይማኖት ቢሆን እንኳንስ እንዲህ ሲሰበክ እርሱ ራሱ ሰብኮ ያላመነለትን አንገትህን እበጥሳለሁ እንደሚል የታወቀ ነው። በሸሪያ ሕግ መሠረት በሳውዲ አረቢያ ክርስትናን ማስፋፋት በሞት እንደሚያስቀጣ ስንቶቻችን እናውቃለን?

ሰው በችኮላ ወይም በሌላ ምክንያት ማንንም ሰላም ሳይል ይችላል። ነቢዩ ኤልሳ ደቀ መዝሙሩ ግያዝን አስቸኳይ መልእክት ባዘዘው ጊዜ ማንንም በመንገድ ሰላም እንዳይል አስጠንቅቆት ነበር። (፪ነገ፬÷፳፱) እኛ ክርስቲያኖች ማንም ሰላም ባይለን በቀና መንገድ ለማየት አንቸገርምና አያስጨንቀም። ይሁን እንጂ ጽንፈኛ በመሆን ብሔራዊነትን ሸጠው፣ አረባዊነትን ተላብሰው እኛ በመረጥነው መንገድና ቋንቋ ሰላም በሉን ብንባል አገርንም ሃይማኖትንም ማበላሸት ነውና አንቀበልም። ከመንገድ አቁመውና ከቤታችን ገብተው እንስበካችሁ የሚሉንንም አንሰማም። እንዲህ ዓይነቶቹን ሰዎች ቁመናቸውን አክብሮ ሸበታቸውን አፍሮ ቆሞ የሚሰማቸው፣ በቤቱም የሚቀባላቸው ምእመን ካለ ወንጌል እንደመሰከረልን ‹‹በክፉ ሥራቸው ይካፈላል።›› (፪ዮሐ፲-፲፩) በዚህ መንገድ ካልመጡ ከሁሉም ጋር ሰላምታ በመለዋወጥ፣ ለጋራ ጥቅም እየሠራን በአንዲት አገር በፍቅር እንኖራለን።

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር**
**ወለወላዲቱ ድንግል**
**ወለመስቀሉ ክቡር**